# ኢትዮጵያዊው፡ጃንደረባ



ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ

Ethiopian Bookstore

Brought to you by

**Ethiopian Bookstore**

https://t.me/etbookstore

## መግቢያ

ይህ መጽሐፍ ስለ አንድ ኢትዮጵያዊና አፍሪካዊ ሰው የአንድ ዕለት የመንገድ ላይ ገጠመኝ የሚተርክና የሚተነትን መጽሐፍ ነው፡ ፡ ታሪኩን የጻፈለት ቅዱስ ሉቃስ ስለዚህ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ የጻፈልን ጥቂት አንቀጾችን ቢሆንም ይህ አጭር ገጠመኝ ግን ስለ ሰውዬው የፊት ማንነትና የኋላ ታሪክ የሚጠቁሙ ብዙ እውነታዎችን የያዘ የተቆለፈ ሳጥን ነው፡፡ በሙያው ሠዓሊ የሆነው ወንጌላዊው ሉቃስ ምስል ከሳች በሆነ አጻጻፍ የጻፈልን በሰረገላ ላይ ተጀምሮ በሰረገላ ላይ የተጠናቀቀው የኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ውብ ታሪክ ለመላው የአፍሪካ ክርስቲያን እጅግ የሚያኮራ ፤ የጌታችንን መስቀል ከተሸከመው ሊቢያዊ አይሁድ በመቀጠል የዓለም ጥቁር ሕዝብ በኩራት የሚያነሣው ታሪክ ነው፡፡

‹‹በይሁዳም በሠማርያም እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ›› ተብለው የታዘዙት ሐዋርያትና አርድዕት ስብከታቸውን ‹ከሴም ድንኳን› ከይሁዳና ሰማርያ የጀመሩ መሆናቸውን የሚተርከው የሐዋርያት ሥራ ሁለተኛው የወንጌል ብርሃን ተቀባይ ደግሞ ካም ሆኖ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ መጠመቁን ይተርካል፡፡ ስለዚህ የጃንደረባው ታሪክ በጳውሎስ ስብከት ካመኑት የያፌት ወገኖች

ቀድሞ የወንጌልን ችቦ የተቀበለው ‹የካም ነገድ› ሁሉ ፊታውራሪ ሆኖ መታየቱን የሚያበሥር የመላው አፍሪካውያን ደስታ የሆነ ታሪክ ነው፡፡

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በመጨረሻ ተጽፎ የምናገኘው ኢትዮጵያዊ ነው፡፡ ከእርሱ ቀድማ የሰሎሞንን ጥበብ ልታይ እንደሔደችው ንግሥት የሰሎሞንን መቅደስ ሊሳለም ሔዶ እውነተኛውን ሰሎሞን የዳዊት ልጅ ክርስቶስን ተሳልሞ የተመለሰ ኢትዮጵያዊ ታሪክ ነው፡፡ የሳባ ንግሥት ከሰሎሞን ልጅን ይዛ መጣች ፤ ይህ ጃንደረባ ግን ‹ልጅነትን› ይዞ መጣ፡፡ ይህች አነስተኛ መጽሐፍ በጌታችን አንደበት ስለ ንግሥተ አዜብ ‹እርስዋ በዚህ ትውልድ ላይ ተነሥታ ትፈርዳለች› ከተባለ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባስ ምንኛ ይፈርድብን ይሆን? በሚል ፍርሃት የእርሱን ነገር ለማስታወስ የተጻፈ መጽሐፍ ነው፡፡

ጃንደረባው ሊዘነጋ የማይገባ ታሪክ ያለው ኢትዮጵያዊ ነው፡፡ እርግጥ ነው ዓለም እያጋነነች የምታወራው የጦረኞችን ፤ የቀማኞችን ፤ የተዋጊዎችን ፤ የእምቢተኞችን ፤ የአትንኩኝ ባዮችን ታሪክ ነው፡፡ ከኢትዮጵያዊያንም ቢሆን ከጀግኖቻችን የሚበዙት የጦር ሜዳ እንጂ የሰላማዊ ሜዳ አይደሉም፡፡ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ግን ትሕትና ገድሉ የሆነ ትሑት ሰው ነው ፤ እጁ ላይ

ያገኘነው መማሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው፡፡ ሲኮፈስ ሳይሆን በትሕትና ሲያወራ ፣ ‹አሁን ይኼ ጠፍቶኝ ነው!› ሲል ሳይሆን ሲጠይቅ የተገኘ ትሑት ኢትዮጵያዊ ነው፡፡ ከአፉ የተሰማ ብቸኛ ፉከራም ‹እንዳልጠመቅ ማን ይከለክለኛል› የሚል ብቻ ነበር፡፡ ከብዙ ጀግኖች ከብዙ ባለታሪኮች የበለጠ ዋጋ ያላት ነፍሱን ያዳነ ሰው ታሪክ ነው፡፡

ጃንደረባው ባኮስ ለመንፈሳዊ መጻሕፍት ንባብ ፣ መጽሐፍ ቅዱስን ለመመርመርና ለመተርጎም ፣ ወደ ቅዱሳት መካናት መንፈሳዊ ጉዞን ለማድረግ ፣ በፖለቲካ ሥልጣን ላይ ሆኖም ሃይማኖትን ለመከተል ምሳሌ የሚሆን ሰው ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ እንግዲህ የጃንደረባውን አጭር ታሪክ እንተነትናለን፡፡ ከዚያ በፊት ግን የሁለት መምህራንን የመንደርደሪያ ጽሑፎች አስቀድማለሁ፡፡

የጃንደረባው ንባብ ይሁንልን

ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ

## መንደርደሪያ አንድ

ግብረ ሐዋርያት (ምዕ.፰፥፳፮-፵) ላይ ታሪኩ የተመዘገበው ኢትዮጵያዊ የመንግሥት ባለሥልጣን (ጃንደረባ) በመንፈስ ቅዱስ ምሪት በሐዋርያዊው ዲያቆን ፊልጶስ ጥምቀተ ክርስትና እንደተፈጸመለት ያስረዳል። መጽሐፍ ቅዱስ የዚህን ጥሙቅ "የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ፣ በገንዘብዋም የሠለጠነ" ብሎ ኃላፊነቱን ሲገልጽ፣ አንዳንድ የውጭ ጸሓፊዎች ከንግሥት ሕንደኬ ጋር በማገናኘት ስሙን "ላካሳ" (Lacasa) "ኢንዳ" (Inda) "ኢንዲካ" (Indica) ብለው ይጠሩታል።

ኢትዮጵያውያን ምንጮች ደግሞ ስሙ "ባኮስ" እንደሆነ የሚናገሩ ሲሆን መንግሥታዊ ኃላፊነቱን ደግሞ "ሕጸዋ ለሕንደኬ" በማለት ይገልጻሉ። የጥንት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች እና ሊቃውንት (ለምሳሌ ቅዱስ ሄሬኔዎስ፣ አውሳብዮስ ዘቂሳርያ፣ ዮሐንስ አፈወርቅ) ስለዚህ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ እና ስላጠመቀው ቅዱስ ፊልጶስ በሰፊው ጽፈዋል። አንዳንዶቹ ድርሳናትም ወደ ግዕዝ ቋንቋ ተመልሰዋል።

ጃንደረባው በብሉይ ኪዳን እምነት የጠነከረ እና የጠለቀ መጻሕፍትን የማንበብና የመጠየቅ ልምዱ ለእኛ ትውልድ በእጅጉ አስተማሪ ነው። "ለንባብ ጊዜ የለኝም" ለምንል ጃንደረባው በሠረገላ

እየተጓዘ እንኳን ያነብ እንደነበረ ስናይ እኛስ ብለን እንድንጠይቅ ይጋብዘናል።

የጃንደረባው ንባብ ብቻ ሳይሆን ፊልጶስ በጉዟቸው ላይ ባጭሩ የሰበከለትን ወንጌል አምኖ የሚቀበል ልቡና እና ለውጤት መብቃቱ ነበር። ውጤቱም "መኑ ይከልአኒ ተጠምቆ" በማለቱ ይታወቃል። ባጭር ሰዓት አምኖ ለጥምቀት በቃ። ብዙዎች ለዓመታት የሚሰሙት ትምህርት ሲለውጣቸው የማይታየው ከጃንደረባው ያነሰ እምነት ስለያዙ ነው። አገልጋዮችም እንደ ፊልጶስ የመንፈስ ቅዱስን ምሪት የሚቀበሉ እና ለተልዕኮ የሚፋጠኑ ቢሆኑ የሚፈለገውን ለውጥ ሊያመጡ እንደሚችሉ ይኸው የመጽሐፍ ክፍል ያስረዳል።

የጃንደረባውን ታሪክ እና ከእርሱ ማንነት ጋር ተይይዘው የሚነሱትን ጥያቄዎች (ለምሳሌ የጃንደረባው ዜግነት፣ የሚያነበው መጽሐፍ ቋንቋው በምን የተጻፈ ነበር? አጥማቂው ፊልጶስ ዲያቆን ወይስ ሐዋርያ? ወዘተ.. የሚሉትን) እና ሌሎች ተያያዥ ርእሶችን በመዳሰስ ማራኪ በሆነ አቀራረብ ከጠለቀ የማሰላሰል አመክንዮአዊ መንገድ ጋር ያቀረበልን ወንድማችን በእጅጉ ሊመሰገን ይገባዋል።

ዲያቆን ሄኖክ በአሁኑ ሰዓት ቤተ ክርስቲያን ካሏት ኹነኛ አገልጋዮች በግንባር ቀደምነት ከሚጠቀሱት አንዱ ሲሆን ለየት

የሚያደርገው በቃልም በመጣፍም ማስተማሩ ነው። ለዚህ ዋቢዎቹ ተወዳጅ ስብከቶቹ እና ካሁን በፊት ለአንባቢዎች ያደረሳቸው መጻሕፍቱ ናቸው።

ይህን ስለ ጃንደረባው ያዘጋጀውን የመጽሐፍ ረቂቅ ተመልከትልኝ ብሎ ሲሰጠኝ በደስታ ተቀበልኩት፣ በጉጉት አነበብኩት። አቀራረቡ ማራኪ ሲሆን፣ እያስተማረ የሚሰብክ መጽሐፍ ሆኖ አገኘሁት። የሚከተለው መንገድ እያንዳንዱን ርእስ ስብከታዊ በሆነ መልኩ በመተንተን ሲሆን በእንግሊዝኛው Homiletical የሚባለው ዓይነት ነው። ይህም ጥንታውያን አበው ድርሳኖቻቸውን የጻፉበት መንገድ ነውና ይበል ያሰኛል።

ከባለቅኔው ከበደ ሚካኤል "የትንቢት ቀጠሮ" (1938 ዓ.ም.) በስተቀር ስለጃንደረባው በስፋት የተጻፈ በሀገራችን እስካሁን አላጋጠመኝም። ስለዚህም ይህ የዲ/ን ሄኖክ ሥራ በዓይነቱም በይዘቱም ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ የሚሰጠው ፋይዳ ብዙ ነው። በመጨረሻም ይህን ግሩም ሥራ ያስነበበንን ዲያቆን ሄኖክ ኀይሌን እያመሰገንኩ፣ ደግመህ ደጋግመህ ጻፍ፤ እኛም በጥልቀት እናንብብ እላለሁ።

ቀሲስ ዶ/ር አምሳሉ ተፈራ
በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥንታውያን ጽሑፎች ጥናት (ፊሎሎጂ) ረዳት ፕሮፌሰር

መንደርደሪያ ፪

ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ በሦስተኛው የሐዋርያዊ ተልእኮ ጉዞው (Third Apostolic Missionary trip) ለሮማና ቆሮንቶስ ነዋሪዎች በጻፈበት መልእክቱ ላይ "ሁሉ ለትምርታችን ተጽፏልና" ፤ "ሁሉ .... ለተግሣጻችን ተጻፈ" የሚሉ ሐረጎች እንደየ ተርታቸው ተከታትለው ይገኛሉ። መጀመርያ ትምህርት ይቀድማል፡፡ ተግሣጽ ደግሞ ሰምቶ ለማይተገብረው እንደ ሆነ ይነገራል። ሰምተነዋል የምንለውም ነገር ፤ ሳንሰማው እንዳይሆን ደግመን መስማት ያስፈልጋል። ሰው በምንድነው የሚሰማው? በምንስ ያያል?! (ሮሜ ፲፭፥፬ ፤ ፩ኛ ቆሮ. ፲፥፲፩)

ሊቃውንት አባቶቻችን "የተጻፈ ሁሉ" የሚለውን ቃል ምርኩዝ በማድረግ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጻፈውን እያንዳንዱን ሓረግ አድማስ ድረስ በሚያዩበት ዓይናቸው በማየት ባዘጋጁልን መንፈሳዊ ሐተታ ሁሉ "ያለ አመክንዮ አልተጻፈም" ብለው፡ ከያዘው ኃይለ-ቃል በላይ፡ ቃላዊውንና ቀጥታዊውን እንዲሁም መንፈሳዊ ትርጉሙን፡ በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት ጽፈዋል። እነዚህ በቤተ ክርስቲያን በኩል ያገኘናቸው አባቶች፤ ቤተክርስቲያን "ማዕከለ-ኵሉ-ማእዝናዊ ማእከለ- አእምሮ - Home of encyclopedic Biblical exegesis" እንደሆነች ያሳዩን ናቸው።

ወንጌላዊው ሉቃስ ያስተዋወቀን ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፡ የንባብ ልምዱና ለነፍሱ ድኅነት የሠጠው ትኩረት እንዴት ነበር? ለወሬ ሳይሆን ለወንጌል የማያርፉ የፊሊጶስ እግሮች እንዴት ሮጡ? ጃንደረባው በአጋእዛዊት ቤተ ክርስቲያን የነበረው ሚና፡ ዓለማዊ ሞያውና ያነበበው መጽሐፍ ምን ነበር የሚለውን ለመፈተሽ የሚገፋፋንም፡ የተጻፈ "ሁሉ" የሚለው ወንጌልን እንደ ነፋስ የሚሮጥባት፥ የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ቃል ነው።

ቅዱሳት መጻሕፍት እንዴት መተርጐም አለባቸው በሚለው ሐተታ፡ ቤተ ክርስቲያናችንን ሐዋርያዊት የሚያስብላት አካሄድ፡ ‹ምእመናን ቀደምት አበውን ትርጓሜ ፡ እንደ አስኬማ በገዛ ራሳችው ደፍተው፡ በእሱ ጥላነት ከሚባላ መናፍቃዊ ዝናም መጠበቅ አለባቸው›፡ የሚለው አካሄድ ነው።

በ‹ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ› መጽሐፍ ላይ ጸሐፊው፡ “የአበውን የትርጓሜ አስኬማ›› በራሱ ላይ በማድረግ፡ አንድ ዓይንና ጆሮን ጨምሮልናል። “ሁሉ“ የሚለው የሐዋርያ ቃል በማስተዋል የተዘጋጀ፡ መልካም ሽታ ያለው የመጽሐፍ መአድ ነው ቢባል መጋነን አይደለም። ይህንን መጽሐፉን፡ አንብቤ ከጨርስሁ በኋላ በምን ታያለህ በምንስ ትሰማለህ የሚለኝ ካለ ‹በዐይኔና በልቤ

አያለሁ፡ በጆሮዬና በልቤ እሰማለሁ› ብየ እመሰክራለሁ። እናንተ አንብባችሁ ምን ትሉ ይሆን?

የቅዱሳን አባቶችን ሕይወት ስንመረምር፡ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ፡ አንድ የዕለት ተግባራቸው ነበር። ዓለም አሁን ካለችበት ጸረ ክርስቲያናዊ ሐሳቦች ደህና በነበረችበት ጊዜ እንኳን በጆሮ መልእክተኝነት ወደ አእምሮ ከሚደርሰው ሕይወት ከማይሰጥ የሚረብሽ ወሬ፡ አእምራቸው ለማንጻት ቅዱሳን መጻሕፍቶችን ማንበብ፡ ቅድሚያ የሚሰጡት ኑሯቸው ነበረ፡፡ አሁንስ? አሁን ባለንበት ጊዜ፡ ሥጋንና ነፍስን የሚያነጻ ንባብ፡ ምን ያህል አስፈላጊ ይሆን?!

ከበረሐ አባቶች አንዱ፡ "ነቢያት ቅዱሳት መጻሕፍት ሰበሰቡ። አባቶች ደግሞ፡ ገለበጡት። ከእነርሱ በኋላ የመጡት አባቶች እነዚያን ቃላት በልባቸው ያዙ። አሁን ያለው ትውልድና ልጆቻቸው ደግሞ፡ እንደ ማይጠቅም ዕቃ የመጽሐፍ መደርደሪያ ላይ አስቀመጡት፡" እንዳለው መጻሕፍትን በተለይም መንፈሳውያን መጻሕፍት ማንበብ እንደ ዐቀበት መውጣት የሚያዩ ትውልድ፡ ላይ ደርሰናል፡፡ ይኼንን የተከሸነ መጽሐፍ ግን በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ አነጋገር "ማንበብ የሚችል፡ ለማንበብ የሚከለክለው ስለሌለ መመገብ ፤ በእጁ ሊበላ፡ የማይችል ሰው ደግሞ አጉርሱት"

ብሎ፡ በሌሎች እጅ ከዚህ ጣፋጭ መንፈሳዊ ምግብ እንዲበላ፡ ምኞቱ ታላቅ ነው።

ተመራማሪዎች ቅዱስ ሙሴ ጸሊምን፡ የማይጋፉ ቅዱስ (non-violent Saint) ብለው እንደ ሚጠሩት፡ የእርሱ ፍኖት በመከተል፡ የማይጋፋ የማስተማር ዘዴን የሚከተለው (non- violent preacher) መምህር ሄኖክ ኃይሌ በቀደሙ መጻሕፍቶቹ እንደ ተገለጠው የሚከተለው የአጻጻፍ ዘዴ፥ በበለጠ በማመሥጠር፥ በጠባብ ውስጥ ሰፊ፥ በትንሽ ውስጥ ብዙ እንዳለ እየደጋገመ የሚያሳይ ሌሎችም ሊከተሉት የሚገባ የአጻጻፍ ዘዴ ነው።

ጸሐፊው፡ "እውነት እሄ ብቻ ነው" ብሎ፡ በእንግሊዘኛ የተጻፉት መጻሕፍትን መጥቀስ እንደ ሥልጣኔና ዕድገት በምታይበት ዘመን፡ በእነዚያ መጻሕፍቶች አልታጠረም። ወይም ደግሞ "ግእዝ ብቻ፡ አማርኛ ብቻ" ብሎም በትንሹ አጥር አልታጠረም። አንዱ ያለውን ሌላው አስፍቶ ወይም ተቃውሞ እንዳይሆን በማለት፡ በእቻ ምሁራን የተስተያየ ምርምር (peer reviewed research) አድርጎ ዳስሶታል። ይሄ አካሔድ፡ ደግሞ የቀደሞ አባቶች፡ የሀገራችን ትምህርት ተምረናልና ይበቃናል ሳይሉ፡ በየሀገሩ ውራት በሚወስድ ጉዞ ርሃብና ብርድ ሳይሉ፡ ተድላ ሳይወዱ፡ በተደላደለ ወንበር ሳይሆን በአባቶች እግር ሥር ላይ ቁጭ ብለው፡ በአንካሳ ቋንቋ

ሳይሆን በጥልቅ ወደ ትርጉም በመግባት፡ ሁሉን በአቅሌስያዊ አስተርእዮ ለመዳሰስ ጥረዋል። ጸሐፊው፡ እንደ ሌሎቹ አለፍ አልፍ ብለው የሚታዩ ዘመን የወለዳቸው ሰባክያን፡ ይሄ "የኛ ብቻ" የሚል አጥር (fence) ፈንጥሶ በመውጣት የመጻሕፍት ቁፋሮ አድርጓል። "ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ" የዚህ ቁፋሮ ውጤት የሆነች፡ የጠራች ሉል ነች።

ንድፈ-ጽሑፉን ለማየት ‹ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ› የሚለውን መጽሐፍ በተቀበልኩ ግዜ፥ በፖለቲካ ዝንባሌ እንደተለከፈ ሰው፥ ገና ሳላነበው፥ ‹እንዲህ እንዲህ ሊል ይሆናል› ብዬ ቀድሜ ገምቼ ነበር፡፡ ወደ መጻፉ እርሻ ዘልየ በገባሁበት ጊዜ ግን፥ የቃረምኩት መንፈሳዊ ትምህርት፥ ከመጠን በላይ በስሎ፥ አጠገበኝ። ከማንበቤ በፊት ለነበረኝ የተሳሳተ ድምዳሜ ሌላ መንፈሳዊ ዓይን ስላሳየኝ ደግሞ አድናቆትና እፍረትም ተሰማኝ፥ አድናቆቴ ለጸሐፊው ነው፥ እፍረቴ ደግሞ በዚያ ፖለቲካ ባወረው ልቤ ነው።

ንጉሥ ሰሎሞን በመጽሓፈ ምሳሌው፥ "ለጠገበ ማር አይጥመውምም፤ ለተራበ ግን እሬት እንኳ ይጣፍጠዋል"። (ምሳ. ፳፯፥፯) እንዳለ። ለእኛ እንደዚህ መንፈሳዊ ምግብ ተርበን ያለነው፥ እንደዚህ አድርገው የሚያስተምሩን መምህራንን ማን በሰጠን?! በላዔ መጻሕፍት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፥ በንባብ ዝንባሌ ላይ በተናገረበት

ጽሑፉ ‹መንፈሳዊ መጻሕፍት ማንበብ መነኩሴ አያደርግም፥ እውነተኛ ክርስቲያን ግን ያደርጋልና ስለዚህም በዓለማዊው ሥራ ለተጠመዳችሁስ ምንኛ ማንበብ ባስፈለጋችሁ?› ይላል። ስለዚህ የዚህችን መጽሐፍ አንባቢዎች፥ “ስለ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ማንበብ፥ ኢትዮጵያዊ አያደርጋችሁም፥ እውነተኛ ክርስቲያን ግን ያደርጋችኋል›› እላለሁ።

በረከት ዑቅባጽዮን
ጸሐፊና ተርጓሚ

# ፩፡
# ጃንደረባ

## የጃንደረባ ትርጉም

ጃንደረባ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ከአርባ ጊዜ በላይ የተጻፈ ቃል ነው፡፡ ከብሉይ እስከ ሐዲስ በሁሉም ክፍለ ዘመናት ታሪኮች ውስጥ ‹ጃንደረባዎች› የነበሩ ሲሆን ስያሜው ወንዶችን ብቻ የሚመለከት ነበር፡፡ ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ ‹ጃንደረባ› የሚለውን ቃል የሚጠቀምበት አገባብ እንደየታሪኩ ሁኔታ የተለያየ ነበር፡፡ በአጠቃላይ በቃል በቃልም ሆነ በምሥጢራዊው የቤተ ክርስቲያናችን ትርጓሜ ጃንደረባ የሚለው ቃል ፍቺዎች በሚከተሉት አከፋፈሎች ማየት እንችላለን፡፡

## ጃንደረባ - ሕጽው

ጃንደረባ ማለት በግእዙ ‹ሕጽው› የሚል ሲሆን ቀጥተኛ ትርጉሙ ‹የተሰለበ ፤ ስልብ ፤ ኅማዳ› ሲል ኅጽወት ደግሞ ‹መስለብ› የሚል ትርጉም ተሠጥቶታል፡፡ ይህ ፍቺ ደግሞ በግእዙ

ብቻ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈባቸው ቋንቋዎችም ተመሳሳይ ትርጉም የሚሠጥ ቃል ነው፡፡[1]

ጠቢቡ ሲራክ ‹‹ጃንደረባ ፈቃዱ ላይፈጸምለት ቆንጆ ልጅን እንደሚወድ እንዲሁ ፍርድን ያደላ ዘንድ የሚወድ አለ›› በማለት የጃንደረባን ሩካቤ መፈጸም አለመቻል ለማይሳካ ከንቱ ምኞት ምሳሌ አድርጎ አስቀምጦታል፡፡ (ሲራ. ፳፥፬) ቀጰዶቅያዊው ቅዱስ ባስልዮስም በአንድ መልእክቱ ላይ ጃንደረባን ከሚደርስበት ሥነ ልቦናዊ መገለል ጋር ሲገልጸው ‹‹በሴቶች መካከል ያለ ወንድ ! በወንዶች መካከል ያለ ሴት›› ብሎታል፡፡[2] በእኛም ሀገር ‹ጃንደረባ በጌታው ብልት ይፎክራል› የሚለው ሥነ ቃል ‹ጃንደረባ› የሚለው ቃል ለምን እንደሚውል ማሳያ ነው፡፡

በጥንት ዘመን በእስራኤልም ሆነ በአሕዛብ ባሕል ውስጥ በነበረው የባሪያ ንግድ ሥርዓት ጃንደረቦችን በንብረትነት መያዝ

---

[1] በግሪኩ εὐνοῦχος (ዩኒኮስ) በዕብራይስጥ סריס (ሳሪስ) የሚል ሲሆን በሁለቱም አገባብ ብልቱ የተሰለበን ሰው ለመግለጽ የሚውል ቃል ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ጃንደረባውን ባኮስ እና አቤላክ በሚል ስም የሚጠሩት ሲሆን ባኮስ የሚለው ከግሪኩ ‹ዩኒኮስ› ጋር የሚገናዘብ ይመስላል የሚል አስተያየታቸውን የሚሠጡ የቋንቋ ሊቃውንት አሉ፡፡ የምሥራቅ ኦርቶዶክሳዊያን ጸሐፍት ደግሞ ጥቁሩ ስምያን ይሉታል፡፡ ዛጋ ዛበ የሚባል ኢትዮጵያዊ ሰው ነገረኝ ከሚል ሰው የሰማ ፖርቹጋላዊ ጸሐፊ ደግሞ ጃንደረባውን ‹ኢንዲች› በሚል ስም ጠርቶታል፡፡

[2] ‘Men among women, and women among men’ St. Basil the great, Epistle to Simplicias 1

የተለመደ ድርጊት ነበር፡፡[3] ስልብ የሆኑት ሰዎችም የሆኑበት መንገድ የተለያየ ነበር፡፡ አንዳንዶች በተፈጥሯቸው እንደዚያ ሆነው የሚወለዱ አሉ፡፡ ሁለተኞቹ ደግሞ ‹ጥበብን ይገልጣል ፤ በፍልስፍና ያራቅቃል› ወዘተ በሚል እንግዳ እምነት ራሳቸውን ፈቅደው የሰለቡ ሰዎች ናቸው፡፡ ሦስተኞቹ ደግሞ ሰዎች በጭካኔ የሰለቧቸው ናቸው፡፡

በጭካኔ የመስለብ ድርጊትን የሚፈጽሙ ሰዎችም አፈጻጸማቸው ለየቅል ነበር፡፡ አንዳንዶቹ የማረኳቸውን ወንዶች ብልት መስለብ እንደ ጀግንነት ምልክት አድርጎ የሚያምን ባሕል ያላቸው ስለሆኑ ድርጊቱን በስለት ይፈጽማሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ባሪያዎቻቸው እንዳይወልዱ በማድረግ የዕድሜ ልክ ባሪያ አድርጎ ለማስቀረት ወይም በውድ ዋጋ የሚሸጥ ባሪያ ለማድረግም የሚጠቀሙበት ስልት ነበር፡፡ ይህንን ለማድረግ ወይ በስለት ቆርጦ በመጣል አለዚያም በዕድሜ ሕፃን የሆኑትን ባሪያዎች ያለ ስለት የዘር ፍሬያቸው በመድኃኒት ወይም ለረዥም ጊዜ በእጅ በማሚሚት እንዲሚሽሽ በማድረግ የሚሰልቧቸው ናቸው፡፡

---

[3] የታሪክ ጸሐፊው ሄሮዶተስ በ440 BC በጻፈው መጽሐፍ ምርኮኛ የሆኑ ሁሉ ይሰለቡ እንደነበረ ጽፎአል:: /The Histories Herodotus, Trans. George Rawlinson pp. 54,177, 197, 218/

ጃንደረቦች በተለይ በቤተ መንግሥት አካባቢ እጅግ ተፈላጊ አገልጋዮች ናቸው፡፡ ብዙ ሚስቶችን በማግባትና ብዙ ዕቁባቶችን በማስቀመጥ የዘሙት ባሕል የነበራቸው ጥንታዊያን ነገሥታት ለሚስቶቻቸው በአገልጋይነት የሚመድቡት ስልብ ጃንደረባን ነበር፡፡ ይህንን የሚያደርጉት በአካሉ ጉድለት ምክንያት ከሚስቶቻቸው ጋር ሊወስልት የማይችል በመሆኑ ታማኝ ስለሚሆን ነው፡፡ የጃንደረባው ተጨማሪ ሥራም የንጉሡ ሚስቶች ከሌላ ሰው ወልደው የንጉሡ አልጋ ወራሽ ያልሆነው እንዳይነግሥ ለመጠንቀቅ ነበር፡፡

‹‹የአስቴር ተራ በደረሰ ጊዜ የሴቶች ጠባቂው የንጉሡ ጃንደረባ ሄጌ ከሚለው በቀር ማንንም አልፈለገችም ነበር›› (አስቴ. ፪፥፲፭)

‹‹አስቴርም ያገለግላት ዘንድ ንጉሡ ያቆመውን አከራትዮስን ጠራች ፤ እርሱም ከጃንደረቦች አንዱ ነበረ›› (አስቴ. ፬፥፭)

የሚሉት ጥቅሶች ይህንን እውነታ ያስረዳሉ፡፡

## ጃንደረባ ማለት ባለ ሥልጣን

መጽሐፍ ቅዱስ ‹ጃንደረባ› የሚለውን ቃል የተጠቀመበት ሌላው አገባብ ሹመኛ ፤ ባለ ሥልጣን የሚል ትርጉም ያለው ነው፡፡ ‹ጃን› እና ‹ደረባ› የሚሉት የአማርኛ ቃላት ለዚህ ትንታኔ የበለጠ

የቀረቡ ናቸው፡፡ ‹ጃን› የሚለው ቃል ‹ንጉሠ› የሚል ትርጉም አለው፡፡ **ጃን፡ሆይ** (ንጉሥ ሆይ) **ጃን፡ሜዳ** (የንጉሥ ሜዳ) **ጃን፡ተከል** (ንጉሥ የተከሉት) ወዘተርፈ የሚሉት አገላለጾች ይህንን ያሳያሉ፡፡ ‹ደረባ› የሚለው ቃል ደግሞ አቻነትን የሚያሳይ ሲሆን ‹ባልደረባ› ቢል ‹በሥራ ተባባሪ ደባል› ማለት እንደሆነ ጃንደረባም የንጉሥ ቀራቢ ሹመኛ ባለ ሥልጣን መሆኑን የሚያስረዳ ቃል ነው፡፡ [4]

ዮሴፍ በወንድሞቹ እጅ ወደ ግብፅ በተሸጠ ጊዜ በባርነት የቆየበት ቤት ባለቤት ጲጥፋራ ‹‹የፈርዖን ጃንደረባ የዘበኞቹም አለቃ›› ነበረ፡፡ (ዘፍ. ፴፱፥፩) በዚህ አገባብ አዛገፉ ጲጥፋራ ጃንደረባ የተባለው እንደ ባለ ሥልጣን ሆኖ እንጂ ከላይ ያየነው አካላዊ ጉድለት ቢኖርበት ኖሮ ትዳር መሥርቶ ሚስት አግብቶ መኖሩ ትርጉም አይሰጥም ነበር፡፡ [5]

---

[4] ንቡረ ዕድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ ፣ ቃለ ዐዋድ ፲፮ ፤ ፳፻፱ ዓ.ም. ፤ በሌላ በኩል ጃን ማለት ዝሆን እንደሆነ እና ዐፄ ሠርፀ ድንግል ፈላሾች ዝሆን ለማባረር ‹ጃንሆይ ጃንሆይ› ሲሉ ሰምተው በዚህ ስም ጥሩኝ እንዳሉ የሚገልጽ ታሪክም አለ፡፡ (ተክለ ጻድቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ቴዎድሮስ ገጽ 219)

[5] የጲጥፋራ ጃንደረባነት የስልብነት ከሆነ የጲጥፋራ ሚስት በዮሴፍ ላይ ያሳየችው ዝንባሌ ምክንያታዊ በሆነ ነበር፡፡ ሆኖም በታሪኩ ላይ የተጻፈው ምክንያት የዮሴፍ ውበት ብቻ ሲሆን ‹ከእኔ ጋር ተኛ› ከማለትዋ ውጪ ሌላ ያቀረበችው ምክንያት አልነበረም፡፡

በትንቢተ ዳንኤል ላይ ሠለስቱ ደቂቅንና ዳንኤልን በናቡከደነፆር ቤተ መንግሥት ጥሬ ቆርጥመው እንዲያድሩ የፈተነና የፈቀደላቸው የጃንደረቦች አለቃም እንዲሁ ባለ ሥልጣን ለመሆኑ እንጂ አካላዊ ጉድለት እንዳለበት የሚያሳይ ምንም ማስረጃ የለም፡፡ (ዳን. ፩፥፯) በተመሳሳይም ነቢዩ ኤርምያስ በጉድጓድ በተጣለ ጊዜ ሳይሞት ያስወጣው የብሉይ ኪዳኑ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ አቤሜሌክም ተሰሚነት ያለው የንጉሥ የቅርብ ባለሟል ከመሆኑ ባሻገር ከላይ የጠቀስናቸው አይነት የዐቃቤ አንስትነት ሥራ የሚሠሩ ስልብ ጃንደረቦች ዓይነት ድርሻ አልነበረውም፡፡ (ኤር. ፴፰፥፯)

በዚህ መሠረት ጃንደረቦች በቤተ መንግሥት ከፍተኛ ሥልጣን ያላቸው ፤ በንጉሡ ዘበኞች ላይ በአለቅነት የተሾሙ ፤ የንጉሡ የቅርብ አማካሪዎችና በገንዘቡ ላይ የማዘዝ ሥልጣን ያላቸው ሹማምንትም ሊጠሩበት የሚችሉት ስያሜ ነው፡፡

## ጃንደረባ በወንጌል

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ጋብቻ ሕግና ፍቺ ምን ያክል ከፉ ሥራ እንደሆነ አስተምሮ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ የነገሩን ጥብቅነት ተመልክተው ‹‹የባልና ሚስት ሥርዓት እንዲህ ከሆነ መጋባት አይጠቅምም›› አሉት፡፡ ‹‹እርሱ ግን

፡- ይህ ነገር ለተሠጣቸው ነው እንጂ ለሁሉም አይደለም ፤ በእናት ማኅፀን ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ ፤ ሰውም የሰለባቸው ጃንደረቦች አሉ ፤ ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ፡፡ ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው›› አላቸው፡፡ (ማቴ. ፲፱፥፲፪)

በቤተ ክርስቲያናችን አበው ትርጓሜ ጌታችን ስለ ሦስት ዓይነት ጃንደረባነት ያስተማረው ትምህርት ከላይ ያየናቸውን ዓይነት የሥጋዊ አካል ጉድለትን የሚመለከት አይደለም፡፡ ምክንያቱም ጌታችን ጉዳዩን ያነሣው ሐዋርያት ‹‹መጋባት አይጠቅምም›› ባሉት ጊዜ በመሆኑና ነገሩን ሲጀምረውም ‹‹ይህ ለተሠጣቸው ነው እንጂ ለሁሉም አይደለም›› ብሎ መናገሩ ነው፡፡

‹ለተሠጣቸው ነው› የሚለው ቃል ስለ አካል ጉድለት ቢሆን ኖሮ ሰው በጭካኔ የሰለባቸው ሰዎች እንዴት ‹ተሠጥቷቸው ነው›› ሊባል ይችላል? ለመንግሥተ ሰማያት ብለው የሚለውስ እንዴት ሰው ራሱን ስለሰለበ መንግሥተ ሰማያትን ማግኘት ይችላል? መንግሥተ ሰማያትስ አካል በማጉደል ልትገኝ ትችላለችን? የሚል ጥያቄ ባስነሣ ነበር፡፡ ጌታችን የተናገረው ግን ስለ ሥጋ ጃንደረብነት ሳይሆን ስለ መንፈሳዊው ጃንደረብነት ስለ ድንግልና ሕይወት ነበር፡፡

ትርጓሜ ወንጌል ዘግእዝ ይህንን ሲተረጉም ‹‹ሕፅዋን: እምከርሠ: እሞሙ: እሉ: እሙንቱ: እለ: አንጽሖሙ: እግዚአብሔር: እምርስሐተ: ዓለም: እምከርሠ: አማቲሆሙ: በከመ: ይቤሉ: ለኤርምያስ: እምከርሠ: እምከ: ቀደስኩከ: ወአንጽሖሙ: እምኵሉ: ዘይትቃወሞ: ለሥጋ›› እንዲል ‹‹ከእናታቸው ማኅፀን ጃንደረቦች ያላቸው እግዚአብሔር ከእናቶቻቸው ማኅፀን ጀምሮ ከዚህ ዓለም መተዳደፍ ያነጻቸው ናቸው:: ለኤርምያስ ከእናትህ ሆድ ጀምሮ ቀደስሁህ እንዳለው ሥጋን ከሚቃወመው ነገር ሁሉ አንጽቷቸዋል››[6]

እንደ ነቢዩ ኤርምያስ ‹‹ከሆድ ሳልሠራህ ቀድሼሃለሁ›› የተባሉ ፣ በቀጥታ በአምላካዊ መገለጥ ፣ በራእይ ፣ በሕልም ወዘተ ወደ ድንግልና ሕይወት የገቡ እጅግ ጥቂት ቅዱሳን አሉ:: መጥምቁ ዮሐንስም ገና በእናቱ ማኅፀን ሳለ ምናኔው የተነገረለት ለደንግልና ሕይወት መንፈሳዊ ጃንደረባ ሆኖ የተወለደ ነበር:: (ሉቃ. ፩፥፲፭) ይህ ዓይነት ከልጅነት አንሥቶ ወደ ድንግልና ሕይወት የመጠራት ዕድል የገጠማቸው ቅዱሳን ታሪክ በሰፊው በየገድላቱ የተጻፈ ሲሆን ይህ ግን ‹የከስንት አንዴ› (exceptional) የሆነ እንጂ የመነኑ ሰዎች ሁሉ ታሪክ አይደለም::

[6] ግእዝ በግእዝ ትርጓሜ ብራና ዘመርጡለ ማርያም

ሁለተኛው ደግሞ ሰው የሰለባቸው የተባሉት ጃንደረቦች ናቸው፡፡ ‹መሰለብ ስለ ሥጋዊ አካል ካልሆነ ስለ ምንድር ነው?› ቢባል ኤልያስ ያስተማረው ትምህርት ኤልሳዕን ሀብቱን ትቶ እንዲከተል እንዳደረገው (፩ነገሥ.፲፱፥፲፱) ጌታ ያስተማረው ትምህርት እነዮሐንስን ሁሉን ትተው እንዲከተሉት እንዳደረጋቸው (ማቴ.፬፥፳) በመንፈሳዊ ትምህርት ተመሥጠው ፤ እንደ ቅዱስ እንጦንስ ወንጌል (ማቴ. ፲፱፥፳፩) ሲነበብ ሰምተው የመነኑ በሰዎች መንፈሳዊ ተግሣጽ የተሰለቡ ጃንደረቦች ብዙዎች ናቸው፡፡[7] እነዚህ ጃንደረቦች የተሰለቡትም በሰይፍ ሳይሆን ‹‹ሁለት አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ በተሳለው ነፍስንና መንፈስን ጅማትንና ቅልጥምን እስኪለይ ድረስ በሚወጋው›› በእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ (ዕብ. ፬፥፲፪)

‹‹ወቦ፡ እለ ሐፀውዎሙ፡ ሰብእ፡ ዘይቤ፡ አበው፡ መንፈሳውያን፡ ሶበ፡ ይጌሥፅዎሙ፡ ለመሃይምናን፡ በትምህርተ፡ መጻሕፍት፡ እስመ፡ ፍቅረ፡ እግዚአብሔር፡ ይበውእ፡ ውስተ፡ ልቦሙ፡ ለመሃይምናን፡ ወይመትር፡ እምአልባቢሆሙ፡ ከዊኖ፡ መጥባሕት፡ ኵሉ፡ ፍትወተ፡ ሥጋ፡ እኩየ፡ ዘይወስድ፡ ኀበ፡ ዓለም፡ መስሐቲት፡፡፡ ወያሚኖሙ፡ ኵሉ፡ ግብር፡ ኅድግስ፡ ከመ፡ ኢይዘምዉ፡ ባሕቲቱ፡ እስከ፡ አሐተኒ፡ ብእሲት፡ ዘሕግ፡

[7] Life of St.Anthony by St. Athanasius. p. 9 , Coptic synaxarium p. 193, month of tubah, Sinksar Jan. 22, geez. p. 431 , Mahbere Hawaryat.

የኃድጉ፡ እስመ፡ ፍቅረ፡ ክርስቶስ፡ ኀበ፡ ውዑደኒ፡ ማይ፡ ውእቱ፡ ዘያጠፍእ፡ወበኀበ፡ቁረርኒ፡ሊብ፡እሳት፡ውእቱ፡ዘያውእዮ›

‹‹ሰው የሰለባቸው ጃንደረቦች አሉ ያላቸው ሰው የተባሉት ምእመናንን በ[ቅዱሳት] መጻሕፍት ትምህርት የሚገሥጹአቸው መንፈሳውያን አባቶች ናቸው:: የእግዚአብሔር ፍቅር ወደ ምእመናን ልባቸው ገብቶ ወደ አሳችዋ ዓለም የሚወስደውን የሥጋ ክፉ ምኞት ሰይፍ ሆኖ ይቆርጠዋል:: ሁሉንም ሥራ እንዲንቁ ያደርጋቸዋል:: ዝሙትን እንዳያደርጉ ብቻ አይደለም:: በሕግ የሆነችውን አንዲት ሴት እንኳን እንዲተዉ ያደርጋቸዋል:: የክርስቶስ ፍቅር እንደ እሳት የነደደውን [ፍትወት] የሚያጠፋ ውኃ ነው ፤ [ለበጎ ሥራ] የቀዘቀዘውን ልብ ደግሞ የሚያሞቀው እሳት ነው››[8]

ሦስተኛው የጃንደረባ ዓይነት ስለ መንግሥተ ሰማያት ብለው ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች ናቸው:: እነዚህ ደግሞ ከማሕፀን ሳይመረጡ ፤ ሌላ የሚገፋፋቸው ሰው ሳይኖር በራሳቸው ልብ ተነሣሥተው ከዓለም የራቁ ፤ መስቀሉን የተሸከሙ ፤ እያሉ እንደሌሉ ለመሆንና ነፍስን ከምታጠፋው ከዚህ ዓለም ሥራ ርቀው ለክርስቶስ ለመኖር የወሰኑ መናንያን ናቸው:: ‹‹ወኀጽዋንሰ፡ እለ፡

[8] ትርጓሜ ወንጌል ግእዝ ዘመርጡለ ማርያም ፤ ወንጌል ዘማቴዎስ

ሐፀዊ፡ ርእሶሙ፡ በእንተ፡ መንግሥተ፡ ሰማያት፡ እስ፡ ርሑቃን፡ እምዓለም፡ ወጾሩ፡ መስቀሉ፡ ወእርሐቁ፡ ሕሊናሆሙ፡ እምግብረ፡ ዝንቱ፡ ዓለም፡ እንተ፡ ተሐጉል፡ ነፍሰተ፡ እጓለ፡ እመ፡ ሕያው›› እንዲል (ትርጓሜ ወንጌል ግእዝ ዘጉንዳጉንዲ)

ጌታችን ይህንን የድንግልና ሕይወት በሰፊው ካስተማረ በኋላ ‹‹ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው›› ብሎ ነበር፡፡ ይህን ማለቱ ‹‹ያለሴት በንጽሕና ይኖር ዘንድ የሚችል ቢኖር ይቀበለው›› ሲል ነበር፡፡ ይህም ‹‹እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ለራሱ የጸጋ ሥጦታ አለው አንዱ እንደዚህ ሁለተኛው እንደዚያ›› ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ የተናገረው ነው፡፡ (፩ቆሮ ፯፥፯) ‹‹ወዘሰ፡ ይክል፡ ጸዊረ፡ ሰይጹር፡ ዘእመሰ፡ ክሀለ፡ ተዓግሦ፡ ይንበር፡ በንጹሕ፡ ዘእንበለ፡ ብእሲት፡ በከመ፡ ይቤ፡ ጳውሎስ››[9]

ጌታችን ይህንን በድንግልና የመኖር ሕይወት እንዳስተማረ ሰዎች ‹‹እጁን እንዲጭንባቸውና እንዲጸልይባቸው ሕፃናትን ወደ ክርስቶስ አመጡለት›› በድንግልና ስለመኖር በሚያስተምርበት ቅጽበት ሕፃናትን ወደ እርሱ ማምጣታቸው ከጉዳዩ ጋር የሚቃረን የሚመስል ድርጊት ነበር፡፡ የጃንደረብነትን ሥጦታ ‹ለተሠጣቸው ነው› ብሎ ሲናገር የጋብቻ ሥጦታ የሆኑትን ልጆች በማቅረብ ድምፅ አልባ ጥያቄ አቀረቡ፡፡ ደቀመዛሙርቱ ይህንን ያረጉትን ሰዎች

[9] ትርጓሜ ወንጌል ዘግእዝ ዘሐይቅ እስጢፋኖስ ፤ ወንጌል ዘማቴዎስ

ገሥጹአቸው፡፡ ይህም ‹‹አንደኛ ሕፃናት ረባሾች ናቸውና በጨዋታቸው ምክንያት ትምህርቱን እንዳያጠፉ ነው፡፡ ሁለተኛው ግን በክርስቶስ ዘንድ ብዙ ደናግላንና መናንያን አሉና ሕፃናትን ባዩ ጊዜ ልባቸው እንዳይጠራጠር ለማድረግ ሐዋርያት ከለከሏቸው›› (ወዘከልእምሙሰ፡ ሐዋርያት፡ ከመ፡ ኢይባኡ፡ ኀበ፡ እግዚእ፡ በእንተ፡ ክልኤ፡ ግብር፡ ፩ሰ፡ ከመ፡ ኢያማስኑ፡ ትምህርተ፡ በተላህዮቶሙ፡እስመ፡ሕፃናት፡ህውካን፡እሙንቱ፡፡ወካልዑኒ፡ እስመ፡ ሀለዉ፡ በኀበ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ደናግል፡ ብዙኃን፡ ወመናንያን፡፡፡ ሶበ፡ ርእዩምሙ፡ ለሕፃናት፡ ከመ፡ ኢይናፍቅ፡ አልባቢሆሙ፡ወበእንተዝ፡ከልእምሙ)[10]

ይህም እንደ ሥርዓት ሆኖ በፈቃዳቸው የጃንደረባነትን ሕይወት በሚኖሩ መነኮሳትና ገዳማዊያን ዘንድ ሕፃናት እንዳይቆዩ ይከለከላል፡፡ በቤተ ክርስቲያን ታሪክም ሕፃኑ ዘካርያስ በመባል የሚታወቀው ጻድቅ አባቱን ተከትሎ ወደ ገዳም በሔደ ጊዜ ‹‹እንዲህ ያለ ያማረ ሕፃን በገዳም አናቆይም›› በማለታቸው ወደ በረሃ ሔዶ ፊቱን በንፍር ውኃ እንዳበላሸና ‹‹ይህ ውበቴ ከዚህ የመነኮሳት ማኅበር ከለየኝ ከእግዚአብሔር መንግሥትም ሊለየኝ ይችላል›› እንዳለ፡፡ መነኮሳቱም ‹‹ትላንት እንደ ሰው መጣህ ዛሬ

---

10 ትርጓሜ ወንጌል ግእዝ በግእዝ ዘመርጡለ ማርያም

ግን እንደ እግዚአብሔር መልአክ መጣህ›› ብለው እንደመለሱለት በዜና አበው ተጽፎአል፡፡[11]

## ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች

ጌታችን ‹ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ› ያለው ቃል መንፈሳዊ ትርጓሜው ከላይ እንደተመለከትነው ነው፡፡ ሆኖም ራስን መስለብ የሚለውን ቃል በቃል ተረድተው ራሳቸውን ለመስለብ የተነሡ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተከስተው ነበር፡፡ እነዚህ ወገኖች ከዚህ ጥቅስ በተጨማሪ ‹‹ዓይን ብታሰናክልህ አውጥተህ ከአንተ ጣላት›› ‹‹የሚያውኳችሁ ይቆረጡ›› የሚሉትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶችም ከዚህ ጋር አያይዘው ይጠቅሳሉ፡፡ (ማቴ. ፲፰፥፱ ፤ ገላ. ፭፥፲፪)

በእነዚህ ሰዎች የተሳሳተ አረዳድ ዓይን ብታሰናክልህ አውጥተህ ጣላት ካለ በዝሙት የሚሰናከል ሰው ደግሞ ብልቱን በመቁረጥ በዝሙት ከመሰናከል ራሱን ያድናል የሚል ነው፡፡ በዚህም እንደ ጫማ ሰፊው ስምዖን ያሉ ሕይወትና ቅድስና እንጂ እውቀት ያልነበራቸው ቅዱሳንም አድርገውት አልፈዋል፡፡

---

[11] Coptic Synaxarium pp.50-51 ፡ ስንክሳር ጥቅምት 13 ዘማኅበረ ሐዋርያት አሥመራ ገጽ 123-125

‹የሚያውኳችሁ ይቆረጡ› የሚለውንም በዝሙት እንድንታወክ የሚያደርገንን አካል መቁረጥ ይገባናል የሚለውን ያስረዳልናል ብለው ጠቅሰውታል፡፡

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ይህን መልእክት በተረጎመበት ሥፍራ እንዲህ ሲል ይመልስላቸዋል ፡- ‹‹ሰዎች ምኞት በዓይን ይገባል ብለው ዓይናቸውን ሊያወጡ አይገባቸውም ፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ሊወቀስ የሚገባው ዓይናችን ወይንም የትኛውም አካል አይደለም ፤ እንዲህ የምትል ከሆነ ስለ ክፉ ንግግርህ ምላስህን ፤ ስለ ስርቆትህ እጅህን ፤ ወደ ክፉ ስለመሔድህ እግርህን ለምን አትቆርጥም? በአጭሩ ራስህን ልትገድል ነውን?›› በማለት ይሞግታል፡፡[12]

ራስን መስለብ ሲነሣ ተደጋግሞ የሚነሣው ባለ አሳዛኝ ፍጻሜው የእስክንድርያው ትምህርት ቤት ቀደምት ሊቃውንት አንዱ የነበረው ኦሪገን ነው፡፡ ኦሪገን (ኦርጌንስ) በጉባኤ የተወገዘ ፤ ክህደቱ የታወቀ የተሠፈረ መናፍቅ ቢሆንም የሕይወት ታሪኩ ግን በበጎም ሆነ በክፉ ገጽታው እጅግ ማስተማሪያ ሊሆን የሚችል አሳዛኝ ታሪክ ነው፡፡ ኦሪገን የዕውቀት ማዕበል የቀለም ስረገላ ጥሎት

[12] St. John Chrysostom Homily On the episte to Galatians, Philip Scaff, kindle Version

ባስተማራቸው የስኅተት ትምህርቶቹ መናፍቅ ተብሎ ከዘመናት በኋላ ከቤተ ክርስቲያን በውግዘት የተለየ ቢሆንም ይህ ሊቅ ለዘመነ ሐዋርያት እጅግ የቀረበ በመሆኑ ፣ ከአይሁድ ረበናት ጋር እና ከግኖስቲኮች ጋር ለክርስትና ወግኖ ከፍተኛ የዕቅበተ እምነት ተጋድሎ ያደረገ ሰው ነበር፡፡

እንዲሁም ከመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና አወሳሰን ጀምሮ እስከ ቤተ ክርስቲያናችን የትርጓሜ መጻሕፍት ድረስ በፍጹም ቸል ሊባል የማይችል መሠረታዊ አሻራውን ያሳረፈ በመሆኑ በእርሱ ዘመን በኋላ በተነሡ እንደ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራት ባሉ ቅዱሳን አባቶች የተመሰከረለት ፣ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ መለኮት መጻሕፍትምና የምርምር ሥራዎች ፣ በምሥራቃውያንም ሆነ በምዕራባዊያን እንደ ቅዱስም ባይሆን እንደ ሊቅ መጠቀሱ የግድ የሆነለት ሰው ነው፡፡

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊው አውሳብዮስ እንደገለጸው ከልጅነቱ ጀምሮ አባቱ በተኛበት ደረቱን እስኪሳለመው ድረስ በቅዱሳት መጻሕፍት ዕውቀት የተሞላ ሆኖ ያደገ ነበር፡፡[13] በወጣትነቱ በቤተ ክርስቲያን ወንጌልን በሚያስተምርበት ጊዜ እጅግ

[13] Eusabius, Ecclecastical History, 6:2.2

ተወዳጅና ተደማጭ የነበረ ሲሆን በትምህርቱም ብዙ ቅዱሳንን እና እስከ ሰማዕትነት የደረሱ ብዙ አዳዲስ አማንያንን አፍርቶ ነበር፡፡

ወጣቱ መምህር በምእመናን ዘንድ በትምህርቱ እጅግ ከመወደዱ የተነሣ አቻዎቹ ከሚሆኑ አንዳንድ መምህራን ቅናትና ምቀኝነትን ፣ ከመናፍቃን ደግሞ ጥላቻን ያዘሉ ትችቶች ሲዘንቡበት ፣ ከአድናቂዎቹ ደግሞ ለፈተና የሚዳርግ አላስፈላጊ ሙገሳ ይወርድበት ጀመር፡፡ ራሱም ስለዚህ ጉዳይ በኋላ በትምህርቱ እንዲህ ብሎ ነበር፡-

‹‹መጥምቁ ዮሐንስን ሕዝብ ሁሉ ያደንቁትና ይወዱት ነበር፡ ፡ በእርግጥም መጥምቁ ዮሐንስ ሕይወቱ ከሰዎች እጅግ የተለየ ነበርና በሰዎች ሁሉ ሊመሰገን የሚገባው ነበረ፡፡ ሆኖም ‹አንተ ክርስቶስ ነህ ወይ?› ብለው ሲጠይቁት ፍቅራቸው ገደቡን አለፈ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም ‹‹ማንም ከሚያይ ከእኔም ከሚሰማ የምበልጥ አድርጎ እንዳይቆጥረኝ› ብሎ እስከሚናገር ድረስ ከገደብ ያለፈን ፍቅር ፈርቶ ነበር፡፡ (፪ቆሮ.፲፪፥፮) እኔም በእኛ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ባለው የተጋነነ ነገር እየተሰቃየሁ ነው፡፡ ብዙዎች ከሚገባኝ በላይ ይወዱኛል ፣ ጽሑፎቼንና ትምህርቶቼን ያደንቃሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ስብከቶቼን ይተቻሉ ፣ የእኔ ያልሆኑ ያልተናገርኳቸውን ሃሳቦች የእኔ እንደሆኑ አድርገው ይናገራሉ፡፡ ከሚገባው በላይ የሚወዱኝም ከሚገባው በላይ

የሚጠሉንም ሁለቱም የእውነትን ሕግ አልጠበቁም፡፡ ምክንያቱም አንዳንዶች በተጋነነ ፍቅር ላይ ሲሆኑ አንዳንዶች ደግሞ በተጋነነ ጥላቻ ላይ ናቸው፡፡ ስለዚህ ለፍቅራችን ገደብ ልናበጅለትና ወዳሻው እንዳይወስደን ልናደርገው ይገባል፡፡ መጽሐፍ ‹እጅግ ጻድቅ አትሁን እጅግም ጠቢብ አትሁን እንዳትጠፋ ይላልና (መክ. ፯፥፲፮)››[14]

‹ውዳሴ፡ ከንቱ፡ ይትለአካ፡ ለዝሙት› (ከንቱ ውዳሴ ለዝሙት ይላላክላታል) እንዲሉ አበው ይህ ከንቱ ውዳሴም ከውስጥም ሆነ ከውጪ የዝሙት ሃሳብ ፈተናን አስከተለ፡፡ በትምህርቱ ወቅት ቆነጃጂትም በጉባኤው ይታደሙ ነበር፡፡[15] በዚህም ምክንያት ወጣቱን ሰባኪ የዝሙት ፈተና ያስቸግረው ነበር፡፡ አንዳንድ ጸሐፍትም እንዳሉትም ባሎች በሚስቶቻቸው እንደይጠረጥሩት ይሰጋም ነበር፡፡ ገና በዐሥራ ስምንት ዓመቱ በእስክንድርያ ትምህርት ቤት መምህርነት የተቀመጠው ይህ ወጣት በንጽሕና ሕይወት ለመኖር የረኸም ጊዜ ዕቅድ ስለነበረው በአጭሩ ከመንገድ ተቀጭቶ እንዳይቀር ስጋት አደረበት፡፡

ስለዚህ መፍትሔ ያደረገው ‹ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች› የሚለውን ቃል ነበር፡፡ አሪገን በኋላ የተምሳሌታዊ ትርጓሜ ልውል

---

[14] Origen of Alexandria, In Joshua, Homily 9.3

[15] The School of Alexandria, Origen, Fr. Tadros Y.Malaty, page 22

(The prince of allegorical interpretation) ተብሎ የተጠራ ሊቅ መሆን የቻለ ቢሆንም በልጅነት አእምሮው ግን ይህንን ጥቅስ በነጠላው ተርጉሞ ራሱን ሰለበ፡፡ ኦሪገን ራሱን የሰለበው በአንዳንድ ምዕራባዊያን ሠዓሊዎች የእስክንድርያን ትምህርት ቤት ለማዋረድ በሚመስል መንገድ እንደሚሣለው በስለት ሳይሆን በነበረው የዕፅዋት ዕውቀት ተጠቅሞ በመድኃኒት ኃይለ ፍትወቱን አድክሟል የሚሉም አሉ፡፡[16]

ይህንን ድርጊት ከፈጸመ በኋላ በሒደት በድርጊቱ የተጸጸተ ሲሆን በወቅቱ በምሥጢር ለፓትርያርክ ድሜጥሮስ (189-231) ብቻ ነግሮ ይቅርታን አግኝቶ ነበር፡፡ (በኋላ አጋልጦታል) በዕውቀትና በዕድሜ ከበሰለ በኋላ የማቴዎስ ወንጌልን ሲተረጉም ‹ስለ መንግሥተ ሰማያት ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረባዎች አሉ› የሚለውን ቃል በተረጎመበት ሥፍራ :-

‹‹ፊደል ይገድላል መንፈስ ግን ሕይወትን ይሠጣል የሚለውን ቃል ልንጠቅስባቸው የሚገቡ የብሉይ ኪዳን ብቻ ሳይሆኑ የሐዲስ ኪዳንም ቃላት አሉ፡፡ በተለይም ለዚህ ቃል ‹ፊደል ይገድላል› የሚለው የሚሠራ ይመስለኛል›› ብሏል፡፡

---

16 Origen, The Early Church Fathers, Joseph W.Trigg,page 14 The Deans of The School of Alexandria, Origen, Fr.Tadros Y.Malaty, Epiphanious Heresi 64፣

አክሎም ይህንን አለ :- ‹‹እውነተኛ ንጽሕና በሰውነት አካል ላይ ጉዳት ማድረስ አይደለም ፤ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ሲሉ ስሜትን መግደል ነው እንጂ›› [17]

ከዚህ በኋላ ግን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በኒቅያ ጉባኤ ባደረገችው ጽድቀ ሃይማኖት የመጀመሪያ አንቀጽ ላይ ራስን መስለብን በጽኑ አውግዛለች:: ‹‹በሕመም ምክንያት የተሰለበ ካህን ቢኖር በክህነቱ ይቀጥላል:: ያልተካነም ቢሆን ይካናል:: ራሱን የሰለበ ሰው ግን ካህን ቢሆን ከክህነቱ ይሻር ፤ ምእመንም ቢሆን አይካን›› ‹‹በሰው እጅ ጃንደረባ የሆነ ወይንም በመከራ ወቅት በደረሰበት ጥቃት የተነካ የተሰለበ ሰው ወይንም በተፈጥሮ ጃንደረባ ሆኖ የተወለደ ሰው ብቁ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ እስከ ጵጵስና ድረስ ይሾም›› የሚሉ ውሳኔዎች ተወስነዋል::[18]

## ኢትዮጵያዊው ጃንደረባስ?

እነዚህን ሁሉ የጃንደረባ ትርጉሞች ስንመለከት መቼም የሕንደኬ መልእክተኛ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ምን ዓይነት ጃንደረባ ይሆን ማለታችን አይቀሬ ነው:: በእርግጥ ይህ ሰው ጃንደረባ

---

[17] Origen of Alexandria., On Matthew vol.15.1

[18] First canon of the Council of Nicea, cf Vol. I, pp. 529-532/ Apostolic canons xxiii/

የተባለው በስልብነት ነው? በምናኔ ነው? ወይንስ በባለ ሥልጣንነት? የሚለውን መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ በስልብነት ነው ለማለት የሚያስችል ምንም ዓይነት ማስረጃ የለም፡፡ ብዙ ምዕራባውያን ጸሐፊዎች የዚህ ጃንደረባ ታሪክ ዘመን ለሚያመጣቸው ጾታ ነክ ጥያቄዎችን ለመመለስ መነሻ ለማድረግ የሚጎትቱት ሲሆን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ከወንድና ሴት ጾታ በተለየ ያሉትን ወይም መሆን የፈለጉትንም ሌሎችንም ያለ ቅድመ ሁኔታ መቀበል አለባት ለማለትም የጃንደረባውን የጥምቀት ታሪክ እንደማስረጃ ሊጠቀሙት ይሞክራሉ፡፡[19]

ቤተ ክርስቲያን ‹ከሁሉም ዓይነት የሰበሰበች መረብ› እንደመሆንዋ በንስሓና ፈጣሪውን በመፈለግ በሕገ እግዚአብሔር ለመኖር ወስኖ እስከመጣ ድረስ የማትቀበለው ሰው የለም፡፡ (ማቴ. ፲፫፥፵፯) ‹ወደ እኔ የሚመጣውን ከቶ ከኔ አላወጣውም› ያለው ክርስቶስም እጆቹ ለሁሉ የተዘረጉ ናቸው፡፡ (ዮሐ. ፮፥፴፯) ሰዶምና ገሞራን እንኳን ባነሣበት ሥፍራ ከመራር ቃል ይልቅ ‹በእናንተ የተደረገው ተአምራት በሰዶም ተደርጎ ቢሆን እስከ ዛሬ በኖሩ ነበር› ብሎ መመለሳቸውን መሻቱን የሚያሳይ ቃል ተናግሯል፡፡ (ማቴ. ፲፥

[19] Queering the Ethiopian Eunuch, Strategies of Ambiguity in Acts, Sean D. Burke, Fortress Press, Minneapolies page 3-20


፳፫) ከዚህ አልፎ ግን የእግዚአብሔር ፍቅር ኃጢአተኛውን እንጂ ኃጢአቱን በመውደድ አይገለጽም፡፡ ያልሆነውን ታሪክም ለሚፈልጉት አጀንዳ ጠምዝዞ ያለማስረጃ ሆነ ብሎ መተረከም ደግሞ ተገቢ አይደለም፡፡

ኢትዮጵያዊን ጃንደረባ ‹ጃንደረብነቱ የስልብነት ነው› እንዳንል የሚከለክለን ትልቅ እውነታ ወደ ኢየሩሳሌም ሊሰግድ መሔዱ ነው፡፡ እንደሚታወቀው አንድ ሰው የአይሁድ እምነት ተከታይ ለመሆን ቢፈልግ የመጀመሪያው መሥፈርቱ ግዝረትን መፈጸም ነው፡፡ ጃንደረቦች ደግሞ ግዝረት ለመፈጸም የሚያስችል ሁኔታ የላቸውም፡፡ እንዲሁም በሕገ ኦሪት ‹‹ብልቱ የተቆረጠ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ›› የሚል ጠንካራ ሕግ ነበረ፡፡ (ዘዳ. ፳፫፥፩) በእዚህ መሠረት ይህ ሰው ‹ጃንደረባነቱ› የአካል ስልብነት ከሆነ ወደ ኢየሩሳሌም ገብቶ ለመስገድ ባልቻለ ነበር፡፡

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ስልብ ሆኖ ቢሆን ኖሮ ግን ያነብ የነበረው የኢሳይያስ መጽሐፍ መሆኑ ‹ጥሩ መጽሐፍ መረጠ› ያሰኛል፡፡ ምክንያቱም ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ለጃንደረቦች ተስፋ ሠጪ ቃል የሚገኝበት ብቸኛ መጽሐፍ ትንቢተ ኢሳይያስ ነበር፡፡ ‹‹ጃንደረባም እነሆ እኔ ደረቅ ዛፍ ነኝ አይበል ፤ እግዚአብሔርም ቃልኪዳኔን ስለሚጠብቁ ጃንደረቦች እንዲህ ይላል በቤቱና በቅጥሩ

ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የማይጠፋ የዘላለም ስምን እሠጣቸዋለሁ›› (ኢሳ. ፶፮፥፫–፭)

ብዙዎቹን ሊቃውንት የሚያስማማው የኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ‹ጃንደረብነት› ግን ‹ባለ ሥልጣን› የሚለው ትርጉም ነው፡ ፡ ‹‹ሕንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ በገንዘብዋ ሁሉ የሠለጠነ አንድ የኢትዮጵያ ሰው›› የሚለው አገላለጽ ‹ጃንደረባን› እንደ ሰውዬው ሹመት እንጂ እንደ ሰውዬው ማንነት አላስቀመጠውም፡፡ ስለዚህ ይህ ሰው በሕንደኬ ሀብት ላይ የተሾመ የቤተ መንግሥት ባለ ሥልጣን ነበረ የሚለው ያመዝናል፡፡



፬

# የምድረ፡በዳው፡አንባቢ

## ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ መቼ ገባ?

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ መቼ ገባ? በሚለው ርእስ ላይ በታሪክና በሃይማኖት ሊቃውንት የሚሠነዘሩ ሦስት ዓይነት የሃሳብ ወገኖች አሉ:: አንደኛው ወገን ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ገና በአንደኛው ክፍለ ዘመን በጃንደረባውና እንደርሱ ባሉ የኢየሩሳሌም ተሳላሚ ኢትዮጵያውያን ቤተ አይሁድ በኩል ገብቷል የሚል ነው:: ሁለተኛው ወገን በሐዋርያው ማቴዎስ ስብከት ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ገብቷል የሚል ነው:: ሦስተኛው ወገን ደግሞ በአራተኛው ክፍለ ዘመን በፍሬምናጦስ በኩል ገብቷል ባይ ነው:: ሦስቱንም አመለካከቶች ለየብቻ እንመልከታቸው::

በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ገባ የሚለው አሳብ በሁለት መልኩ ነው:: አንደኛው ኢትዮጵያ ከክርስቶስ ልደት በፊት የአይሁድ እምነት በመቀበሏ ምክንያት ከኢየሩሳሌም ጋር ከነበራት ቅርበት ጋር ይያያዛል:: በበዓለ ሃምሳ ሐዋርያት

መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው በብዙ ቋንቋ ሲናገሩ ለበዓሉ የሔዱ ኢትዮጵያውያን አይሁድንም በግእዝ ቋንቋ ሰብከዋቸው ወንጌልን ተቀብለዋል የሚል ነው:: ይህንን ሃሳብ ከቀደምት አበው ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የተናገረው ሲሆን ከታሪክ ምሁራንም ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅና ፕሮፌሰር ሥርግው ሐብለ ሥላሴም ዋቢ አድርገው ጽፈውበታል::[20]

ሁለተኛው ወገን ደግሞ ‹ሐዋርያው ማቴዎስ በኢትዮጵያ አስተምሮ ሰማዕት ሆኖ አርፏል ፤ ክርስትናም ወደ ኢትዮጵያ የገባው በቅዱስ ማቴዎስ ሐዋርያነት ነው› የሚል ነው:: ቅዱስ ማቴዎስ በኢትዮጵያ አስተምሯል የሚለውን ሃሳብ የጻፈው ጥንታዊው የታሪክ ጸሐፊ ሩፊኖስ እና ሶቅራጥስ ናቸው::[21] የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስንክሳር ግን ሐዋርያውን በሚዘክርበት የጥቅምት ዐሥራ ሁለት ምንባብ ይህንን ጉዳይ አላነሣም:: አንዳንድ የሀገር ውስጥ መዛግብት

[20] St. Jhon Chrysostom, Homily on Epiphany, / Ephraim Isaac, The Ethiopian Orthodox Church, The Red Sea Press, Institute of Semetic Studies, Princeton page 17,/ Sergew Hable Selassie, Ancient and Medival Ethiopian History to 1270, p 97

[21] Rufinus, Historica Ecclesiastica, Vol. xxi, col 479 ፣ Socrates Scolasticus – Historia ecclesiastica p. 57 / ሩፊኖስ ታሪኩን የጻፈው ከፍሬምናጦስ ወንድም ከኤዴስዮስ ቢሆንም (ታሪኩን የጻፈበት ጊዜ በእርጅናው ዘመን በመሆኑ ዘንግቶ ይሆናል ይባላል) የታሪኩን መቼት ኢትዮጵያ በማለት ፈንታ ሕንድ ብሎ ጽፎታል::

ግን ቅዱስ ማቴዎስ በትግራይ አድዋ አውራጃ ናዕዴር በተባለ ሥፍራ እንዳስተማረ ይገልጻሉ፡ ፡[22]

ይሁንና ቅዱስ ማቴዎስ ‹አስተምሯል› ከሚለው ሃሳብ በቀር በኢትዮጵያ ሰማዕት ሆኖ ሞተ የሚለውን ሃሳብ ቤተ ክርስቲያኒቱ አጥብቃ ትቃወመዋለች፡፡ በገድለ ሐዋርያት የተጻፈው ቅዱስ ማቴዎስ በግሪክ አጵሎን የተባለ ጣዖት በሚመለከበት ሥፍራ በሰማዕትነት መሞቱን ነው፡፡

ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫም ‹‹ሀገራችን ኢትዮጵያ ግን እንዲህ አይደለም የሐዋርያት እግር በእርሷ ላይ አልተመላለሰም የጌታም ተአምራት በውስጧ አልተደረገም በዜና አመነችው በድምፅም ተቀበለችው እንጂ›› ‹‹ወሀገርነሰ፡ ኢትዮጵያ፡ አኮ፡ ከማሁ፡ ኢያንሶሰዋ፡ እግረ፡ ሐዋርያት፡ ዲቤሃ፡ ወኢተገብረ፡ መንክራተ፡እግዚእ፡በውስቴታ፡አላ፡አምነቶ፡በዜና፡ወተወክፈቶ፡በድምፀ›› በማለት የማቴዎስን መምጣት የማያሳይ ሐተታ ጽፎአል፡ ፡ (መጽሐፈ፡ምሥጢር፡፯፥፬)

እንደ አለቃ አያሌውና መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬ የመሳሰሉ የኋላ ሊቃውንትም ‹‹ኢትዮጵያ ራስዋ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ዘርግታ ተቀበለችው እንጂ ተከራክሮ ያሳመናት የውጪ

[22] ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ ገጽ 95

ሀገር ሰው የለም፡፡ በብሉይም ሆነ በሐዲስ እጁና ልቧ ከነቢያት ከሐዋርያት ደም ከጻድቃን በቀል ከሰማዕታት ቂም ንጹሕ ነው›› በማለት በመንፈሳዊ ኩራት ጽፈዋል፡፡

ሦስተኛው የክርስትና አገባብ ሦስት ምዕተ ዓመታት ዘግይቶ በአራተኛው ክፍለ ዘመን በከሳቴ ብርሃን አባ ሰላማ (ፍሬምናጦስ) እና በወንድሙ ኤዴስዮስ አማካኝነት ክርስትና ገባ የሚለው ድምዳሜ ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ግሪካውያን ወንድማማቾች በምርኮ ወደ አክሱም ቤተ መንግሥት በመግባታቸውና ከነገሥታቱ ልጆች ጋር አብረው በማደጋቸው ምክንያት ክርስትናን ማስተማር የቻሉ ሲሆን በኋላም በነገሥታቱ መጠመቅ ምክንያት ክርስትና የሀገሪቱ ብሔራዊ ሃይማኖት ሆኖአል፡፡[23]

ድርሳነ ጽዮንም ‹‹ወአመ፡ ፲፩፡ ወ፫፡ ዓመተ፡ መንግሥቶሙ፡ ለአብርሐ፡ ወአጽብሐ፡ መጽአ፡ ጥምቀተ፡ ክርስትና፡ ውስተ፡ ኢትዮጵያ፡ በምድረ፡ አክሱም›› ‹‹አብርሐና

---

[23] የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ በ2009 ዓ.ም. ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ወደ ሊባኖስ በተጓዘበት ወቅት በሜዲትራንያን ባሕር ዳርቻ በምትገኘው የጢሮስ ከተማ ለጥቂት ቀናት ቆይቶ ነበር፡፡ በዚያም በነበረበት ቤተ ክርስቲያን ለብቻ ተከልሎ የተሠራ የጸሎት ሥፍራ አይቶ ነበር፡፡ ቀርቦ ሲጠይቅ ሥፍራው ሁለቱ ግሪካውያን ወንድማማቾች ከአባታቸው ጋር ይኖሩ የነበረበት ሥፍራ ሲሆን በመርከብ ተሣፍረው ወደ አክሱም የተጓዙበት ወደብ በቅርበት የሚገኝበት በመሆኑ ለኢትዮጵያውያን ከሳቴ ብርሃን የሆነው ቅዱስ ፍሬምናጦስ መታሰቢያ መሆኑን ከሥፍራው ባለቤቶች ተረድቶ ለኢትዮጵያውያን የመጀመሪያው ጳጳስ የሆነው አባ ሰላማ ጉዞ የጀመረበትን ሥፍራ ተሳልሞ መጥቷል፡፡

አጽብሐ በነገሡ በ፲፫ኛው ዓመት የክርስትና ጥምቀት በአክሱም ምድር ወደ ኢትዮጵያ መጣ›› ይላል፡ ፡[24]

እርግጥ ነው ከዚያ በፊት ክርስትና በኢትዮጵያ በብሔራዊ ሃይማኖት ደረጃ ሥፍራ አላገኘም፡ ፡[25] በኢትዮጵያም የጣዖትም ሆነ የዘንዶ አምልኮ እንደነበረ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ፡ ፡ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በመጽሐፈ ምሥጢር ‹‹የዘንዶውን ራስ ቀጠቀጠህ ለኢትዮጵያም ሰዎች ምግባቸውን ሠጠሃቸው›› የሚለውን ቃለ ትንቢት በተረጎመበት አንቀጽ እግዚአብሔር ለኢትዮጵያውያን ምግብ የተባለ ሃይማኖትን ከመሥጠቱ በፊት ያመልኩ የነበረውን የዘንዶ አምልኮ እንዳጠፋላቸው መስክሮአል፡ ፡ በኋላ ወደ ክርስትና የተመለሱት ነገሥታትም የቀደመ ሳንቲማቸው በፀሐይ በጨረቃና በከዋክብት ማምለካቸውን የሚያሳይ ነበር፡ ፡

ይሁንና በብሔራዊ ደረጃ አልደረሰም ሊባል ይችላል እንጂ ክርስትና እስከ አራተኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ቆይቶ ወደ ኢትዮጵያ

---

24 Amsalu Tefera, *The Ethiopian Homily on the Ark of the Covenant: Critical Edition and Annotated Translation of Dərsanä Ṣəyon*. TSEC vol. 5, Leiden. Brill, 2015, p.93. [ለሰፊ ገለጻ፣ በዚሁ መጽሐፍ ገጽ 184-187]።

25 BRUK AYELE ASALE , *1 ENOCH* IN *JUDE* AND IN THE EOTC "CANON": p-165 footnote, citing / Baur, John 2009, *2000 Years of Christianity in Africa: An African Church History*, 2nd ed., Nairobi: Paulines Pub.

ገባ የሚለው ሃሳብ ግን በብዙ መልኩ አሳማኝ አይደለም:: የኢትዮጵያ ግዛት እስከ ጋዛ በሚደርስበትና አክሱም ለመካከለኛው ምሥራቅ ከነበራት የአዱሊስ ወደብን ማእከል ያደረገ የንግድ ትስስር አንጻር ክርስትና ከኢየሩሳሌም አክሱም ለመድረስ አራት መቶ ዓመታት ፈጀበት ብሎ መቀበል እጅግ የሚከብድ ነው::[26]

በጣዖት አምልኮ የኖረው ዓለም ክርስትናን በፍጥነት በተቀበለበትና ወንጌል በተዳረሰበት ጊዜ ብሉይ ኪዳንን ተቀብላ የኖረችው ኢትዮጵያ ከመካከለኛው ምሥራቅ አፍንጫ ሥር ሆና ወንጌልን ጨርሶ አልሰማችም ማለትም እጅግ የማይታሰብ ነው:: የአባ ሰላማ ስብከት በቀላሉ ተቀባይነት ማግኘቱም አስቀድሞ የክርስትና ዜና ለመሰማቱ ማሳያ ነው::

ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የአባ ሰላማን ውለታ በዜማ ሲያመሰግኑም በጃንደረባው ጥምቀት መምጣቱን ሳያነሡ አላለፉም :-

«ጥምቀተ፡አምጽዓ፡ሕጽወ፡ንግሥት፡ለእሊአሁ፡
እም፡ኀበ፡ፊልጶስ፡ድኅረ፡ተጠምቀ፡ኪያሁ፡
ሰላማ፡አቡነ፡አምጽዓ፡ለነ፡በዕድሜሁ፡

[26] በቅርቡም በጣሊያናዊ የሥነ ጥንት (አርኪዎሎጂ) ባለ ሙያ በተደረገ የጥናት ውጤት እጅግ ጥንታዊው የምሥራቅ አፍሪካ ቤተ ክርስቲያን ቅሪት በአዱሊስ ተገኝቷል:: https://archaeologynewsnetwork.blogspot.com

ለመድኀኒነ፡ምሥጢረ፡ደሙ፡ወሥጋሁ›

‹‹ከፊልጶስ ዘንድ ከተጠመቀ በኋላ የንግሥቲቱ ጃንደረባ ጥምቀትን ለወገኖቹ አመጣ፡፡ አባታችን ሰላማ ደግሞ በዕድሜው የመድኃኒታችንን የሥጋና ደሙን ምሥጢር አመጣልን››[27]

እንደ ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት ያሉ የታሪክ ምሁራን ክርስትና ከአራተኛው ክፍለ ዘመን በፊት ወደ ኢትዮጵያ ስለመግባቱ ፍንጮች እንደነበሩና ከአራተኛው እስከ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ድረስ የተገኙ የግእዝ መዛግብት ከመጻሕፍቱ መተርጎም በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ የተስፋፋ ክርስትና ለመኖሩ ማስረጃዎችን ያሳያሉ ሲሉ ጽፈዋል፡፡[28]

ዶ/ር መብራቱ ኪሮስም (ቀሲስ) በፒኤችዲ ማሟያ ጽሑፋቸው ይህንን የክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባበትን መቼት ሲያነሡ ፡-

‹‹በክርስትና ቀዳማዊ ዘመናት ወቅት የአክሱም ሥርወ መንግሥት ከሮም አገዛዝ ጋር የቀረበ ትስስር ነበረው፡፡

[27] ዋዜማ ዘፊልጶስ

[28] Richard Pankhurst, The Ethiopians, The People of Africa Series /Oxford, Blackwell pub, 1998} Discovery of earliest Illuminated Gospel manuscripts Anthology of African Christianity, Christianily in Ethiopia, Bruk Ayele Asale, WCC, page 576

አክሱማውያን ገዢዎችም ከግሪክ ሥልጣኔ ጋር ትውውቅ ነበራቸው፡፡ የአክሱም ነገሥታት ራሳቸውን በቀይ ባሕርና በዓረብ ባሕረ ሰላጤ ደሴቶች ላይ ልዕልና ያላት የኢትዮጵያ ኃያላን ገዢዎች ማድረጋቸው በሮማውያን ነገሥታት ዘንድ በትኩረት የሚታዩ ተፎካካሪዎች እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ የሥርወ መንግሥቱ መናገሻ የነበረችው አክሱም በቀይ ባሕር ላይ በነበራት የአዱሊስ ወደብዋ ከግሪክና ሶርያ ለሚመጡ ነጋዴዎች የመገበያያ ማዕከል ነበረች፡፡ እነዚህ ክርስቲያን ነጋዴዎች ከኢትዮጵያውያን መካከል ወደ ክርስትና ማርከው ጥቂት ሰዎችን ለውጠው እንደሆን አይታወቅም››

በማለት ክርስትና እንዲገባ የሚያደርግ ዕድል የነበረ መሆኑን ካመለከቱ በኋላ ፡-

‹‹ይሁንና በሐዋ. ፰፥፳፮ ላይ የተመዘገበው የኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ማመንና መጠመቅ ለክርስትና በኢትዮጵያ መሰበክ አስተዋጽ አድርጓል›› በማለት ደምድመዋል፡፡[29]

---

[29]Mebratu Kiros Gebru, Liturgical Cosmology, The Theological and Sacramental Dimensions of Creation in the Ethiopian Liturgy page 17 ትርጉም የእኔ

## የጀንደረባው ዜግነት

ኢትዮጵያ የሚለው ስያሜ በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በታሪክ ዘርፍ የዛሬይቱን ኢትዮጵያ ብቻ የሚመለከት ስያሜ አይደለም:: ብዙ መዛግብት እንደሚያስረዱት በጥንቱ መልክዓ ምድር ኢትዮጵያ የሚለው ስያሜ ከግብፅ በስተደቡብ ያለውን ኑቢያን (መርዌን) ፣ አክሱምን ፣ ምድረ አግዓዚን በአጠቃላይ የኩሽ ሀገርን ሁሉ የሚያካትት ስያሜ ነበር:: ስለዚህ ጉዳይ እንደብዙ ጸሐፍት ሁሉ የኢትዮጵያ ባለ ውለታ የሆኑት ሲልቪያ ፓንክረስት ‹‹በጊዜው ኢትዮጵያ የሚለው ስም በአባይ ወንዝና በቀይ ባሕር ፣ በምድር ወገብና በሕንድ ውቅያኖስ መካከል ያሉትን ሀገራት ሁሉ የሚያጠቃልል ስያሜ ነበር›› ሲሉ ጽፈዋል::[30]

አንዳንዶች የጥንትዋን ‹ኢትዮጵያ› ከዛሬይቱ ለመለየትና በመጽሐፍ ቅዱስ የነበረችው ኢትዮጵያ የዛሬዋ ሳትሆን ሱዳን ብቻ ናት ለማለትና በመጽሐፍ ቅዱስ ኀትም ሳይቀር ለመጻፍ የሞከሩ ነበሩ:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በዚህ የኢትዮ ሱዳን ታሪካዊ ሽሚያ ዙሪያ ‹የዛሬዋ ኢትዮጵያ የቅዱሳት መጻሕፍት ፣ የታሪክና የሥነ ጥንት ኢትዮጵያ

[30] Sylvia Pankhurst, Ethiopia : A Cultural History, London, Lalibela House, 1955, p. 1} Budge, A History of Ethiopia, Nubia and Abyssina /London 1928 p.122/

ናት› በሚል ርእስ ለመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር የሰጠው ኦፊሴላዊ ምላሽ ሁለቱንም እውነታዎች ያልካደና እንዲህ የሚል ነበር፡-

‹‹በመጽሐፍ ቅዱስ አነጋገር ሱዳን ኢትዮጵያ አልነበረም ማለት አይደለም ወይም ኩሽ የዛሬይቱን ኢትዮጵያ አይሸፍንም ማለትም አይሆንም፡፡ ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ ‹ኢትዮጵያ› ሲል ብዙ ጊዜ የሚናገረው ከግብፅ ደቡብ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ድረስ ያለውን አካባቢ ሲሆን በዚህ ክልል የሚገኙት ደግሞ ኢትዮጵያና ሱዳን ናቸው››[31]

በማለት ‹ኢትዮጵያ› የሚለው ስያሜ ሱዳንን ያካትታል ማለት የዛሬይቱን ኢትዮጵያ ከጥንት ኢትዮጵያነት ውጪ ያደርጋታል ማለት አለመሆኑን የቤተ ክርስቲያኒቱ ቅዱስ ሲኖዶስ አቋሙን አስቀምጧል፡፡

በዚህም የተነሣ ኢትዮጵያ የሚለው ስም በዛሬው መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ሱዳንን ፣ ኢትዮጵያን ፣ ኤርትራን እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ያሉ ግዛቶችን ሁሉ የሚያካትት ስያሜ ነበር፡፡ በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ታሪክ ላይ የተጠቀሰችው ንግሥት ሕንደኬ በአብዛኛው የታሪክ ጸሐፍት ዘንድ ኑቢያን መናገሻዋ ያደረገች

---

[31] ‹የዛሬዋ ኢትዮጵያ የቅዱሳት መጻሕፍት ፣ የታሪክና የሥነ ጥንት ኢትዮጵያ ናት› የኢኦተቤ/ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ነሐሴ 1989 ዓ.ም.

ንግሥት እንደነበረችና ‹ሕንደኬም› እንደ ‹እቴጌ› ያለ የኑቢያ ንግሥታት ስመ መንግሥት እንደነበረ ተጽፎአል፡፡ በዚህ ምክንያት ይህ ጀንደረባ ‹ከኢትዮጵያ ተሰልቦ / እንደ ባሪያ ተሸጦ የሔደ ነው ካልተባለ በቀር ንግሥቲቱ ግን ኑቢያዊት ናት› ብለው ጠንክረው የሚከራከሩ ሊቃውንትም አሉ፡፡ ይሁንና በህንደኬ ማንነት ዙሪያ የተጻፉ የታሪክ መዛግብትም ሆኑ ታሪክ ቀመስ ልብ ወለዶች እርስ በእርስ የማይስማሙና ብዙ ማጣራት የሚጠይቁ ከመሆናቸው በላይ ንግሥቲቱ ከታላቁ እስክንድር ጋር ነበራት ተብሎ የሚተረከው የፍቅር ታሪክም ከንግሥተ ሳባና ንጉሥ ሰሎሞን ታሪክ የተቀዳ ነው የሚል ብዙ ትችት የዘነመበት ነው፡፡[32]

የሀገራችን ታሪክ ጸሐፍት ንግሥቲቱ ግዛትዋ ኢትዮጵያ ነው ባሉበት ሥፍራ የኢትዮጵያ ግዛት ሰፊ መሆኑን የሚያጣቅሱ ሲሆን ‹መናገሻዋ ኑቢያ ወይንስ አክሱም› በሚለው ላይ ብዙዎቹ አስተያየት አልሰጡም፡፡ በአንጻራዊ ሚዛናዊነታቸው የሚታወቁት ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ንግሥት ሕንደኬ ግዛትዋ ከእነዚህ ሀገራት አልፎ ወሰን ተሻግራ ጋዛ ድረስ ርስት እንደነበራት የጻፉ ሲሆን የንግስቲቱም ስም ገርሳሞት ይባል እንደነበርና ከ፴፬—፵፪ ዓ.ም. እንደነገሡች

[32] 'the conflation was a part of the ancient blending of candace- Sheba and Solomon Alexander stories.'' /E. Ullendorff, Candance and Queen of Sheba,, NT studies 2 {1955-1956, 53,6}

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባም በጋዛ የሚገኘውን ርስትዋን እንዲጠብቅ የተሾመ የግምጃ ቤትዋ ሹም እንደነበረ ጽፈዋል፡፡[33]

ይህች ንግሥት የነገሡችው ኢትዮጵያ ተብለው በተጠሩ በእነዚህ ሁሉ ሀገራት ላይ ከነበረና ጃንደረባውም የእርስዋ ሹም ከሆነ ይህንን ጃንደረባ ‹የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የእኔ ነው ልትል የምትችልበት መሠረት ምንድርን ነው?› የሚል ጥያቄ ይከተላል፡፡ እርግጥ ነው የታሪክ ጥናት በሚጠይቀው መሥፈርት ከሔድን ‹ይህ ጃንደረባ በዛሬው መልክዓ ምድር የዚህኛው ሀገርና አካባቢ ተወላጅ ነው ወይም አይደለም› ብሎ ለመደምደም የሚያስችል የተረጋገጠ ምንም የታሪክ ማስረጃ አልተገኘም፡፡ ሆኖም ‹የማስረጃ አለመኖር ግን ያለመኖር ማስረጃ አይደለም› (The absence of evidence is not the evidence of absence) እንደሚባለው ማስረጃ አልተገኘም ተብሎ ሕልውናውን መካድ አይቻልም፡፡

በእርግጠኝነት ይህ ሰው አፍሪካዊ ነው ፤ ከአፍሪካም ግብፃዊ ሊሆን እንደማይችል በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ ስለዚህ የዚህ

---

[33] ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ ፤ የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግሥተ ሳባ እስከ ዐድዋ ገጽ 11

ሰው ማንነት የሚወድቀው ኢትዮጵያ በሚባለው ሰፊ ግዛት ውስጥ ባሉ የዛሬዎቹ ኢትዮጵያ ኤርትራ እና ሱዳን ላይ ነው፡፡

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ‹ሱዳናዊ ነው› ብለው ደምድመው የጻፉ የሀገር ውስጥም የሀገር ውጪም ጸሐፍት አሉ፡፡ ጥቂቶቹን ብንጠቅስ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ መምህር የነበሩት ዶ/ር ራልፍ በፒኤችዲ ጽሑፋቸው ይህንን የሐዋርያት ሥራ ታሪክ ባነሡበት አንቀጽ ‹‹በእነዚህ ምንባባት ኢትዮጵያ ተብሎ የተጠቀሰው ያለ ጥርጥር የሚያመለክተው ኑቢያን ወይንም መርዌን ነው›› ሲሉ ጽፈዋል፡፡

አለቃ ኪዳነ ወልድም /ምንም ማስረጃ ባይጠቅሱም/ ‹‹በበዓለ ጰራቅሊጦስ ከኢትዮጵያ የሔዱ ፈላሾችና አይሁድ ሐዋርያት በግእዝ ቋንቋ ሲናገሩ ሰምተው አምነው ጴጥሮስ ካጠመቃቸው ሦስት ሺህ አርድእት ተቆጥረዋል፡፡ እነዚህ ኢትዮጵያውያንም እንደ ኖባ ንግሥት ጃንደረባ እየዞሩ በየአህጉሩ ሰብከዋል እርሱ ለሱዳኖች እንደሰበከ›› ብለው የክርስትናን

ለኢትዮጵያ መሰበክ ከጃንደረባው በፊት ነው የሚለውን ሃሳብ ደግፈው ጃንደረባውንና ንግሥቲቱን ሱዳናውያን ናቸው ብለዋል፡፡[34]

አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያም ስለ ኑቢያና አክሱም ልዩነትና አንድነት በሰፊው በተነተኑበት መጽሐፋቸው ‹‹በክርስትና ዘመን በፊልጶስ በአርድዕቱ እጅ የተጠመቀው ጃንደረባ የሕንደኬ አራተኛ ነው፡፡ ነገር ግን ጃንደረባው ወደ መርዌ ተመልሶ ምንም ያህል ክርስትና ሊስፋፋ አልቻለም›› በማለት ጃንደረባውን ለመርዌ እንደሚጠጋ ጽፈዋል፡፡[35]

ሕንደኬ ለኑቢያ የምትቀርብበት ብዙ ማስረጃ ካለና ጃንደረባውንም ወደ ኑቢያ የሚስበው ከበዛ ይህ ጃንደረባን ኢትዮጵያ የእኔ ነው የምትልበት መሠረትዋ ምንድን ነው? ወደሚለው ጥያቄ እንምጣ፡፡

ጃንደረባውን ከሱዳን ወደ ኢትዮጵያ የሚስበው ብቸኛ ቁምነገር በሐዋርያት ሥራ ላይ በተጻፈው ታሪኩ ላይ ባለው እውነታ የአይሁድን እምነት የተቀበለ መሆኑ ነው፡፡ ጃንደረባው ወደ ኢየሩሳሌም ለመስገድ የሚጓዝ ጽሙድ አይሁዳዊ (Devoted Jew)

---

[34] Lee, Ralph 2011 Symbolic interpretations in Ethiopic and Ephremic Litreture, Phd thesis, SOAS, Univercity of London, አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ሃይማኖተ አበው ቀደምት

[36] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ፤ ኑብያ (ናፓታ-መርዌ) ፤ 1965 ዓ.ም አዲስ አበባ ፤ ገጽ 267

መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን እያነበበ የመጣው የነቢያት መጻሕፍትን መሆኑና ‹ነቢዩ ስለራሱ ተናግሮታል ወይንስ ስለሌላ› የሚለው ብስለት የተሞላ አጠያየቁ ደግሞ ሥር የሰደደ የአይሁድ እምነት ተከታይ መሆኑን ያሳያል፡፡

‹የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት› መጽሐፍ ላይ ‹‹የሰውዬው የቀድሞ ሃይማኖት ላይ ያተኮርን እንደሆንን [ሱዳናዊ ነው የሚለውን] አባባል ለመቀበል ይቸግረናል››[36] ሲሉ የጻፉትፕሮፌሰር ሥርግውሐብለ ሥላሴ ‹Ancient and Medieval Ethiopian History to 1270› በተሰኘው ተጠቃሽ መጽሐፋቸው ደግሞ ይህንን ጉዳይ በዝርዝር እንዲህ ሲሉ ይሞግታሉ ፡-

‹‹ለአብዛኛው የግሪክ ጸሐፍት ኢትዮጵያ የሚለው ስም ያልጠራና አጠቃላይ ስያሜ ይሆንባቸዋል፡፡ ስለዚህ ጥያቄው ይህ ሰው ከየትኛው ሀገር የመጣ ነው የሚለው ነው፡፡ ሉቃስ ይህ ሰው የንግሥት ሕንደኬ በገንዘብዋ ሁሉ የሠለጠነ ብሎታል፡፡ ሕንደኬ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ከሮማውያን ጋር ራስዋን ለመከላከል ባደረገቻቸው ጦርነቶች ምክንያት ስምዋ በግሪክና ሮማውያን ጸሐፊዎች ዘንድ የታወቀ ነው፡፡ በዚህ የተነሣ ብዙ ጸሐፊዎች

[36] ሥርግው ሐብለ ሥላሴ (ዶ/ር)፤ አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ፤1988 ዓ.ም. አዲስ አበባ ቅጽ. 7 ገጽ 6

የሁሉም የኢትዮጵያ ግዛቶች ንግሥት የነበረች በመሆንዋ ላይ ይስማማሉ፡፡ በሐዋርያት ሥራ ላይ የተገለጠው ሰው እንግዲህ የዚህች ንግሥት በጅሮንድ ነው››

በማለት የንግሥት ሕንደኬን ግዛት ስፋት ከመሰከሩ በኋላ ይህ ሰው የኑቢያ (መርዌ) ሰው ይሆንን በሚለው ጉዳይ ላይ የሚከተለውን ሃሳብ አስፍረዋል፡-

‹‹እንደ እውነታው ከሆነ ስለዚህ ሰው ማንነት ምንም ማስረጃ የለንም ፤ ይሁንና በሐዋርያት ሥራ ላይ ይህ ሰው የአይሁድን እምነት የተቀበለና መጽሐፍ ቅዱስን ሲያነብ የነበረ መሆኑ ተገልጧል፡፡ የመርዌ ነዋሪዎች የአይሁድን ሃይማኖት ተቀብለው ነበር የሚል ነገር ደግሞ ከየትኛውም ምንጭ አልሰማንም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በኤለፋንታይን (በላዕላይ ግብፅ) ጠንካራ የአይሁድ ማኅበረሰቦች እንደነበሩ ይታወቃል፡፡ ምናልባት እነዚህ ማኅበረሰቦች /የኑቢያን/ ሀገር በቀል ሕዝቦች ወደ ይሁዲነት ለውጠዋቸው እንደሆን አይታወቅም››

‹‹በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጥናት ዘርፍ ‹ክርስትና እንዴት ወደ ኑቢያ ገባ?› በሚለው ርእሰ ጉዳይ ላይ ዘመኑን ያሳለፈው የኤፌሶኑ ዮሐንስ ስለዚህ ጉዳይ [ወደ ኑቢያ የአይሁድ እምነት ቀድሞ ገብቶ የነበረ ስለመሆኑ] ጨርሶ ምንም ፍንጭ አልሠጠም፡፡ ከዚህ

በተቃራኒው ግን በአክሱማዊው ሥርወ መንግሥት አይሁዳዊነትና አምላክ የለሽነት ክርስትና በይፋ ከመግባቱ በፊት እንደሚቀድሙ በግልፁ የታወቀ ነው፡፡ ክርስትና ከአራተኛው ክፍለ ዘመን በፊት ወደ አክሱም በተወሰነ መልኩ ገብቶ እንደነበር የሚያስጠረጥሩ መረጃዎች አሉ፡፡

ከዚህ ጋር በተገናኘም ኦሪገን ፡- ወንጌል ለሁሉም ኢትዮጵያውያን አልተሰበከም ነበር፡፡ በተለይም ከወንዞች ባሻገር ለሚኖሩት አልደረሰም›› ብሏል፡፡ በኢትዮጵያ እዚህና እዚያ የተበታተኑ ክርስቲያን ማኅበረሰቦች ግን ነበሩ፡፡ ይህም የጃንደረባው ማመን ፍሬ ሊሆን ይችላል፡፡ የግሪክ ነጋዴዎችም ይህንን ሥራ ገፍተውበት ነበር›› በማለት አጠቃልለዋል፡፡[37]

ፕሮፌሰር ሥርግው ጃንደረባው የአይሁድን እምነት መቀበሉን እና የአይሁድ እምነት በኑቢያ ስለመኖሩ ፍንጭ አለመኖሩን በአንድ ወገን ፤ በአክሱም የአይሁድ እምነት ሥር ሰድዶ መቆየቱን በሌላ ወገን አስቀምጠው ይህንን ጠንካራ ይሁዲ ጃንደረባ ከኑቢያ ይልቅ ለኢትዮጵያ የቀረበ መሆኑን አሳይተዋል፡፡

---

[37] Sergew Hable Selassie, Ancient and Medival Ethiopian History to 1270, p 99 / A. Harnack, The Expansion of Christianity in the 1st three Centurys, 1905, vol.iii p.123

ይህ ብቻ አይደለም የአይሁድ እምነት ኑቢያ ውስጥ ካለመገኘቱ ባሻገር የኑቢያን የክርስትና ታሪክ የሚያወሱ መዛግብትም ይህንን ጃንደረባ ጨርሰው አያነሡትም፡፡ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ በጻፉት የኑቢያ ታሪክ ላይ በ፱፫ ዓመተ ምሕረት የኑቢያ ንጉሥ ክርስትናን ተቀብሎ እንደነበርና በኋላ ግን ኑቢያውያን በኃይል ወደ እስልምና ስለመሔዳቸው ጽፈዋል፡፡ ሆኖም ይህ ትርከት ከጃንደረባው ታሪክ ጋር ግንኙነት የለውም፡፡[38]

የሱዳንን የክርስትና ታሪክ ያጠናው ቻማህ ጃካውንዳ ግን የሱዳንን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በሦስት ክፍለ ዘመናት የከፋፈለ ሲሆን የጥንታዊት ኑቢያ ቤተ ክርስቲያን (The Church in Ancient Nubia) ብሎ በመጀመሪያ ደረጃ ያስቀመጠው ከ543-1504 ያለውን ጊዜ መሆኑ የኑቢያ የክርስትና ታሪክ ከጃንደረባው ታሪክ ምን ያህል በዘመናት የራቀ ለመሆኑ አመላካች ነው፡፡[39] ሌላው የኑቢያ ክርስትና አጥኚ ዶ/ር ሳሊም ፋራጅ ደግሞ የኑቢያ ክርስትና ከግብጽ የተገኘ መሆኑን ጽፎአል፡፡[40]

---

[38] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ፤ ኑብያ (ናፓታ-መርዌ) ፤ 1965 ዓ.ም አዲስ አበባ ፤ ገጽ 267

[39] Anthology of African Christianity, Chammah Jkaunda, Christianity in Republic of Sudan, page 712 E.A Wallis Budge,(1928) A history of ethiopia, nubia, abyssinia p. 111-119,

[40] Dr. Salim Faraji, The Roots of nubian chrsitianity uncovered, the Triumph of the last pharoah, Storial della nubia cristiania, rome 1938 too. p 130

## በስረገካ ተቀምጦ

በአንድ ወቅት የበረሃውን ኮከብ የአባ እንጦንስን ዝና የሰማው ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ከጻድቁ አባት ጸሎትና ምክር ለመቀበል አስቦ የሰላምታ ደብዳቤ ጽፎ በወታደሮቹ እጅ ወደ ግብፅ በረሃ ላከ፡፡ የንጉሡ ወታደሮች ወደ በረሃው ሲደርሱ አባ እንጦንስ በበዓቱ ቁጭ ብሎ መጽሐፍ ቅዱስን እያነበበ ነበር፡፡ የተላከውን መልእክት ከፍቶ እስከሚያነብላቸው የጓጉት የአባ እንጦንስ ደቀ መዛሙርት አባ እንጦንስ ከብበው ቢጠባበቁም እርሱ ግን ከሚያነበው መጽሐፍ ዓይኑን አልነቀለም፡፡ በመጨረሻም አንዱ ተማሪው ‹‹አባታችን ከንጉሥ ቆስጠንጢኖስ የተላከ ደብዳቤ እኮ ነው ክፈተው እንጂ›› ብሎ ተቁነጠነጠ፡፡ አባ እንጦንስ ግን ቀና ብሎ ‹‹እኔ ከሰማያዊ ንጉሥ የተላከልኝን ደብዳቤ እያነበብሁ ነው›› ብሎ ከተናገረ በኋላ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ንባቡ ተመለሰ፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ በእርግጥም ለእያንዳንዳችን የተላከ የሰማያዊ ንጉሥ ደብዳቤ ነው፡፡ ይሁንና ብዙዎቻችን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ቁጭ ብሎ የማንበብ ልማድ የለንም፡፡ ምናልባትም ተልኮልን ጨርሰን ያላነበብነው ብቸኛ ደብዳቤ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡

ሳናነበው ልንሞት የምንችለውና እንዲያም ቢሆን ብዙም የማንቆጭበት አምላካዊ ደብዳቤ በብዙዎቻችን እጅ ቢኖርም ገና ለማንበብ ስናስብ የሚደክመን መሆኑ ያሳዝናል፡፡ ሰባኪው ለስብከቱ ሲል ከመግለጥ በቀር ለእኔ ብሎ አያነብም፡፡ አብዛኛው ሕዝበ ክርስቲያን ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን አክብሮ ከመሳለምና ክፉ መናፍስትን የሚያርቅ ቃል መሆኑን በማመን ከራስጌው ከማስቀመጥ አልፎ እንደ ክርስቲያን ወግ ቁጭ ብሎ ለራስ የማንበብ ልምድ የለውም፡፡

ብዙ ሰው መጽሐፍ ቅዱስ ለማንበብ ‹ጊዜ የለኝም› ‹የሥራዬ ጠባይ አያመቸኝም› ‹ብዙ ሓላፊነት አለብኝ› ‹ሳነበው ይከብደኛል› ወዘተ በሚሉ ብዙ ምክንያቶች ሰበብ መጽሐፍ ቅዱስን አያነብም፡፡ ያለንበት ዘመን መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ በእጅ ስልኮች ሳይቀር የሚቻልበት የተመቻቸ ዘመን ቢሆንም ተራ ነገሮችን ስናስስ የምንውል ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ ግን አንጠቀምበትም፡፡ ምናልባትም መጽሐፍ ቅዱሳችን እንደ ስልክ መተግበሪያዎች ለመጨረሻ ጊዜ የታየበትን ቀንና ሰዓት (last seen) ቢናገር ኖሮ ብዙዎቻችን ከመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ከራቅን የቆየን መሆናችን በተገለጠ ነበር፡፡

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ግን አስደናቂ የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢ ነበር፡፡ ይህ ሰው የአንዲት ሀገር ታላቅ ንግሥት የገንዘብ ሚኒስቴርዋ ነው፡፡ እጅግ ብዙ መንግሥታዊ ሓላፊነቶችም አሉበት፡፡ ከማንም በላይ አድካሚ የሆነ የሒሳብ ሥራ ያለበት ባለ ብዙ ሃሳብ ሰው ነው፡፡ ሆኖም ሌሎች ባለ ሥልጣናት እንደሚያደርጉት ብዙ ኪሎ ሜትሮችን ተጉዞ የሔደው ወደ ሥጋዊ መዝናኛ ሥፍራ ሳይሆን ወደ ቅድስት ሀገር ለፈጣሪው ሊሰግድ ነበር፡፡ ከአድካሚ የሰረገላ ጉዞ ሲመለስ ደግሞ ለራሴ ዕረፍት ልስጥ ሳይል የነቢዩን ኢሳይያስ መጽሐፍ ያነብ ነበር፡፡

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዲህ ይላል ፡-

‹‹በጉዞ ላይ ሆኖ ያውም በሰረገላ ላይ ተቀምጦ ማንበብን አለማቋረጥ ምን ያህል ትጋት የሚጠይቅ እንደሆነ እንድታስተውሉ እጠይቃችኋለሁ፡፡ በቤታቸው እንኳን ቁጭ ብለው ማንበብን ለማይፈልጉ ሰዎች ይህ ታሪክ ሊስተዋል ይገባዋል፡፡ ይልቁንም መጻሕፍትን ማንበብን ጊዜን እንደማጥፋት የሚቆጥሩ ወይንም ለትዳር አጋሮቻቸው ‹ጊዜ መሥጠት አለብኝ› የሚል ምክንያት የሚያቀርቡ ፣ በውትድርና አገልግሎት ላይ ነኝ የሚሉ ፣ ልጆቼን

እየተንከባከብኩ ነው ፤ ከንባብ ኑሮዬን ማስቀደም ይኖርብኛል የሚሉ ሰዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን የማንበብ ጠቀሜታው አይታያቸውም››[41]

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ግን ላለማንበብ ሰበብ የሚደረድር አልነበረም፡፡ ብዙ መንገድ ተጉዞ መሳለሙን እንደበቂ ነገር ቆጥሮ ለራሴ ዕረፍት ልሥጥ ሳይል በሚነቀንቅ ሰረገላ ላይ ሆኖ ማንበቡን ቀጠለ፡፡ ይህ ጃንደረባ መጽሐፍ ቅዱስን ላለማንበብ ‹ትርጉሙ አይገባኝም› የሚል ምክንያት ቢሠጥ ያስኬደው ነበር፡፡ እርሱ ግን ባይረዳውም እንኳን ማንበብ አላቆመም፡፡ ይህን ትጋቱን አይቶ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አስተማሪ ላከለት፡፡

## ከምስተኛው ወንጌል

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ምን ዓይነት ጻድቅ ሰው ነው? ከረዥም ጉዞ በኋላ ኢየሩሳሌምን ተሳልሞ በመመለስ ላይ ሆኖ እንኳን መንፈሳዊነቱ አልቀዘቀዘም፡፡ ከመንፈሳዊ ጉዞ የሚመለሱ ሰዎች ምናልባትም ከጉዞው መጠናቀቅ በኋላ ለራሳቸው ዕረፍትን ይሠጣሉ፡፡ ሰውነታቸውን የሚያዝናና ከድካማቸው የሚያበረታ ነገር ለማድረግ አያመነቱም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ከመንፈሳዊ ጉዞ መልስ

---

41 St. John Chrysostom, Homiies on Genesis 35.3

የሚያደርጉት መዝናናት ከገደብ አልፎ መስመሩን ጥሶ የጉዞውን በረከት እስከማሳጣት የሚደርስበትም ጊዜ አለ፡፡

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ግን ፍቅረ እግዚአብሔር የማይወጣለት መንፈሳዊ ነበር፡፡ የገንዘብ ሚኒስቴር እንደመሆኑ እንደ ባለ ሥልጣን ብዙ ሊያያቸው የሚችሉ መዛግብት ቢኖሩትም ከስግደት መልስ መጽሐፍ ቅዱስን እያነበበ የሚመለስ ባለ ሥልጣን ነበር፡፡

መንፈሳዊ መጻሕፍትን ለማንበብ ‹ሥራ ስለሚበዛብኝ ጊዜ የለኝም› የምትል ወንድሜ ሆይ እዚህ ላይ ራስህን ከጃንደረባው ጋር አነጻጽረው፡፡ ይቅርታ አድርግልኝ ምንም ሥራ ቢበዛብህ በንግሥት ሕንደኬ በገንዘብዋ ሁሉ ከሠለጠነው ለጅሮንድ በላይ ሥራ አይበዛብህም፡፡ ቅዱስ ጄሮም እንዲህ ሲል ራሱን ይወቅሳል ፡- ‹‹እዚህ ላይ ታሪኩን ትቼ ወደ ራሴ መለስ ልበል፡፡ የንግሥቲቱን ቤተ መንግሥት ትቶ ከምድር ዳርቻ ከኢትዮጵያ ድረስ ወደ ቤተ መቅደስ ከተጓዘውና ለእግዚአብሔር ሕግና ለአምላካዊ እውቀት ካለው ፍቅር የተነሣ በሰረገላው ላይ ሆኖ እንኳን ቅዱሳት መጻሕፍትን ከሚያነበው ከዚህ ጃንደረባ የተሻልሁ ጻድቅም ጽኑዕም አይደለሁም››[42]

[42] St. Jerome, Letters 53 to Paulinus of Nola, 5

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በሰረገላው ተቀምጦ ያነብ የነበረው ትንቢተ ኢሳይያስ የተሰኘውን መጽሐፍ ነበር፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ዛሬው ታትሞ ባልተሠራጨበትና የነቢያቱ መጻሕፍት አንድ ላይ ባልተጠረዙበት በዚያ ዘመን አንድን መጽሐፍ በግለሰብ ደረጃ ማግኘት እጅግ ከባድ ነበር፡፡ መጽሐፉ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጻፈበትን ብራና ወይንም ፓፒረስ ቅጂ (autograph) ማግኘት ጨርሶ የማይታሰብ ቢሆንም የመጻሕፍቱ የቅጂ ቅጂም ከሰው ወደ ሰው የሚሸገረው ሙሉ ሥራቸው መጻሕፍትን ከብራና ወደ ብራና እየጻፉ መገልበጥ በነበረው በቁምራን ዋሻ ይኖሩ እንደነበሩት ጸሐፍት (scribes) ዓይነት ሰዎች አማካኝነት ነበር፡፡

ይህንን የመጻሕፍት ቅጂ የራስ ለማድረግ እጅግ ባለ ጸጋ መሆን ይጠይቅ የነበረ ሲሆን አንድ ሰው የራሱ መጽሐፍ ቅዱስ አለው ማለት እጅግ ሀብታም ነው እንደማለት ነበር፡፡ ስለዚህ ጃንደረባው መንገድ ለመንገድ ይዞት የሚዞረው የራሱ የትንቢተ ኢሳይያስ ጥቅል የነበረው መሆኑ ከቤተ መንግሥት ሥልጣኑ ጋር ባለ ሀብትም እንደነበረ የሚያሳይ ነው፡፡ ለነገሩ ኢየሩሳሌም ድረስ በራሱ ሰረገላና አሽከሮች የሚጓዝ ሰው ባለጠጋ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡

ጃንደረባው የሚያነበው መጽሐፍ ትንቢተ ኢሳይያስ መሆኑ ደግሞ ክርስትናን ለመቀበል እጅግ የተመቸ ሰው እንዲሆን የሚረዳው

ነበር፡፡ ትንቢተ ኢሳይያስን የመጻሕፍት ሊቃውንት ‹ወንጌለ፡ ብሊት› ወይንም ‹ደረቅ፡ሐዲስ›፡‹ወንጌለ፡ኢሳይያስ› በማለት ይጠሩታል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ነቢዩ ኢሳይያስ በግልጥ ስለ ክርስቶስ ደጋግሞ ስለተናገረ ነበር፡፡ ሊቃውንቱ እንዲህ መስክረዋል ፡-

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ‹‹ከማንኛውም ነቢይ በላይ የወንጌልን ሃይማኖት ምሥጢር ያወቀው ኢሳይያስ ነበረ›› ሲል ቅዱስ ጄሮም ደግሞ ‹‹ኢሳይያስ ነቢይ ከሚባል ወንጌላዊ ቢባል ይሻላል፡፡ ምክንያቱን መጽሐፉ የሚመጣውን ነገር የሚናገር ሳይሆን የተፈጸመን ታሪክ የሚጽፍ እስከሚመስል ድረስ የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያንን ምሥጢራት ሁሉ ስለሚያትት ነው›› ብሏል፡፡[43] በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ እያነበበ የቆየው የብሉይ ኪዳኑን ወንጌል ነበር፡፡

እውነትም ትንቢተ ኢሳይያስ ስለ እግዚአብሔር ወልድ በግልጽ የሚናገር መጽሐፍ ነው፡፡ ‹‹ያዕቆብ ሆይ የጠራሁህ እስራኤል ሆይ ስማኝ እኔ ነኝ እኔ ፊተኛው ነኝ እኔ ኋለኛው ነኝ›› የሚል ቃል ስናነብ አልፋና ኦሜጋ ፊተኛውና ኋለኛው የሚል ቃል ያለበት የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ መኖሩ ያስደንቀናል፡፡ ‹‹እጄም

[43] St. Jerome, Preface to Isaiah 1.2

ምድርን መሥርታለች ቀኜም ሰማያትን ዘርግታለች ... እኔ ከጥንት ጀምሬ በስውር አልተናገርሁም፡፡ ከሆነበት ዘመን ጀምሮ እኔ በዚያ ነበርሁ አሁንም ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል›› የሚለው ቃል በትክክል ምሥጢረ ሥላሴንና ከእግዚአብሔር አብና ከመንፈሱ በተለየ አካሉ የተላከው ወልድ ስለመሆኑ በግልጥ ያስረዳል፡፡ (ኢሳ. ፵፰፥፲፪)

‹ከሆነበት ዘመን ጀምሮ እኔ በዚያ ነበርሁ› የሚለው ቃል ‹ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውስ አንዳችስ እንኳን ያለ እርሱ አልሆነም› የሚለው ቃል ትርጓሜም ጭምር ነው፡፡ ምክንያቱም ‹ሁሉ በወልድ ሕልውና ተፈጠረ ከተፈጠረውም አንዳች ስንኳ ያለ ወልድ ሕልውና አልተፈጠረም› ማለት ስለሆነ ነው፡፡ (ኢሳ. ፵፰፥፲፮)

ነቢዩ ኢሳይያስ ‹እግዚአብሔርን ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት› ብሎ ነበር፡፡ እግዚአብሔር አብን ያየው ማንም የለም ፤ ኢሳይያስ በራእይ በሰው አምሳል የታየው እግዚአብሔር ወልድ እንደሆነ ‹‹ዓይኖቼ የሠራዊት ጌታ ንጉሡን እግዚአብሔርን ስላዩ ወዮልኝ›› በሚለው ንግግሩ ታውቋል፡፡ (ኢሳ. ፮፥፭) ወንጌላዊውም ዮሐንስም ‹‹ክብሩን ስላየ ኢሳይያስ ይህንን አለ ፤ ስለ እርሱም ተናገረ›› ብሎ መስክሮለታል፡፡ (ዮሐ. ፲፪፥፵፩)

ነቢዩ ኢሳይያስ እግዚአብሔር ወልድን በመመልከቱ በኋላ ዘመን እግዚአብሔር ወልድን በአባቱ ቀኝ የተመለከተውን ቀዳሚ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስን መሰለ:: (ሐዋ. ፯፥፶፭) ሁለቱም ወልደ እግዚአብሔርን ያዩ ቅዱሳን በሰማዕትነት ያለፉ ሲሆን አሟሟታቸውንም ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ሰማዕታት በተናገረበት አንቀጽ ‹‹በድንጋይ ተወግረው ሞቱ በመጋዝም ተሰነጠቁ›› ብሎ በአንድ አንቀጽ ተናግሮታል:: (ዕብ. ፲፩፥፴፯)

ነቢዩ ኢሳይያስ ስለ እግዚአብሔር ሰው መሆን ያየውን በግልጥ ጽፎአል:: ‹‹እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች›› ብሎ ጽንሰቱን (ኢሳ. ፯፥፲፬) ፤ ‹‹ሕፃን ተወልዶልናል ፤ ወንድ ልጅም ተሠጥቶናል ፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ነው:: ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል›› ብሎ ልደቱን (ኢሳ. ፱፥፯) ፤ ‹ተጨነቀ ተሠቃየ› ብሎ መከራውን ፤ ‹በእርሱ ቍስል እኛ ተፈወስን› ብሎ ግርፋቱን ፤ ‹ከዓመፀኞች ጋር ተቆጠረ› ብሎ ከወንበዴዎች ጋር መሰቀሉን ፤ ‹ከክፉዎች ጋር መቃብሩን አደረጉ› ብሎ መቃብሩን (ኢሳ. ፶፫፥፩–፲) ፤ ‹የናሱን ብረት ሰበረ ፤ የብረቱን መወርወሪያዎች ቆረጠ› ብሎ ሲኦልን መመዝበሩን (ኢሳ. ፵፭፥፪) የጻፈ የነገረ ክርስቶስ መድበል ትንቢተ ኢሳይያስ ነው::

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ይህንን ተፈትፍቶ ያለቀ ወንጌል በማንበብ ላይ ስለቆየ ለፊልጶስ እጅግ ምቹ ተማሪ ነበረ፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስ ‹‹የሰማነውን ነገር ማን አምኗል?›› ብሎ የጀመረውን ሃምሳ ሦስተኛውን ምዕራፍ እያነበበ የነበረው ይህ ጃንደረባ ያመነበት ፍጥነት በእርግጥም ለነቢዩ ኢሳይያስ ‹ማን አምኗል?› የሚል ጥያቄ ‹ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ አምኗል› የሚል መልስ የሚያሠጥ ነው፡፡

## የጌታ መልአክ አዘዘው

ቅዱሳን መላእክት ለሰው ልጅ ድኅነት እጅግ የሚጓጉ ከእግዚአብሔር የተሠጡ ጠባቂዎቻችን ናቸው፡፡ እርግጥ ነው በመጀመሪያ እኛም እንደ መላእክት ክብሩን ለመውረስ ስሙን ለመቀደስ የተፈጠርን ነበርን፡፡ ግንኙነታችንም እርሱ ከእኛ ቀድመው በመፈጠራቸው ታላላቅ ወንድሞቻችን ናቸው፡፡ ከሰው ልጅ ውድቀት በኋላ ግን ነገሮች ተለወጡ፡፡ በእኛ የባሕርይ መጎስቆል ምክንያት ታላቅ ወንድም የታመመ ታናሹን እንደሚጠብቅ ጠባቂዎቻችን ሆኑ፡፡ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ እንዳለው የሰው ልጅ ከመላእክት ጋር ክቡር ሆኖ ሲፈጠር ጠባቂን አይሻም ነበር፡፡ ‹‹ሰው በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ግን እግዚአብሔር መላእክትን ጠባቂ

አደረገለት፡፡ ምክንያቱም ዲያቢሎስ ሰውን ለማጥፋት ሁልጊዜ ምክንያቶችን ስለሚፈልግ ነው››[44]

እነዚህ መላእክት ከጠባቂነታቸው ባሻገር ለሰው ልጅ መዳን እጅግ የሚጓጉ ሰውን ወዳጆች ናቸው፡፡ አምላክ ሰው ሆኖ በተወለደባት በዚያች ምሽት ሲዘምሩ ያደሩት በአምላክ ሰው መሆን የሚያገኙት ጥቅም ኖሮ ሳይሆን ለሰው ልጅ መዳን ካላቸው ፍላጎትና ፍቅር የተነሣ ነበር፡፡ ‹‹በሰማይ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ፤ በምድርም ሰላም›› የሚለው ዝማሬያቸው የእኛ ሰላም ለእነርሱ ምስጋና ምክንያት መሆኑን የሚያሳይ ምስጋና ነበር፡፡ (ሉቃ. ፪፥፲፬) የማያገቡትና የማይጋቡት እነዚህ መላእክት በሰማይ የሰርግ ያህል ደስ የሚሰኙት በምድር አንድ ኃጢአተኛ ንስሓ ሲገባ መሆኑ ምን ያህል የእኛ ወዳጆች መሆናቸውን ያሳየናል፡፡ (ሉቃ. ፲፭፥፲)

‹‹ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ መናፍስት አይደሉም?›› ተብሎ የተነገረላቸው እነዚህ መላእክት ለሰው ልጅ ካላቸው ፍቅር የተነሣ ለሁሉ መዳን የሚፋጠኑትን ሐዋርያት ለማገዝ ተልከው ሐዋርያት በሚገባ ተራድተዋል፡፡ (ዕብ. ፩፥፲፬) ሐዋርያት ጌታችን ባረገበት ዕለት መምህራቸውን ወደ ሰማይ

[44] St. Gregory of Nyssa, About the Life of Mosses in Migne, pp 44

ሸኝተው በትካዜ ሰማይ ሰማዩን ሲመለከቱ ከአሳባቸው ያባነኗቸው ሁለት መላእክት መጥተው ነበር፡፡ ‹‹የገሊላ ሰዎች ሆይ ስለምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሔድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል›› ብለው ሐዋርያትን ወደ ጸሎት አሠማርተዋቸው ነበር፡፡ (ሐዋ. ፩፥፲፩)

የሐዋርያት ሥራን ስናነብ መላእክቱ ሐዋርያትን ሲያግዙ ፣ ሲያስማሩ እናገኛቸዋለን፡፡ በሕልም በራእይ እየተገለጡ ሲያበረቱ ፣ የታሰሩትን ከወህኒ እያወጡ ወደ አገልግሎታቸው ሲመልሱ ፣ ‹ተነሥ ፣ ታጠቅ ጫማህን አድርግ› እያሉ ሲያግዙ ፣ ከወንዝ ማዶ ቆመው ‹ወደዚህ ተሻገርና እርዳን› እያሉ ሕዝቡን ወክለው ሲጣሩ እናገኛቸዋለን፡፡[45] መላእክት በሐዋርያት የወንጌል አገልግሎት ላይ ከነበራቸው ድርሻ መጠን ከመብዛቱና ከመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ጋር ከነበራቸው ቅርበት የተነሣ ክርስቲያኖች በተሰበሰቡበት ቤት በር ሲንኳኳ እንኳን ‹‹መልአክ ይሆናል›› እስከማለት ተደርሶ ነበር፡፡ (ሐዋ. ፲፪፥፲፫) አሁን ደግሞ አንድ መልአክ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ መዳንን ይወርስ ዘንድ ስለሚገባው ‹‹ፊልጶስን ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው ምድረ በዳ ወደ ሆነ መንገድ ሂድ አለው›› (ሐዋ. ፰፥፳፮)

---

45 የሐዋርያት ሥራ ፭፥፲፱ ፣ ፲፪፥፰ ፣ ፲፮፥፱ ፣ ፳፮፥፳፫

እዚህ ላይ መነሣት የሚገባው ትልቁ ጥያቄ መላእክት ሐዋርያቱን እየሔዱ ‹በዚህ ሒድ› ‹በዚያ ሒድ› እያሉ ከሚጠቁሙ ራሳቸው ለምን አይሰብኩም የሚለው ጥያቄ ነው:: ፊልጶስን ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው መንገድ እንዲሔድ ከመንገር ራሱ ፈጣኑ መልአክ ለምን ወደ ጃንደረባው ቀርቦ አያስተምረውም? በአጠቃላይ መላእክት ስለምን ሰዎችን በማስተማር በስብከተ ወንጌል አገልግሎት ላይ አልተሠማሩም? እግዚአብሔር ዛሬ ሰብኮ ነገ የሚታክተውን ፣ እንደ ዮናስ አልሔድም እያለ የሚሟገተውን የሰው ልጅ ሒድና አስተምር ከሚል ለምን መላእክቱን በቀጥታ ለሰው ልጅ አስተማሪዎች አላደረጋቸውም?

የምንሰብከውን መኖር ከሚሳነን ከእኛ ጋር ከሚታገል ስለምን ‹ፈቃዱን የሚያደርጉ መናፍስቱን› ከቅድስና ጋር እንዲሰብኩለት አላሰማራቸውም? እንደ ኢሳይያስ ከንፈሮቻችን የረከሱብንን እኛን ‹ማንን እልካለሁ› እያለ ከሚለምን የእኛን ለምጽ ጉጠት ይዞ በፍሕም የተኮሰውን ቅዱስ ሱራፌ ለምን አይልከውም? ከእኛ እነርሱ አይሻሉትምን? ቅድስና የሚያንሰንን ፣ ዕውቀት የሚከፈልብንን ፣ ግማሽ ዕድሜያችንን በእንቅልፍ የምናሳልፈውን እኛን ‹ሒዱና አስተምሩ› ከሚለን ትጉሐኑን ፣ አዋቂዎቹን ፣

ዕረፍት የማይሹትን ፤ ስሙን በምንም የማያስነቅፉትን መላእክት ስለምን አይልካቸውም?

ይህ የመላእክት ‹ሐዋርያትን ለወንጌል የማሰማራት ብቻ› ሚና የኦርቶዶክሳውያን አበውን ትኩረት የሳበ ጉዳይ ነበር፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ‹‹መላእክት እንዴት ስብከትን እንደሚያግዙ ተመልከቱ ፤ ራሳቸው ግን አይሰብኩም፤ ሰባክያኑን ግን ወደ ሥራ ይጠራሉ›› ሲል ቅዱስ አውግስጢኖስ ደግሞ ‹‹የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ለነበረው ጃንደረባ ያብራራለት ዘንድ መልአክ እንዳልተላከለት ወይንም ደግሞ በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ያለ ሰው እርዳታ ወንጌሉ መረዳት እንዳልቻለ እናስተውላለን፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ከእግዚአብሔር የተላከው መምህር ፊልጶስ ወደ እርሱ መጣ ፤ አብሮት ተቀመጠ ፤ በሰብአዊ ቃልና አንደበት ቅዱሱን መጽሐፍ አብራራለት›› ብሏል፡፡[46]

እርግጥ ነው በጣት የሚቆጠሩ ጊዜያት መላእክት ተገልጠው የምሥራች ሰብከዋል፡፡ ለዚህ ለዘካርያስ ‹የምሥራች ልሰብክልህ ተልኬያለሁ› ያለው ቅዱስ ገብርኤል (ሉቃ. ፩÷፲፱) ፤ ለእረኞች የሰበከላቸውና አብረውት የተገለጡት መላእክት (ሉቃ. ፪÷፲) ፤

---

46 St. John Chrysostom, Homily 15 On Acts, St. Augstine, On the Christian doctrines, pref. 7

ቅዱስ ዮሐንስ ‹‹በምድር ለሚኖሩ ለሕዝብም ለነገድም ለቋንቋም ለወገን ሁሉ ይሰብክ ዘንድ የዘላለም ወንጌል ያለው ሌላ መልአክ ከሰማይ መካከል ሲበር አየሁ›› ያለው በሰማይ ሲሰብክ የታየው መልአክ (ራእ. ፲፬፥፮) ፤ ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹እኛ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የተለየ ሌላ ወንጌልን የሰማይ መልአክም ቢሆን ቢሰብክ የተረገመ ይሁን›› ብሎ መናገሩ (ገላ. ፩፥፰) መላእክት አልፎ አልፎ በመገለጥ የምሥራችን መስበካቸውን ያሳያል፡፡ ይህ ግን እጅግ በጥቂት ቦታዎች የተፈጸመ እንጂ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን የማስተማር ሥራ ጨርሶ ለመላእክት አልተሰጠም፡፡

እርግጥ ነው ከኢትዮጵያዊው ጃንደረባው በተለየ መንገድ የእግዚአብሔር መልአክ ለቆርኔሌዎስ ተገልጦ በቀጥታ አነጋግሮት ነበር፡፡ (ሐዋ. ፲፥፫) ቆርኔሌዎስ መልአክ ይታየው ዘንድ የቻለው በጸሎትና በምጽዋት ይተጋ የነበረ ሰው ስለነበረ መሆኑን ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ‹‹ምጽዋት ለቆርኔሌዎስ የሰማይን በር ከፈተችለት›› በማለት መስክሯል፡፡[47]

ይሁንና መልአኩ ለቆርኔሌዎስ ቢገለጥለትም የማስተማሩን ሥራ ግን አልሠራም፡፡ ‹‹መልአኩም አለው፡- ቆርኔሌዎስ ሆይ ጸሎትህና ምጽዋትህ በእግዚአብሔር ፊት ለመታሰቢያ እንዲሆን ዐረገ

[47] St. Chrysostom, Homily Acts 22

፡፡ አሁንም ወደ ኢዮጴ ሰዎችን ልከህ ጴጥሮስ የሚባለውን ስምዖንን አስመጣ፡፡ እርሱ ቤቱ በባሕር አጠገብ ባለው በቍርበት ፋቂው በስምዖን ዘንድ እንግድነት ተቀምጦአል፡፡ ልታደርገው የሚገባህን እርሱ ይነግርሃል›› ሐዋ. ፲፥፭–፮

መልአኩ ራሱ ለቆርኔሌዎስ ሊያደርግ የሚገባውን መንገር ይችል ነበር፡፡ ሆኖም ወደ ጴጥሮስ ላከው እንጂ ራሱ አላስተማረውም፡፡ ‹‹ሁሉም ነገር በመላእክት መሣሪያነት ሊጠናቀቅ ይችል ነበር፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ከእኛ ከሰው ልጆች መካከል ለቃሉ አገልጋዮችን ጨርሶውኑ ባይመርጥ ኖሮ ለሰው ዘር መዋረድ በሆነ ነበር››[48]

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስን ባወደሰበት ድርሳኑ ‹‹መላእክት ወንጌልን ለእንዳንዱ ሰው ይሰብኩ ዘንድ ስለምን አይላኩም? ምክንያቱም በሰው ተፈጥሮና በመላእክት ተፈጥሮ መካከል ታላቅ ልዩነት አለ፡፡ ስለዚህ የሰው ልጅ ‹የእኔ ተፈጥሮ ከመላእክት ተፈጥሮ የተለየ እኮ ነው› ብሎ ለስንፍናውና ለቸልተኝነቱ ምክንያት እንዳያገኝ መላእክት ሰባኪያን ሆነው ወደ ሰው አልተላኩም፡፡ ሞትን የመንቀል ኃይል ያለው ቃል ፤ የኃጢአት ይቅርታን የሚሠጥ ቃል ፤ ለዕውሩ ብርሃን የሚመልስ

[48] St. Augstine, Christian Instractions, preface 6

ቃል ፣ ምድርን ወደ ሰማይነት የሚቀይር ቃል ከምድራዊው የሰው አንደበት መውጣቱ ምንኛ ይደንቃል?››[49]

በእርግጥም ቅዱሳን መላእክት ለእያንዳንዱ ሰው መምህራን ሆነው ቢላኩ እያንዳንዱ ሰው መላእክትን ለማየት የሚያስችል የቆርኔሌዎስ ዐይነት በጾምና ምጽዋት የበረታ ትከሻ የለውም፡፡ ‹ንጻሬ መላእክት› (መላእክትን መመልከት) ደግሞ ሁሉም ሰው የሚደርስበት መዐርግ አይደለም፡፡ ከዚያም በተጨማሪ አንድ ሰው በሰማይ መልአክ ቢሰበክለት ካለ ፍርሃት ነጻ ሆኖ አይሰማም፡፡ ወንጌል ደግሞ በነጻነት የምናምንባት እንጂ በፍርሃት የምንቀበላት አይደለችም፡፡

## ወይ ሰረገላው ሮጠ

ፊልጶስ ሐዋርያት ከሾሟቸው ከመጀመሪያዎቹ ሰባት ዲያቆናት አንዱ ነው፡፡ በዲያቆናቱ የስም ዝርዝር ከሊቀ ዲያቆናት እስጢፋኖስ በመቀጠልም በሁለተኛ ደረጃ የተቀመጠው እርሱ ነበር፡ ፡ (ሐዋ. ፮፥፭) ከሰባቱ ዲያቆናት ስድስቱ የተሠጣቸውን አደራ ተወጥተው ‹‹በዲቁና ሥራ በመልካም ያገለገሉ ለራሳቸው ትልቅ

---

[49] Preaching in the apostolic era , Fr. Tadros Malaty, page 4

ማዕረግና በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው እምነት ብዙ ድፍረት ያገኛሉ›› የሚለውን ቃል የፈጸሙ ነበሩ፡ ፡ (፩ጢሞ. ፫፥፲፫)

ከሰባቱ አንዱ ዲያቆን ኒቆላዎስ ግን ከህነቱን አፍርሶ ሃይማኖቱን ጥሶ ክህደት የሚያስተምር መናፍቅ ሆነ፡ ፡ በዚህም ምክንያት የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን አለቃ ሲመሰገን የተመሰገነበት በጎ ጎኑ ‹‹ይህ ነገር አለህ የኒቆላውያንን ሥራ ጠልተሃልና›› የሚል ሲሆን የጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን አለቃ ደግሞ ‹‹የኒቆላውያንን ትምህርት የሚጠብቁ ሰዎች በአንተ ዘንድ አሉ›› ተብሎ ተወቅሷል፡ ፡ (ራእ. ፪፥፮፣፲፭)

ከደጋጎቹ ዲያቆናት ቀዳሚው ቅዱስ እስጢፋኖስ ግን በጸጋ እግዚአብሔር ተሞልቶ ሲሰብክ አይሁድ በአፍም በመጽሐፍም ሊቋቋሙት ስለልቻሉ በግፍ በድንጋይ ወግረው ገደሉት፡ ፡ የእስጢፋኖስን ሞት ተከትሎ ክርስትና ይስፋፋ ዘንድ ፈጣሪ ወድዶ ነበርና ክርስቲያኖች መከራ ሲጸናባቸው ተሰድደው ወደየሀገራቱ ተበተኑ፡ ፡ በዚህ ጊዜ ከተበተኑት ክርስቲያኖች አንዱ ፊልጶስ ነበር፡ ፡ ከሰባቱ ዲያቆናት በተራ ቁጥር አንድ የተቀመጠው ከተገደለ ተረኛው ሁለተኛው መሆኑ አይቀርምና ዲያቆኑ ፊልጶስ ከኢየሩሳሌም ወጣ፡ ፡

እንደ ጌታውም ‹በሠማርያ ሊያልፍ ግድ ሆነበት› በሰማርያም ሰብኮ ብዙዎችን አሳምኖ አጠመቀ፡፡ ከኢየሩሳሌምም ጴጥሮስና ዮሐንስ መጥተው በተጠመቁት ላይ እጅ በመጫን ጸጋ መንፈስ ቅዱሳን አሳደሩ፡፡ ፊልጶስም ሐዋርያዊ ተልዕኮውን በተናቁት ሣምራውያን ላይ ጀመረ፡፡ ‹‹በኢየሩሳሌምም በይሁዳም በሠማርያም እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ›› የሚለውን የጌታችን የስብከት ካርታ ተከትሎ በመስበኩም የትምህርቱ ቃል ከሠማርያ ተነሥቶ የሳባ ንግሥት እስከመጣችበት ‹እስከ ምድር ዳርቻ› ድረስ ደረሰ፡፡

ከመጀመሪያዎቹ ዲያቆናት አንዱ የሆነውን ይህን ዲያቆን እስቲ እናመስግነው!? ነፍሳትን ለማዳን በምድረ በዳ መካከል በፍጥነት ከሚሔድ ከሰረገላ ጀርባ የሚሮጠውን ይህንን ዲያቆን «ዲያቆናት፡ ንጹሐን፡ እለ፡ አቅለሉ፡ ክነፊሆሙ፡ ለተልዕኮ፡ ምሥጢር››፡ (ለምሥጢር ይላኩ ዘንድ ክንፎቻቸውን ያቀለሉ ንጹሐን ዲያቆናት) የሚለው ምስጋና ምንኛ ይገባው ይሆን?

እግዚአብሔር ከሚጠላቸው ሰባት ነገሮች አንድዋ ‹ወደ ክፉ የምትሮጥ እግር›ን ከሆነ ሰውን ለማዳን የሮጡ የፊልጶስ እግሮች ምንኛ የተደነቁ ናቸው? (ምሳ. ፮፥፲፰) ‹መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቹ እንዴት ያማሩ ናቸው?› (ሮሜ ፲፥፲፭) እንደ

ጴጥሮስ አሕዛብን አስተምር የሚል ሕልም ማየት ሳያስፈልገው ወደ ሰማርያ የገሰገሰ ፣ አሁን ደግሞ አንድን አፍሪካዊ ለማዳን በእርሱም ወገኖቹን ለመታደግ የሚሮጠው ይህ ፊልጶስ እጥፍ ክብር ይገባዋል፡ ፡ የታቦተ ጽዮንን መማረክ ለመናገር ከሮጠው ወሬኛ ይልቅ ፣ የአቤሴሎምን ሞት ለመንገር ከሮጠው አኪማስ ይልቅ ለሌላው መዳን የሚሮጥ የመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ፈጻሚ ፊልጶስ ምስጉን ነው፡፡

በዚያች ምድረ በዳ በፍጥነት የሚገሰግሱትን የኢትዮጵያዊው ተጓዥ ፈረሶች ለማስቆም ፊልጶስ በትጋት ሮጠ፡፡ የጃንደረባው የቤተ መንግሥት ፈረሶች እንደ ከተማ ጋሪ የሚያዘግሙ ሳይሆኑ ሀገር አቋራጭ ጋላቢዎች ናቸውና ሳያመልጡት ሮጦ አስቆማቸው፡፡ ፊልጶስ ‹ወደ እኔ መጥታችሁ ተማሩ ፣ ደጅ ጥኑኝና ስሙኝ ፣ ጎዝጉዙልኝ ነስንሱልኝ!› የሚል ሰባኪ አልነበረም፡፡ ራሱ ደጅ ጸንቶ ፣ በትሕትና አባብሎ ፣ ተማሪውን በሩጫ እየተከተለ የሚያስተምር ፣ በፈረስ ተቀምጦ የሚታጀብ ሳይሆን ፈረስ እየተከተለ የሚሰብክ ትሑት መምህር ነበር፡፡ ለነገሩ ‹እስመ፡ስሙ፡ይመርሖ፡ ኀበ፡ ግብሩ›፡ (ስሙ ወደ ሥራው ይመራዋል) እንዲሉ የስሙ ትርጓሜም ከሥራው ጋር የሚሔድ ነው፡፡ ፊልጶስ ማለት በግእዙ ‹ፈያጼ፡አፍራስ›፡‹ነያኤ፡አፍራስ›፡(ፈረሶችን ገሪ) ማለት ሲሆን

በግሪኩም (Philos - ፍቅር Hippos - ፈረሶች) (መፍቀሬ አፍራስ) የፈረሶች ወዳጅ ማለት ነው፡፡

ቅዱስ ፊልጶስ ለኢትዮጵያውያ ቤተ ክርስቲያን የማይዘነጋ ባለ ውለታዋ ነው፡፡ በጋዛ መንገድ በምድረ በዳ በሩጫ እየተከተለ የዘላለም ሕይወትን ስንቅ ለጃንደረባው አስይዞ የሰደደላትን ይህንን ደግ ሐዋርያ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ‹‹የክርስትና አባትዋ ስለሆነ በስሙ ቤተ ክርስቲያን አንጻ ጽላት ቀርጻ ታከብረዋለች፡፡[50] በጸሎቱና በአማላጅነቱም ትታመናለች››[51]

መልክዐ ፊልጶስ በተሰኘው የምስጋና ጸሎትዋም ይህንን ዲያቆን ስታመሰግን ፡- ‹‹ሰላም ለእእዛኒከ እለ ሰምዓ በከዋላ ቃለ መንፈስ ቅዱስ ዘይቤ ትልዎ ለሰረገላ›› ‹‹ይህን ሰረገላ ተከተለው የሚለውን የመንፈስ ቅዱስ ቃል ለሰሙ ጆሮዎችህ ሰላምታ ይገባል››

---

[50] የኢትዮጵያውያን ባለ ውለታ ሐዋርያ የሆነው የዲያቆኑ ቅዱስ ፊልጶስ ብቸኛ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ደብረ ምጥማቅ ቅዱስ ፊልጶስ ተሰኝቶ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አነሳሽነትና መልካም ፈቃድ በ1978 ዓ.ም. የተመሠረተ ሲሆን በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ይገኛል፡፡ ዓመታዊ ክብረ በዓሉም ጥቅምት 14 እና የካቲት 20 ይከብራል፡፡

[51] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ልደት እስከ ዕሥራ ምዕት ገጽ ፲፮ /

‹‹ሰላም ለሰኰናከ ወለመከየድከ ዕጉሥ ፤ ሦከ አሜከላ በሊሀ በፍኖተ ሣምር መብእስ›› ‹‹በሰማርያ መንገድ ሹል የሆነውን እሾህ ለታገሰ ተረከዝህ ሰላምታ ይገባል!›› በማለት ታመሰግነዋለች፡፡[52]

## ሲያነብ ሰማው

ፊልጶስ ወደ ጃንደረባው በቀረበ ጊዜ ‹‹ሲያነብ ሰማ›› ይህም ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ መጽሐፉን በለኆሳስ ሳይሆን ድምፁን ከፍ አድርጎ ያነብ እንደነበር ያሳያል፡፡ ታሪክን መለስ ብለን ስንቃኝ ይህ ልማድ የጃንደረባው ብቻ ሳይሆን የጥንት አንባቢያን ሁሉ ልማድ እንደነበረ ለመረዳት እንችላለን፡፡

በጥንት ዘመን ቅዱሳት መጻሕፍትን ከሚያነቡ ይልቅ የሚሰሙ ሰዎች ቁጥር ይበዛ ነበር፡፡ ለዚህ መነሻ ምክንያቱ አብዛኛው ሰው መጻሕፍትን ለራሱ የመግዛት አቅም ያልነበረው ሲሆን ቢኖረውም የመጻሕፍት አቅርቦት ለሁሉ የሚዳረስ አልነበረም፡፡ ከዚያም ባሻገር በጥንታውያኑ ዘንድ ማንበብ የሚችሉ ሰዎች በቁጥር እጅግ ውስን ነበሩ፡፡ በዚህ የተነሣ መጻሕፍትን ከማንበብ መስማት የብዙኃን ልማድ ነበረ፡፡

[52] መልክዐ ፊልጶስ ግእዝና አማርኛ 1999 ዓ.ም. አዲስ አበባ

ከዚህ ባሻገር በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን መጻሕፍትን ጮኾ ማንበብና ምእመናንም በጽሞና መስማታቸው እጅግ የተለመደ ተግባር ነበር፡፡ ‹‹ይህች መልእክት በእናንተ ዘንድ ከተነበበች በኋላ በሎዶቅያ ሰዎች ማኅበር ደግሞ እንድትነበብ አድርጉ፡፡ ከሎዶቅያም የምትገኘውን መልእክት እናንተ ደግሞ አንብቡ›› (ቆላ. ፬፥፲፮) ‹‹ይህ መልእክት ለቅዱሳን ወንድሞች ሁሉ እንዲነበብ በጌታ አምላችኋለሁ›› (፩ተሰ. ፭፥፳፯) የሚሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች መጻሕፍትን ጮኾ ማንበብ የመጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን ባሕል እንደነበረ ያስረዳናል፡፡

ከሐዋርያት በኋላ ከተነሡ አባቶች አንዱ የሆነው ሰማዕቱ ዮስጦስ በዚያን ዘመን የነበረው ሁኔታ ሲገልጥ ‹‹ጊዜው የፈቀደውን ሰዓት ያህል የሐዋርያት መልእክታትና የነቢያት መጻሕፍት ይነበቡ ነበር›› ብሏል፡፡ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ይህንን ጥንታዊ ሥርዓት እስከ አሁንም ድረስ ጠብቃ የምትከተለው ሲሆን ቅዱሳት መጻሕፍትን አንድ ሰው ቆሞ ጮኾ የሚያነብበት ሥርዓት እጅግ የተለመደ ነው፡፡

ወንጌል ሲነበብ ደግሞ ‹‹ሣሌ ሉያ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን ቅዱሱን ወንጌል ቆማችሁ ስሙ›› ብሎ ዲያቆኑ ያውጃል፡፡ ምእመናንም ‹‹የከበረ የወንጌልን ቃል ለመስማት


የተገባን ያድርገን›› ብለው በዜማ ይመልሳሉ፡፡ ከዚህ በኋላም ቤተ ክርስቲያን ወንጌል የንጉሥ ቃል እንደመሆኑ ጥላ ዘርግታ መብራት አብርታ ታነበዋለች፡፡ የአምላክ ቃል እንደመሆኑ ደግሞ ‹በቅዱስ ወንጌልህ ቃል እናምናለን› እያለች ልጆችዋን ታሳልማለች፡፡

በለኆሳስ ማንበብ ወይም ለራስ ብቻ ማንበብ በጥንት ዘመን ጨርሶ አልተለመደም፡፡ አንድ ሰው ድምፅ ሳያሰማ ማንበቡ እንደ ብርቅ የሚነገርም ነገር ነበር፡፡ ከኒቅያ ጉባኤ በኋላ ከተነሡ አባቶች አንዱ የሆነው ቅዱስ አውግስጢኖስ ከእርሱ የቀደመ መምህሩ ቅዱስ አምብሮስ መጻሕፍትን በሆዱ ያለ ድምፅ ሲያነብ ባየ ጊዜ ተደንቆ እንዲህ ብሏል፡-

‹‹አምብሮስ ሲያነብ ዓይኖች ገጹን ቀርጸው ያስቀሩ ነበር፡፡ ልቡ ደግሞ ትርጓሜውን ይረዳ ነበር፡፡ ድምፁ ግን ዝም ብሎ ፣ አንደበቱም ጸጥ ብሎ ነበር፡፡ ማንም ሰው በነጻነት ቀርቦ ሊያነጋግረው ይችል ነበር፡፡እንግዶች የሚቀበለው ቀድማችሁ ንገሩኝ ሳይል ነበር፡፡ ልንጠይቀው ወደ እርሱ ስንሔድም እንዲሁ በዝምታ ሲያነብ አገኘነው ምክንያቱም እርሱ እንደሌላው ሰው ጮኾ አያነብም ነበር›› ብሎ እንደብርቅ ከስተት ጽፎታል፡፡[53] ሰው በሆዱ ከሚያነበው ይልቅ ጮኾ የሚያነበው የበለጠ በሕሊናው ተቀርጾ

[53] St. Augstine, Confessions, Book 6, Chapter 3

ይቀራል፡፡ የሚሰሙትም ሰዎች ቃሉን የበለጠ ይረዱታል፡፡ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባም ጮኾ ማንበቡ ይህ ሥርዓት ምን ያህል ጥንታዊ እንደነበረ ያስረዳናል፡፡



፲፡

# የሰረገላ፡ጉባኤና፡ጥምቀት

ይቤሉ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ለፊልጶስ፡፡
ሑር፡ትልዎ፡ለዝንቱ፡ሰረገላ፡ዘአፍራስ፡
ፊልጶስ፡መሀሮ፡ለባኮስ፡በእንተ፡ክርስቶስ፡
ወአጥመቆ፡በማየ፡ጥምቀት፡ሐዲስ፡

አንገርጋሪ፡ዘፊልጶስ

## የምታነበውን ታስተውለዋለህን?

መጻሕፍትን በማንበብ እና በማስተዋል መካከል እጅግ ሰፊ ልዩነት አለ፡፡ ከሁሉም ይልቅ ደግሞ ማስተዋል የሚጠይቀው መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ አይሁድ የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት ዕለት ዕለት በምኩራቦቻቸው ያነቡና ያስነብቡ ነበር፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹በየሰንበቱ የሚነበቡትን የነቢያትን ድምፆች ስላላወቁ›› ብሎ እንደገለጸው መጻሕፍትን ቢያነቡም አያስተውሉም ነበር፡፡ (ሐዋ. ፲፫፥፳፯) በዚህም ምክንያት ክርስቶስን ሰቅለው ለመግደል በቁ፡፡

በቃላቸው የሚያውቁትን የኢሳይያስን ትንቢትና የዳዊትን መዝሙር ማስተዋል ስላልቻሉ ራሳቸውን ለፍርድ አሳልፈው ሰጡ፡፡

በማንበብና በማስተዋል መካከል ልዩነት ስላለ ጌታችንም ባስተማረበት ጊዜ ስለ ነቢዩ ዳንኤል ትንቢት በተናገረ ጊዜ ደጋግሞ ‹‹አንባቢው ያስተውል›› ይል ነበር፡፡ (ማቴ. ፳፬፥፲፭) ከትንሣኤው በኋላም ለደቀ መዛሙርቱ ‹‹መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው›› ተብሎ ተጽፎአል፡፡ (ሉቃ. ፳፬፥፵፩)

አንድን መጽሐፍ ማንበብ ይቻላል ውስጡን ለመረዳት ግን የግድ ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡ አንዳንድ ሰው የመጽሐፍ ስም በተጠራ ቁጥር ‹‹አንብቤዋለሁ›› እያለ ይኩራራል ከመጽሐፉ ቢጠየቅ ግን አንዳች አይመልስም፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ሰው አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ሲገልጸው ‹‹ይትሜካሕ፡ በአንብቦታ፡ ወኢየአምር፡ ዘውስጢታ›› ‹‹በማንበቡ ይመካባታል ፤ በውስጥዋ ያለውን ግን አያውቅም›› ይለዋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሁልጊዜ አዲስ ሁልጊዜ እንግዳ የሆነና ባነበቡት ቁጥር አዲስ ነገር የሚያገኙበት ባሕር ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ እስከ የዮሐንስ ራእይ ድረስ አንብቦ ‹ጨርሼዋለሁ› ብሎ የሚያስብ ሰው መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሆነ ያልተረዳ ሰው ብቻ ነው፡፡ አንድ ግሪካዊ ካህን እንዳሉት መጽሐፍ ቅዱስ ማለት ተወልደህ ባደግህበት ቤት ውስጥ

የማታውቀው አዲስ ክፍል የማግኘት ያህል ሁሌ እንግዳ የሆነ መጽሐፍ ነው፡፡[54] ስለዚህ ማስተዋል ለመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ እጅግ ወሳኝ ነገር ነው፡፡

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ እያነበበ የነበረው የተፈጸመ ትንቢትን ነበር፡፡ በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን የሚለውን ስለ ክርስቶስ መከራ የሚናገረውን ቃል እያነበበ ቢሆንም ስለ ተገረፈውና ስለ ቆሰለው መሲሕ ግን ምንም አልሰማም ነበር፡፡ እግዚአብሔር ለዚህ ሰው የክርስቶስን መምጣት የሚናገር አስተማሪ የላከለት ከኢየሩሳሌም ሲመለስ ነበር፡፡ ወደ ኢየሩሳሌም ገና ሲጓዝ ስለ ክርስቶስ ቢማር ኖሮ ወደ ኢየሩሳሌም ሲደርስ በክርስቶስ ተከታዮች ላይ የሚደርሰውን መከራ በትኩረት ያይና ገና ከማመኑ መልሶ ወዲያው በመከራ ይፈተን ነበር፡፡

‹ለእግዚአብሔር የሥራ ጊዜ አለው› ተብሎ እንደተጻፈ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ወደ ጃንደረባው ፊልጶስን የላከለት በተገቢው ቅጽበት ነበር፡፡ ከፊልጶስ ጋር ሲገናኙ ጃንደረባው ከትንቢተ ኢሳይያስ ስለ ክርስቶስ መከራ በግልጥ የሚናገር ወሳኝ ምዕራፍ ላይ ደርሶ ነበር፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን ስረገላው ተጉዞ እስከ ውኃ ዳር እስከሚደርስ ድረስ ፊልጶስ ‹‹ከዚህ መጽሐፍ ጀምሮ ስለ

[54] Bishop Kallistos ware, Orthodox Study Bible, page 1757

ኢየሱስ ወንጌል›› በበቂ ሁኔታ ሊያስተምር የሚችልበትን ጊዜ ታሳቢ ያደረገ ነበር፡፡ ከተገናኙበት ውኃው ጋር እስከደረሱበት ያለው ሰዓትም ቀርቦ ፣ አናግሮ ፣ ሰብኮ እስከማጥመቅ የሚያስችል ትክክለኛ ቅጽበት ላይ ፊልጶስን ያደረሰው የእግዚአብሔር ዕቅድ ነበር፡፡

‹‹ፊልጶስ ወደ ሰረገላው ቀርቦ ‹‹የምታነበውን ታስተውለዋለህን?›› አለው፡፡ ጃንደረባውም ‹የሚመራኝ ሳይኖር እንዴት ይቻለኛል?› አለ››

ወዳጄ ሆይ ለአንድ አፍታ ከንባብህ ቀና ብለህ ነገሩን በራስህ አድርገህ አስበው፡፡ በመንገድ ላይ በትራንስፖርት ተሳፍረህ እያነበብህ ስትሔድ አንድ የማታውቀው ወጣት ቀረብ ብሎ ‹‹የምታነበውን ታስተውለዋለህን?›› ብሎ ቢጠይቅህ ምን ይሰማህ ይሆን?

ልብ በል ከዚህ በፊት አይተኸው የማታውቀው ሰው ‹የምታነበው ይገባሃል ወይ?› ሲልህ ምን ትለዋለህ? የአንተን ምላሽ አላውቅም በእኔ ገጠመኝ ግን ይህ ጥያቄ ምናልባትም ትልቅ ጠብ ሊያስነሣ የሚችል ይመስለኛል፡፡ ምናልባትም ‹‹የት ታውቀኛለህ? ላስተውለው ላላስተውለው አንተን ምን ያገባሃል?...›› ለሚል የተካረረ ንግግር መነሻም ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ በተራ ሰው ደረጃ

ነው:: ቁጭ ብሎ የሚያነበው ሰው ባለጠጋና የአንድ ሀገር የገንዘብ ሚኒስቴር ከሆነ ደግሞ ምላሹ ከበድ ሳይል አይቀርም:: ባለ ሥልጣኑ አሽከሮቹን ‹‹ይህንን ደፋር ልክ አስገቡልኝ›› ብሎ ሊያዝዝም ይችል ይሆናል:: እንዲህም የማያደርጉ ባለ ሥልጣናት ሊኖሩ ይችላሉ:: ሆኖም ‹የምታነበው ይገባሃል› ብሎ የጠየቀውን ሰው በሰረገላ ላይ አብሮት እንዲቀመጥ የሚለምን ትሑት ግን ብዙም ያለ አይመስለኝም::

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ‹‹ፊልጶስ ‹የምታነበውን ታስተውለዋለህን? ብሎ ሲጠይቀው አልተበሳጨም ፣ አልተቃወመም ፣ ብዙ ሞኝ ሰዎች እንደሚመስላቸው ክብሩ እንደተነካ አድርጎም አልቆጠረውም›› እጅግ የሚገርመው ወጣቱን ፊልጶስ ‹አንተ ማን ነህ? ከየት ሀገር ነው የመጣኸው?› ብሎ እንኳን አልጠየቀውም:: እንደ ሐዋርያ እንደ ዲያቆን ስላከበረው ነው ይህንን ዓይነት ትሕትና ያሳየው እንዳንል ሐዋርያ ይሁን ፣ ዲያቆን ይሁን የሚያውቀው ነገር የለም:: ይህ ጃንደረባ ማንነትህን ሳይጠይቅ የሚያከብር ትሑት ሰው ነበር:: ተርታ ልብስ ለብሶ ወደ ሰረገላው ለሚሮጥና ከዚህ በፊት አይቶት ለማያውቀው ሰው ‹የሚመራኝ ሳይኖር እንዴት ይቻለኛል?› ብሎ አለማወቁን ለመግለጥ አላፈረም:: ‹‹ለመማር ያለውን

ፍላጎትም ለመግለጥ አላፈረም ስለዚህ ተማሪ ለሆነው ለእርሱ የመንፈስ ቅዱስ ሥጦታ ተሠጠው›› ይህ ሥጦታም ወንጌል ነበር፡፡[55]

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዲህ ያደንቀዋል ፡-

‹‹ጃንደረባው ለውጪያዊ ገጽታ ምንም ትኩረት የማይሠጥ ሰው እንደሆነ ተመልከቱ፡፡ ‹አንተ ማን ነህ?› ብሎ እንኳን አልጠየቀውም፡፡ እንከን አልፈለገበትም ፤ ሊያስመስልም አልሞከረም ፤ እንደ አዋቂ ሊታይም አልወደደም፡፡ አለማወቁን ገለጠ እንጂ፡፡ ስለዚህ ተማሪ ፤ ቁስሉን ለሐኪሙ ገልጦ አሳየ ፤ ፊልጶስ ስለ ጉዳዩ እንደሚያውቅና ለማስተማር ፈቃደኛ የሆነ ሰው እንደሆነ ተረድቷል››[56]

የጃንደረባው ትሕትና ዕውቀትን የሚሻ ሰው ሁሉ ሊኖረው የሚገባ ትሕትና ነው፡፡ ብዙ ሰዎች ‹አላውቀውም› የምትለውን ቃል ከአፋቸው አውጥቶ መናገር እጅግ ይከብዳቸዋል፡፡ እንኳን ያነበቡትን መጽሐፍ ‹አልገባኝም› ለማለት ቀርቶ ያላነበቡትን መጽሐፍ ራሱ ‹አላነበብኩትም› ለማለት የሚቸገሩ ብዙዎች ናቸው፡፡ ‹‹ብዙ ሰዎች አለማወቃቸውን አምነው ከሌላው ለመማር መጠየቅ

[55] St. Athanasius, Festal letters 19.5
[56] St. John Chrysostom, On the Acts of the Apostles 19

ስለሚያሳፍራቸው ከአላዋቂነታቸው ጋር ለዘላለም መኖርን ይመርጣሉ››[57]

ዕውቀት ትሕትናን አጥብቆ ይጠይቃል፡፡ አንድን ዋንጫ በውኃ ለመሙላት ዋንጫው በመጀመሪያ ባዶ መሆን አለበት፡፡ ራሱን ባዶ ያላደረገ ሰው በዕውቀት ሊሞላ አይችልም፡፡ ትሕትና የሌለው ሰው ሁሉን አዋቂ መስሎ መታየት ይፈልጋል፡፡ የሚያውቀውን ዕውቀትም ሁሉ ከሌሎች በትምህርት ወይ በንባብ ያገኘው ሳይሆን አውቆት የተወለደ ያህል ይኮፈሳል፡፡ ከሌሎች ከመጠየቅ ሞትን ይመርጣል ፣ ከእርሱ የተለየ ሃሳብ ያላቸውን ሰዎች ለማዳመጥ አይፈልግም ፤ ‹ታውቀዋለህ ወይ› ተብሎ መጠየቁን ብቻ እንደ ስድብ ይቆጥረዋል፡፡

ምሁራዊ ትሕትና የሌለው ሰው ብዙ የተማረ ቢሆንም እንኳን በተማረበት ነገር ራሱም አይጠቀምም ሌሎችን አይጠቅምም፡፡ የማያውቃቸው ብዙ ነገሮች እያሉ የሚያውቃቸውን ነገሮች ብቻ ሲያገላብጥ ስለሚውል አዲስ ነገር የማይገኝበት እንደ ኩሬ ውኃ ባለበት የሚቀር ይሆናል፡፡ ጥያቄ ሲጠየቅም ከሚያውቀው ውጪ ከሆነ ይበሳጫል ፣ ጠያቂዎችን ይተቻል እንጂ ‹ቆይ በዚህ ጉዳይ እስቲ ላንብብበት› እንኳን አይልም፡፡

---

[57] St. John Chrysostom, On Genesis 35.5

እንዲህ ዓይነቱ ሰው በተጠየቀ ቁጥር አለማወቁ እየተገለጠ የሚመጣ ዓይነት ሰው ነው፡፡ ‹‹አንድ ነገር ብቻ አውቃለሁ ፤ እሱም ምንም አለማወቄን ማወቄን ነው›› በሚል ንግግሩ የሚታወቀውና ‹የምሁራዊ ትሕትና ጠባቂ ጻድቅ› (The patron saint of intellectual humility) ተብሎ የሚጠራው ግሪካዊው ፈላስፋ ሶቅራጥስ እንዲህ ያሉትን ምሁራዊ ትዕቢት (Intellectual arrogance) ይዞአቸው የማያውቁትን አላውቅም ለማለት የሚቸገሩ የተማሩ ደናቁርት በአደባባይ በመስቀለኛ ጥያቄ በማዋከብ አላዋቂነታቸው እንዲታወቅ የማድረግ ልምድ ነበረው፡፡

ምሁራዊ ትሕትና ያላቸው ሰዎች ጥፋታቸውን ለማወቅና ለመታረም የማያውቁትንም ለማወቅ ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎች ናቸው፡፡ ይህ የኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ምሁራዊ ትሕትና (Intellectual humility) ባለንበት ዘመን የታመነበት የዕውቀት በር የሆነ ጽንሰ ሃሳብ ሆኖ በሥነ ልቡናና በማኔጅመንት ትምህርት ዘርፍ እንደ ሙያ የሚሠጥ ለእውቀትና ለዕድገት እጅግ አስፈላጊ የሆነ አንድ የትምህርት ዓይነት እስከመሆን ደርሷል፡፡

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የገንዘብ ሚኒስቴር ነው ፤ ሀገራትን አቋርጦ የሚጓዝ ሰው ነው ፤ ንግድ አዋቂም ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ሁሉ እውቀቱ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የመተርጎም ሥልጣን

እንደማይሠጠው በሚገባ ተረድቶ የዲያቆኑን እርዳታ ጠየቀ:: አንዳንድ ሰዎች በሌላ የሙያ ዘርፍ ያላቸው እውቀትና በማኅበራዊ ዘርፍ ያገኙትን ስመ ማኅተም ምክንያት አድርገው በማያውቁት ጉዳይ ላይ ገብተው ይዘላብዳሉ:: ተዉ ሲባሉም ‹እኔ ስንት ነገር የሠራሁ ይኼ ሊያቅተኝ ነው?› ብለው ይኮፈሳሉ:: ጃንደረባው ግን ሥልጣንና እውቀት ያልፈተነው ትሑት ሰው ነበር::

‹የሚመራኝ ሳይኖር እንዴት ይቻለኛል› የሚለው የጃንደረባው ንግግር ለክርቲያኖች ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው የሚጠቁም መመሪያ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹እንደ ገባኝ መጠን ፤ እንደተረዳሁት›› እያሉ በመላምት የሚተረጎም መጽሐፍ አይደለም:: ‹‹ይህንን በመጀመሪያ እወቁ ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም›› ተብሎ በግልጥ እንደተነገረ እንደ መሰለው መተርጎም አይገባውም:: (፪ ጴጥ. ፩፥፳)

ጃንደረባው መጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ያለው መጽሐፍ መሆኑን ከማወቅ አልፎ ለመተርጎም ደግሞ የሚመራ ሰው እንደሚያስፈልግ ጠንቅቆ ተረድቶ ነበር:: ኦርቶዶክሳዊው የመጽሐፍ ቅዱስ አነባበብ አንዱ መገለጫም መጽሐፍ ቅዱስን ከቤተ ክርስቲያን ጋር ሆኖ ማንበብ ነው:: እንደሚታወቀው ከመጽሐፍ ቅዱስ በቁጥር

የወሰነችውና ከመጽሐፍ ቅዱስ በፊት የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ነበረች፡፡ ቤተ ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊ ፣ ቀጣሪና ሰፋሪ ናት፡፡ በዚህ የተነሣ አንድ አንባቢ መጽሐፍ ቅዱስን ሲያነብ ‹ቤተ ክርስቲያን ይህንን ቃል እንዴት ትተረጉመዋለች› ብሎ በቤተ ክርስቲያናዊ ንባብ (ecclesiastical reading) ማንበብ አለበት፡፡ እንዲህ ዓይነት ትሕትና ካለው እንደ ጃንደረባው ሁሉን ይማራል፡፡ ከጃንደረባው አጠገብ የነበረው ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን ፊልጶስ ነበር፡፡ እኛም መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት አጠገባችን ካሉ መምህራን ጀምሮ መጻሕፍትን ተርጉመው የጻፉ ሊቃውንትን በማንበብና በመጠየቅ መረዳት እንችላለን፡፡

የአሪት ዘሌዋውያን ትርጓሜው ቢጠፋበት ተማሪዎቹን አንድ ጊዜ ቆዩኝ ብሎ ጸሐፊውን ሙሴን በአካለ ነፍስ ጠርቶ ተርጉምልኝ ብሎ እንደጠየቀው እንደ አባ እንጦንስ በቀጥታ የመጽሐፉን ጸሐፊዎች የምናነጋግርበት ቅድስና ባይኖረንም እንኳን ቢያንስ እንደ ጃንደረባው አጠገባችን ያሉ መምህራንን አክብረን መጠየቅ ይገባናል፡፡ ጃንደረባው ፊልጶስን በወጣትነቱ ሳይንቅ ፣ ባለባበሱ ሳያናንቅ ወደ ሰረገላው ወጥቶ እንዲቀመጥ ለመነው፡፡

‹‹ራስን በመግዛት በጨዋነት መመለሱና ንግግሩን መቀጠሉ ብቻ አይደለም፡፡ ተራ ልብስን የለበሰውን የተናቀ ሰው ፊልጶስን ከአሕዛብ

ሀገር የመጣው ይህ ጃንደረባ በሰረገላው እንዲቀመጥ በመጋበዙ የጠባዩን መልካምነት አሳየን››[58]

## የማይናገረው በግ

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በሰረገላው ቁጭ ብሎ ሲያነብ በነበረው ምንባብ የክርስቶስ ስሞች ‹ጻድቅ ባሪያ› ‹በግ› የሚል ስያሜ ያለበት ነበር፡፡እስቲ ለአንድ አፍታ ብራናውን ዘርግተን ከጃንደረባው ጋር አብረን እናንብብ ፤ ያነበው የነበረው ክፍል በውስጡ ጥልቅ መልእክት ያዘለ የክርስቶስን ሥቃይ የሚናገር ነበር፡፡

ነቢዩ ኢሳይያስ ምዕራፉን ‹የሰማነውን ነገር ማን አምኗል የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገልጧል?› በማለት በጥያቄ ይጀምራል፡፡ በእርግጥም ኢሳይያስና እርሱን የሚመስሉ ነቢያት ስለ አምላክ ሰው መሆን ከፈጣሪ የሰሙትን የትንቢት ቃል ከመጽሐፍ አዋቂዎች ከአይሁድ ዘንድ ማን አምኗል? የእግዚአብሔር አብ ክንዱ የተባለው የወልደ እግዚአብሔር ነገርስ ለማን ተገለጸለት? የነቢዩ ንግግር በእውነትም ልክ ነበር፡፡

ነቢዩ የሚያምን የለም ብሎ ትንቢቱን አላቆመም፡፡ ‹‹በፊቱ እንደ ቡቃያ ከደረቅም መሬት እንደ ሥር አድጓል›› ብሎ ክርስቶስ

---

[58] St. John Chrysostom, On Genesis 35.5

ያለ ወንድ ዘር ያለ ሩካቤ ዘር ካልተዘራባት ከታተመች ድንግል መወለዱን ፣ ‹መልክና ውበት ያለውም ባየነውም ጊዜ እንወድደው ዘንድ ደም ግባት የለውም› ብሎ በደረሰበት መከራ የተነሣ አጥንቱ እስከሚታይ በመገረፉ ደምግባቱ መጥፋቱንና ከግርፋቱ የተነሣ ‹ሰው ፊቱን የሚሰውርበት› የተናቀ እንደሆነ ፣ የሰው ልጆች እኛን ለማዳን መቁሰሉን አለመረዳታችንንና በመስቀል በመሰቀሉ እንደተረገመና ‹በእግዚአብሔር እንደተቀሠፈ እንደቆጠርነው› የቆሰለው ቊስል ግን ለእኛ ፈውስ እንደነበረ ፣ ‹እንደ በግ ተቅበዝብዘን የጠፋነውን የሁላችንን በደል መሸከሙን› በዝርዝር ጻፈ፡፡

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ስለዚህ የሕማም ሰው እያነበበ ምንኛ ይጨንቀው ይሆን? እኛ እንኳን ማንነቱን አውቀን መከራውን በሰማን ጊዜ እንጨነቃለን፡፡ ይህ የበረሃ መንገደኛ በምድረ በዳ እየተጓዘ ሲያነብ ይህ የሕማም ሰው ማን መሆኑን ሳያውቅ እንዴት ይጨነቅ ይሆን? ጥላውን እያነበበ አካሉን የማያውቀው ፣ ትንቢቱን እያነበበ ፍጻሜውን ያልተረዳው ፣ ስለማይናገረው በግ የሚነግረው ያጣው ይህ የዋህ ሰው በቊስሉ የፈወሰውን ሐኪም ማንነት ለማወቅ ነፍሱ ስትጨነቅ ሁሉን የሚያስተምር ፣ መጽሐፍ ቅዱስን በትሕትና ለሚመረምሩ ሰዎች ሁሉ ረዳት የሚልክላቸው መንፈስ ቅዱስ

ለጃንደረባው ተርጓሚ ላከለት፡፡ የእግዚአብሔር በግ ማን እንደሆነም አብራርቶ ነገረው፡፡

መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠራባቸው ስሞች እጅግ ብዙ ናቸው፡፡ ቃል ፣ ጌታ ፣ ካህን ፣ ሊቀ ካህናት ፣ መምህር ፣ አገልጋይ ፣ የዓለም ብርሃን ፣ እረኛ ፣ መንገድ ፣ የበጎች በር ፣ የሰው ልጅ ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ፣ የዳዊት ልጅ ፣ ሁለተኛው አዳም፣ የአይሁድ ንጉሥ ፣ አልፋና ኦሜጋ ፣ የማዕዘን ድንጋይ ፣ የነገሥታት ንጉሥ ፣ ዓለት፣ እውነተኛ የወይን ግንድ ፣ ትንሣኤና ሕይወት ... እጅግ ብዙ ስሞች ስለ መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ተጽፈዋል፡፡

የስሞቹ መብዛት እግዚአብሔርን ሊገልጸው የሚችል አቅም ያለው አንድ ሰብአዊ ቃል አለመኖሩን ያሳያል፡፡ ለዚህም ነው ነቢዩ ዳዊት የሚገልጽበት ቃል ቢጠፋው ‹‹አንተ ግን ያው አንተ ነህ!›› ያለው፡፡ ‹የእግዚአብሔር በግ› የሚለው የክርስቶስ ስም እጅግ ብዙ ጥልቅ መልእክት ያለው ነው፡፡ በኦሪት ዘመን ስለ አንድ ሰው ኃጢአት መሥዋዕት አንድ በግ መሥዋዕት ሆኖ ይቀርብ የነበረ ሲሆን ክርስቶስ ግን ‹የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ› ነበረ፡፡ ይስሐቅ ለአባቱ ለአብርሃም ‹የመሥዋዕቱ በግ ወዴት አለ?› ብሎ ሲጠይቅ ‹እግዚአብሔር ያዘጋጃል› ብሎ የሠጠው መልስ

እውነተኛ ትርጉም ለይስሐቅ ብቻ ሳይሆን ለዓለሙ ቤዛ የተሠዋ ‹የእግዚአብሔር በግ እነሆ› ተብሎ የተነገረለት እርሱ ነው፡፡

በግ በበረት ውስጥ እንደሚወለድ በበረት ውስጥ የተወለደ ፤ በግ ሲወለድ እረኞች ደስ እንደሚላቸው ወደ ልደቱ ደስታ እረኞችን የጋበዘ ፤ የሚሠዋ በግ በቤተ ሳይዳ በበጎች በር በኩል እንደሚገባ ወደ ኢየሩሰሌም በበጎች በር የገባ ፤ በየዕለቱ የሚሠዉትን የእንስሳት መሥዋዕት ማሳለፉን ለማሳየት በጎችን ከእዚህ አውጡ ብሎ ራሱን ለዓለም የሚበቃ መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበ፡፡ በጲላጦስና በሔሮድስ ፊት ፤ በገራፊዎቹ ፊት ባሳየው ዝምታ የማይናገር በግ የተባለ ፤ በመስቀል ላይ በተናገራቸው ሰባቱ ቃላት ‹በግዕ፡ነባቢ› (የሚናገር በግ) የተባለ ነውር የሌለበት ንጹሕ በግ ክርስቶስ ነው፡፡

በግ ከሆነ እረኛ ለምን ይባላል የሚል ካለ ደግሞ ‹ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው› ለሆነ ለእርሱ ፍጹም እረኛ ፍጹም በግ ቢሆን ምን ይደንቃል? እንለዋለን፡፡ ቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም እንዲህ ብሏል ‹‹ይህ በግ እረኛ ተብሎ የተጠራና ራሱንም ‹መልካም እረኛ እኔ ነኝ› ያለ ነው፡፡ሰውነቱ በግ ነው ፤ በአምላክት ፍቅሩና ቸርነቱ ደግሞ እረኛ ነው››[59]

[59] St. Cyril of Jerusalem, Catechetical Lectures 10,3

‹እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ› የሚለው ንግግር ክርስቶስ በፈቃዱ ወደ ሞት እንደሔደባት ወደዚያች ዕለተ ዓርብ ይመልሰናል፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በቅዳሴያችን ‹በቁጣ ጎተቱት በፍቅር ተከተላቸው› ብሎ የመሰከረለት ክርስቶስ ሐሙስ ማታ ከተያዘበት ሰዓት አንሥቶ እስከተሰቀለበት ሰዓት ድረስ ወዲያ ወዲህ ሲያንከራትቱት ያለ ተቃውሞና ያለ ሽሽት የሚታረድ መሆኑን እንደማያውቅ የዋህ በግ በታዛዥነት መነዳቱን እናስታውሳለን፡፡

ክርስቶስን በቀራንዮ መንገድ ላይ እንደበግ ለመታረድ እንዲነዳ ያደረገው እንደበግ የሚመጣበትን የማያውቅ ሆኖ ሳይሆን ገመድ ሆኖ የጎተተው ለሰው ልጅ ያለው ፍቅር ነበር፡፡ ‹‹ኃያል ወልድን ፍቅር ከዙፋኑ ሳበው እስከ ሞትም አደረሰው ለሚስቡት ሰዎች በቀንዱ የማይበረታታ ፣ ለሚያርዱትም ሰዎች አንገቱን የሚያዘነብል ላም ምን ይደንቅ፡፡ በሚሸልተው ፊት የማይናገር በግ እንደምን ያለ ነው? በመከራው ጊዜ በሚወጉት ፊት አፉን ያልገለጠ ምን ዓይነት ትዕግሥት ነው?›› ይላል አባ ሕርያቆስም በቅዳሴው፡፡

‹‹የበግ ጠቦትም በሸላቹ ፊት ዝም እንደሚል፥ እንዲሁ አፉን አልከፈተም›› ይላል፡፡ በእስራኤል ባሕል በግ ጠጉር ተሸልቶ ወፍራም ልብስ ይሠራበታል፡፡ ይህን ለማድረግ በጉ በሚሸለትበት ወቅት ‹‹ይበርደኛል እባካችሁን አትግፈፉኝ›› ብሎ አይከራከርም፡፡

ሾላቾቹን ከብርድ እያዳነ ያለተቃውሞ ዝም ብሎ ይኖራል::
የክርስቶስ ዝምታም እንዲህ ነበር ፤ ዝምታው ግን አለመናገር ብቻ
ሳይሆን ኃይል ያለው ሰውን ከእግዚአብሔር ያገናኘ ዝምታ ነበር::
ቅዱስ አቡሊዲስ እንዲህ ይላል :-

‹‹ከነቢያት መካከል በመሣሪያ እየተጫወተ ትንቢትን
የተናገረው በግሪካውያን ትርጉም ትንቢቱ ‹መዝሙር› ተብሎ
የተጠራለት ንጉሥ ዳዊት ብቻ ነበረ.. የክርስቶስ ዝምታ ግን
በእውነት መሣሪያ ነው:: ሕብሩ ያማረ ፣ የተዋበ ፣ የተደረደረ
የሰው መምቻ የማይፈልግ በዜማ የማይለካ ከአብ ጋር የሚያገናኝ
መሣሪያ ዝምታ ነው››[60]

በዝምታው ለእኛ አንደበት ሆነን ፤ እንደ በግ ለመታረድ
በመነዳቱ ዲያቢሎስ ወደ ሲኦል ይነዳን የነበርን እኛን አዳነን::
ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ እንዲህ ሲል ያደንቀዋል:-

‹‹ይጸልያል ነገር ግን የሌሎችን ጸሎትም ይሰማል::
ያለቅሳል የሌሎችን ዕንባ ግን ያብሳል:: ሰው ነውና አልዓዛር ወዴት
እንደተቀበረ ጠየቀ:: አምላክ ነውና አልዓዛርን ከሞት አስነሣ::
እርሱ በርካሽ ዋጋ ያውም በሠላሳ ብር ብቻ ተሸጠ:: ነገር ግን
ዓለምን በውድ ዋጋ በከበረ ደሙ ገዛ:: እንደ በግ ለመታረድ ተነዳ

[60] Hyppolytus, Fragments on the Psalms 1.6

እርሱ ግን የእስራኤል እረኛ የዓለምም ሁሉ ጠባቂ ነበረ፡፡ እንደ በግ ዝም አለ ነገር ግን እርሱ በምድረ በዳ በሚጮኽ ሰው ድምፅ የተሰበከ ቃል ነበር፡፡ እርሱ የተሰቃየና የቆሰለ ነበር ፤ ሁሉንም በሽታና ቁስል ግን ይፈውስ ነበር››[61]

ነቢዩ ኢሳይያስ ክርስቶስን በአንድ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ሁለት ዓይነት በግ አድርጎ አስቀምጦታል ‹ለመታረድ የሚነዳ በግ› እና ‹የሚሸለት በግ›! በእርግጥ የእግዚአብሔር በግ ፋሲካችን ክርስቶስ በዕለተ ዐርብ ታርዷል? ወይንስ ተሸልቷል? መልሱ ሁለቱንም የሚል ነው፡፡

‹ለመታረድ ተነዳ› ሲል ሞትን የቀመሰ ሥጋውን (ትስብእቱን) የተሸለተ ሲል ደግሞ ሞት ሕያው የሆነ መለኮቱን እናስባለን፡፡ መሸለትና መታረድ የሚሉት ቃላት እንደ፡ አለቃና፡ እንደ፡ ጠበቃ፡ ይጠባበቃሉ፡፡ መታረድ የሚለውን ይዞ ሞተ እንጂ መለኮት አይደለም የሚል ቢኖር ‹በሸላቾቹ ፊት› ይልብሃል እንለዋለን፡፡ ‹በሸላቾቹ ፊት› የሚለውን ይዞ አልሞተም የሚል ቢኖር ‹ለመታረድ ተነዳ› ይልብሃል ብለን ነገረ ተዋሕዶን እናስረዳዋለን፡፡ ወይትባረክ፡እግዚአብሔር፡አምላክ፡አበዊነ፡፡

---

61 On the Son, Theological oration 3(29).20

የተሸለተ በግ በጠጉሩ ለሸላቾቹና ለሌሎች ሰዎች ሁሉ ልብስ ይሆናል፡፡ በዕለተ ዓርብ ስለኛ ልብሱን ተገፍፎ ዕርቃኑን በመሆኑ ዕርቃናችንን አልብሶልናል፡፡ ‹‹የተቤዠን በደሙ ብቻ አይደለም፤ በተሸለተው ጠጉሩ ዕርቃናችንን አለበሰ እንጂ፡፡ በልብስነቱም በከፋት ቆፈን የተያዝነውን አሞቀን፡፡ ሐዋርያው ‹የተጠመቃችሁ ሁላችሁ ክርስቶስን ለብሰናል› ብሏልና (ገላ. ፫፥፳፯)››[62]

## ነቢዩ ይህን ስለማን ይናገራል?

ጃንደረባው የነቢዩን ኢሳይያስን መጽሐፍ ትንቢት በሚገባ አንብቦ ተረድቶታል፡፡ የጠየቀው የትንቢቱን አቅጣጫ ነው እንጂ ማንበብ የቸገረው ሀ ሁ ቢስ (Illiterate) ወይንም ቋንቋ የከበደው ባዕድ ሆኖ አይደለም፡፡ ይህ ጃንደረባ በትክክል አንብቦ ሊረዳ በሚችለው ቋንቋ የተጻፈ የትንቢተ ኢሳይያስ ቅጂ እያነበበ ነበር፡፡

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ያነበው የነበረው ይህ መጽሐፍ በምን ቋንቋ የተጻፈ ነበር? የሚለው ጉዳይ ከዚህ ታሪክ ጋር ተያይዘው ከሚነሡ አከራካሪ ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡ በዕብራይስጥ ነው? በግእዝ ነው? በግሪክ ነው? ወይንስ በምንድር ነው? በሚለው ጉዳይ ላይ

[62] Bede, Commentary on the Acts of the Apotles 8.23

የተለያዩ ጸሐፍት ብዙ ብለዋል፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለዕሥራ ምዕት ባሳተመችው መጽሐፍ ላይ ፡-

‹‹ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ያነብ የነበረው በግእዝ ነበር፡፡ አንዳንድ ሊቃውንት ግን በግሪክ ወይንም በዕብራይስጥ ነው ብለዋል›› ያለች ሲሆን ይህም ‹የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተተረጎሙት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነው› የሚለውን በንቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የተጻፈውን አሳብ ከፊት ያስቀደመና ለሌሎች አሳቦችም ዕውቅና ያልነሣ ነው፡፡[63]

ሁለተኛው አሳብ ደግሞ ይህ ጃንደረባ ያነብ የነበረው የሰባው ሊቃናትን የግሪክ ቋንቋ ትርጉም ነው የሚል ነው፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ዶ/ር ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል ሲያትቱ ፡-

‹‹በአመዛኙ ጃንደረባው ያነብ የነበረው የሰባ ሊቃናትን የግሪክኛ ትርጉም (Septuagint) ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ያን ጊዜ የግሪክኛ ቋንቋ በኢትዮጵያ በተለይም በአክሱም ቤተ መንግሥት አካባቢ በሰፊው ይነገር ነበር፡፡ እንዲሁም ያነበው የነበረው ምንባብ ከዕብራይስጡ መጽሐፍ (Masoretic text) ይልቅ

[63] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከልደተ ክርስቶስ እስከ ሁለት ሺህ ዓመተ ምሕረት ገጽ 159

በአመዛኙ በግሪክኛ የተተረጎመውን የሰብዓ ሊቃናትን ትርጉም ይመስላል›› ብለዋል፡፡[64]

ግብፃዊው ካህን ቄስ ታድሮስ ያዕቆብ ማላቲ ደግሞ ጃንደረባው የሰባው ሊቃናትን ትርጉም በማንበቡ ላይ አጽንዖት ከሠጡ በኋላ ጃንደረባው የመጽሐፉን ጥቅል የተዋሰው ከእስክንድርያ ቤተ መጻሕፍት ነበር ብለው ጽፈዋል፡፡[65] ‹ጃንደረባው ግብፃዊ ባይሆንም የያዘው መጽሐፍ ከግብፅ ነው› ነው ነገሩ፡፡ ይህ እንኳን ‹‹ያም ለእኔ ይላታል ወደ እኔ›› የሚለውን የእናቶች መዝሙር የሚያስታውስ ድምዳሜ ነው፡፡

አንዳንድ ያሉ የግእዝ መዛግብትና የታሪክ ሊቃውንት ደግሞ ‹‹ዕብራይስጥ ሊሆን ይችላል፡፡ ሰባ ሊቃናት የተረጎሙት ይሁዲ ላልሆነው ዓለም ነው፡፡ ጃንደረባው ይሁዲነትን የተቀበለ ከሆነ በምንነቱ ነው ነው የሰባ ሊቃናትን ትርጉም የሚያነበው?›› የሚል ግምት አዘል ጥያቄ በማንሣት ይሞግታሉ፡፡ ያም ሆነ ይህ ይህ ጃንደረባ በሚገባው ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስን እያነበበ እንደነበረ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡

[64] ቀ/ዶ/ር ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል ፤ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በግእዝ ቋንቋ ፤ 2000 ዓ.ም አዲስ አበባ ገጽ 17
[65] Fr. Tadros Y. Malaty, Patristic commentary on the Act of the Apostles ch. 8

የትንቢቱን ገጸ ንባብ በሚገባ የተረዳ ቢሆንም ፊልጶስን ሲያገኝ ግን ‹ነቢዩ ይኼን ስለ ማን ተናግሮታል? ስለ ራሱ ነው ወይንስ ስለ ሌላ› በማለት ጠየቀ፡፡ አጠያየቁ የተራ አላዋቂ አጠያየቅ ሳይሆን በመልሱ ላይ ሚና ያለው ‹መልሱ ሀ ነው ወይንስ ለ› ብሎ አማራጭ የማቅረብ ዓይነት ጥያቄ ነበር፡፡ ንግሥተ ሳባ ወደ ሰሎሞን ስትመጣ አላዋቂ ሆና ልትማር የመጣች ሳትሆን የምትጠይቀው ጥያቄ ይዛ ሰሎሞንን ልትፈትነው እንደነበረና በኋላም በነገራት ጥበብ እንደተደነቀች ይህ ጃንደረባም የነቢያትን የትንቢት ሥልት አውቆ ዲያቆኑን በጥያቄ የሚፈትን ፊልጶስ ከሰሎሞን ስለሚበልጠው ክርስቶስ ሲሰብክለት የሚደነቅ ነበረ፡፡ የሳባ ንግሥት የጠየቀችውን ሀብት ሁሉ ተቀብላ ነፍስ ሳይቀርላት በደስታ ወደ ሀገርዋ እንደሔደች ይህ ጃንደረባም ጥምቀትን ጠይቆ ተቀብሎ ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ታድሎ መንገዱን ደስ እያለው ሔዷል፡፡ አፄ ዘርዐ ያዕቆብ ‹‹የኢትዮጵያ ሰዎች እውቀትን የተጠሙ ናቸው›› ያለው እውነቱን ነበር፡፡[66]

ጃንደረባው ነቢዩ ሊናገር የሚችለው ስለ ራሱ አሊያም ስለሌላ ሰው በመሆኑ ላይ እርግጠኛ ነው፡፡ ኢሳይያስ ትንቢቱን

---

[66]The book of light /መጽሐፈ ብርሃን/ አፄ ዘርዐ ያዕቆብ /translated by Prof. Ephraim Issaac /taken from his public lecture

የጻፈው ‹እኔ› ብሎ ባይሆንም እንኳን ነቢያት እኔ ሳይሉ ስለራሳቸው አርቀው ሊናገሩ እንደሚችሉ አንባቢው ጃንደረባ የመጻሕፍትን ልማድ በሚገባ ተረድቷል፡፡ የትርጓሚ ስልት አውቆ ይህንን ጥቅስ በየትኛው ስልት ልፍታው የሚል ሊቅ ጠያቂ ነበር፡፡ ንባቡን ይዞ ‹ሌላ ትርጉም አልፈልግም ፤ የተጻፈው ይኼ ነው› የሚል ችክ ያለ ተማሪ አይደለምና ለፊልጶስ የትምህርት ርዕስ ሠጥቶ ሊማር ቁጭ አለ፡፡

ይህንን ተከትሎ ፊልጶስ ለጃንደረባው ከትንቢቱ ትርጓሜ ተነሥቶ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን ሰበከለት፡፡ ውጤቱ እንጂ ይዘቱ ያልተጻፈልን ይህ በፍጥነት በሚሔድ ሰረገላ ላይ የተሰበከ ስብከት እንዴት ያማረ ይሆን? የጦርነት ስንቅ ተሸከመው በመጋለብ ፈንታ ወንጌላዊውን ከአዲስ ተማሪው ጋር ይዘው የጋለቡ እነዚያ ፈረሶች ምንኛ የታደሉ ናቸው? በክፋቱ ከነፈረሶቹ በባሕር የሚሠጥም ፈርዖንን የያዙት ፈረሶች ያልታደሉ ከሆኑ ወንጌል ተሸክመው የጋለቡና እንደ ግብፅ ፈረሶች በውኃ በመስጠም ፈንታ ከውኃ ዳር ባለቤታቸውን ሊያስጠምቁ ተለጉመው የቆሙት እነዚህ ፈረሶች እንዴት የከበሩ ናቸው? ያንን ‹የፈረስ ወዳጅ› የፊልጶስን ስብከቱን ሰምተውት ይሆን? ምነው እንደ በለዓም አህያ አንደበታቸው በተከፈተና ስለዚያ ፍቱን ስብከት በነገሩን?

ጃንደረባውን በዚያ ቅጽበት የለወጠ ፣ እንደ ኤማሁስ መንገደኞች የሰሚውን ልብ ያቀለጠ ይህ ስብከት እንዴት ያለ ይሆን? የኤማሁስ መንገደኞች ከኢየሩሳሌም ሲወጡ ክርስቶስ ከመካከላቸው ሆኖ እንዳናገራቸው ጃንደረባውም ከኢየሩሳሌም ወጥቶ ሲጓዝ ፊልጶስ ከመንገድ አነጋገረው፡፡ የኤማሁስ መንገደኞች ጌታን ‹ከእኛ ጋር እደር› ብለው እንደለመኑት ጃንደረባውም ፊልጶስን ከእኔ ጋር ተቀመጥ ብሎ ለመነው፡፡ (ሉቃ. ፳፬፥፲፫-፴፩)

የኤማሁስ መንገደኞች የነቢያት መጻሕፍት ሲተረጎሙላቸው ልባቸው እንደተቃጠለ ጃንደረባውም ፊልጶስ በተረጎመለት የትንቢተ ኢሳይያስ ትርጓሜ ልቡ ተቃጠለ፡፡ የኤማሁስ መንገደኞች ከጌታ እጅ ቁራሽ ተቀብለው ዓይናቸው ሲከፈት ጌታ ተሰወራቸው ፤ ጃንደረባው ደግሞ ጥምቀትን ተቀብሎ ፊልጶስ ከእርሱ ተነጠቀ፡፡ እነርሱ ወደ ኢየሩሳሌም ሊናገሩ ሲገሰግሱ ጃንደረባውም ወደ ዳግማዊት ኢየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ ገሰገሰ፡፡

### "እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድር ነው?

‹በመንገድም ሲሔዱ ወደ ውኃ ደረሱ ፤ ጃንደረባውም ፡- እነሆ ውኃ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድር ነው?›› አለ፡፡

‹‹አሁንም ትሕትናውን ተመልከቱ፡፡ አጥምቀኝ አላለውም፡፡ ዝምም አላለም፡፡ በመጓጓትና በፍርሃት መካከል ሆኖ ‹የሚከለክለኝ ምንድር ነው› ብሎ ተናገረ፡፡ የእምነትን ትምህርት በሚገባ እንደተማረ አያችሁ? የነቢዩ ኢሳይያስ ትንቢት ሥጋዌውን ፣ ስቅለቱን ፣ ትንሣኤውን ፣ ዕርገቱንና ምጽአቱን ያካተተ ነበር፡፡ ስለዚህ ትልቅ መጓጓትን ቢያሳይ አትደነቁ›› ይላል ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ[67]

በቅዱስ ጳውሎስ የተሰበከለት ፊልክስ የተባለው ሀገረ ገዢ ስለ ክርስቶስ የጳውሎስን ስብከት ከሰማ በኋላ ‹‹አሁንስ ሒድ በተመቸኝም ጊዜ ልኬ አስጠራሃለሁ›› ብሎ መልሶለት ነበር፡፡ ሆኖም ፊልክስ ከዚያ በኋላ ጳውሎስን አስጠርቶ አጥምቀኝ አላለም፡፡ ጭራሽ ጳውሎስን በእስር ቤት ተወው፡፡ (ሐዋ. ፳፬፥፳፭) ልናልፋቸው የማይገቡ የመዳን ዕድሎችን እንደ ዋዛ ማሳለፍ አይገባም፡፡

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ፊልጶስን ‹በል ከሰረገላው ውረድ ልኬ አስጠራሃለሁ› ብሎ ሊሸኘው አልወደደም፡፡ ‹የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል› ብሎ ሀገርኛ ተረት ተርቶም አልሸኘውም፡፡ ‹በተወደደ ጊዜ ሰምቼሃለሁ ፤ በመድኃኒትም ቀን ረድቼሃለሁ› የሚለውን የትንቢተ ኢሳይያስ ቃል ያነበበው ይህ ጃንደረባ ‹ቆይ ላስብበበት›

[67] St. John Chrysostom, On the Acts of the Apostles 19

ብሎ ለመዳን ቀጠሮ መሥጠት አልፈለገም፡፡ እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹እነሆ የተወደደው ሰዓት አሁን ነው ፤ የመዳን ቀን አሁን ነው›› ብሎ ተነሣ፡፡ (ኢሳ. ፵፱፥፰ ፤ ፪ቆሮ. ፮፥፪) የተማረውን ለመፈጸም ጊዜ ማጥፋት አልወደደም ‹ትእዛዝህን ለመጠበቅ ጨከንሁ አልዘገየሁም› ብሎ ሊዘምር ወደደ፡፡ (መዝ. ፻፲፰፥፰) ውኃ እንዳየ ጥምቀት ትዝ አለው ስለዚህ ‹‹እነሆ ውኃ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድር ነው?› ብሎ ጠየቀ፡፡

እንደ ባለ ሥልጣን ‹በል አጥምቀኝ› ብሎ አላዘዘም ፤ ምኞቱን ግን በትሕትና ተናገረ፡፡ በሐዋርያት ወንጌል የተሰበከላቸው ሰዎች ብዙዎቹ ‹ምን እናድርግ› ብለው ይጠይቃሉ ፤ ሐዋርያቱም ‹በኢየሱስ ክርስቶስ እመኑ ፤ ተጠመቁ› ብለው ያስተምሩአቸው ነበር፡፡ (ሐዋ. ፪፥፴፰) በአንዳንድ ቦታም ሐዋርያቱ ‹‹እንዳይጠመቁ ውኃን ይከለክላቸው ዘንድ የሚችል ማን ነው?›› ብለውም ሲያጠምቁ ታይቷል፡፡ (ሐዋ. ፲፥፵፯) ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ግን ለፊልጶስ ‹ምን ላድርግ› አላለውም ፤ ፊልጶስም ‹ተጠመቅ› አላለውም፡፡ ጃንደረባው ራሱ የመጠመቅ አሳብ አቀረበ፡፡ በዚህም ኢትዮጵያ የሐዋርያ ደም ሳታፈስስ ራስዋ የመጠመቅ ሃሳብ አቅርባ የተጠመቀች ሀገር ሆነች፡፡

‹‹ጃንደረባው ከእናቱ ከኢትዮጵያ ባገኘው የኦሪት ትምህርት ልቡናው የታደሰ ፣ አእምሮው የጎለመሰ በመኾኑ ኦሪት ወደ ክርስቶስ ስለመለሰችው ወዲያውኑ ነቢያት የሚያስተምሩትን ተቀብሎ ‹ውኃ ይኸው ብጠመቅ ማን ይከለክለኛል?›› ብሎ ሰረገላውን አቁሞ በፊልጶስ እጅ በክርስቶስ ስም ተጠመቀ:: በኦሪት ውጥን የነበረችውን ሃይማኖቱን ፍጹም አደረጋት›› ብለዋል አለቃ አያሌው ታምሩ::[68]

## ጸሎተ ሃይማኖት ዘባኮስ

ዲያቆን ፊልጶስ ለጃንደረባው የጥምቀት ጥያቄ የሠጠው መልስ ‹በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዷል› የሚል ነበር:: ‹በፍጹም ልብህ ብታምን› የምትለዋ የፊልጶስ ንግግር ከሰማርያ መልስ የተነገረች መሆንዋ በፍጹም ልቡ ሳያምን ከነክፋቱ ተጠምቆ መጨረሻ ላይ በጴጥሮስ ቃል ለመወገዝ የተዳረገው ሲሞን ዕጣ እንዳይደርስበት የሚያሳስብ ይመስላል:: ክርስቶስን ‹የእግዚአብሔር ልጅ› ለማለት አጋንንትም ‹የእግዚአብሔር ልጅ ሆይ ልታጠፋን መጣህን› ብለዋል::(ማር. ፩፥፯) እምነት ግን በፍጹም ልብ ሲሆን ይገባዋልና ‹በፍጹም ልብህ› አለው::

---

[68] አለቃ አያሌው ታምሩ ፣ የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት ገጽ 115

ይህን ጊዜ ጃንደረባው ‹‹ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ›› የሚል ድንቅ ዐረፍተ ነገር ተናገረ፡፡ ልብ አድርጉ ፤ ፊልጶስ ‹እንዲህ በል› አላለውም ፤ ገና የጥምቀት ሥርዓት ሙሉ በሙሉ ባልተሠራበት በዚያ ዘመን ይህ ጃንደረባ ግን የሃይማኖትን ጸሎት አረቀቀ፡፡ ለመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን የሥርዓት ቀመርም (Liturgical formula) የበኩሉን አስተዋጽኦ አበረከተ፡፡ ኢትዮጵያንም ከሠለስቱ ምዕት ዘመን ቀድማ በሐዋርያት ጉባኤ በንዑሰ ክርስቲያን የተወከለችና ለጸሎተ ሃይማኖትም ቃል ያዋጣች አደረጋት፡፡ በእርግጥም ከጃንደረባው አጠገብ የነበረው ፊልጶስ ሆኖ ነው እንጂ ክርስቶስ ቢሆን ኖሮ ለዚህ ንግግሩ ‹‹የሕንደኬ ጃንደረባ ሆይ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ እኔም እልሃለሁ አንተ ዓለት ነህ›› ባለው ነበር፡፡

አንድ ሰው ከመጠመቁ በፊት የሚጸልየው (ወይንም በዋሱ ዲያቆንና /ክርስትና አባት/እናት አንደበት የሚጸልየው) ጸሎተ ሃይማኖት (Creed[69]) ቤተ ክርስቲያን ከዘመነ ሐዋርያት እስከ ዘመነ ሰማዕታት ለአራት መቶ ዓመታት ቀስ በቀስ እየተሟላና እየተረቀቀ የመጣ ነው፡፡ አንድ ሰው ከመጠመቁ በፊት ‹ሰይጣን ሆይ

[69] በላቲን ‹Credo› ማለት ‹አምናለሁ› ማለት ነው፡፡

እክድሃለሁ› እንዲል ይታዘዛል::[70] ከዚያም ሃይማኖትን የሚገልጠውን ‹የሃይማኖት ጸሎት› ይደግማል::

የሃይማኖት ጸሎቱ ዋነኛ ዓላማ እምነትን መግለጥና በሚቃወሙ ፊት ምስክር ሆኖ መቅረብ ነው:: ቅዱስ ጴጥሮስ ‹አንተ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ› ያለው ‹ኤልያስ ነህ ሙሴ ነህ ይሉሃል› ከሚለው ተከትሎ መሆኑ የሃይማኖት ምስክርነት ቃል ከሚቃወሙ በተቃራኒ መቆም መሆኑን ያሳያል:: (ማቴ. ፲፮÷፲፮) ‹ጸሎተ ሃይማኖት› ብለን ዛሬ የምንደግመው ክፍለ ዘመናት የተሻገረ ጸሎትም በየዘመኑ በሚነሡ አረማዊያንና መናፍቃን ፊት የተሠጠ የምስክርነት ቃል ነው::[71]

ሐዋርያት በዘመናቸው የሚመሰክሩት በኢየሱስ ‹ክርስቶስነት› በማያምኑ በአይሁድ ፊት ስለነበር እንደ ሃይማኖት መግለጫ ‹ኢየሱስ ክርስቶስ ነው› ‹ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው› ይሉ ነበር:: ‹ክርስቶስ አይደለም ብሎ ኢየሱስን ከሚክድ በቀር ውሸተኛው ማን

---

[70] ዲድስቅልያ አንቀጽ 39፡16 ፤ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ሲጠመቅ ተጠማቂዎችን ‹እክህደከ ሰይጣን› ‹ሰይጣን እክህድሃለሁ› የማሰኘት ሥርዓት ገና አልተሠራም:: ሆኖም ጃንደረባው እንዳልጠመቅ ‹መኑ ይከልአኒ› ‹ማን ይከለክለኛል› እያለ የተናገረው ቃል ራሱ በሰይጣን ጆሮ ሲሰማ ከማመን ከመጠመቅ ለሚከለክል የሰው መዳን ጠላት ዲያቢሎስ የሚያሸማቅቅ የሃይማኖት አርበኛ ፉከራ ነው::

[71] Earily Christian Creeds, J.N.D. Kelly page 22

ነው?› ‹አንተም ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ብሎ መለሰለት› የሚሉት ቃላት ይህንን ያስረዳሉ፡፡ (፩ዮሐ. ፪፥፳፪ ፤ ማር. ፰፥፳፱)

ወደ ሮማውያን ግዛቶች ስንሔድ ደግሞ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ፈተና ‹ቄሣር ጌታ ነው› (Kurios kaisar) በሉ› የሚል ትእዛዝ ነበር፡፡ ጌትነቱ ተራ ጌትነት ቢሆን ዕዳው ገብስ ነበር ፤ በሮማውያን እምነት ግን እንደሚታወቀው ቄሣሮች እንደ አምላክ ይመለካሉ፤ ሲሞቱም በመቃብራቸው የሚቆመው ሐውልት ከአማልክት ተደምሮ ይታጠናል፡፡ ስለዚህ ቄሣርን ጌታ ነው ማለት ለክርስቲያኖች የክርስቶስን አምላክነት መካድ ነበር፡፡ [72]

ሮማውያኑ ቄሣርን ጌታ ከማሰኘት አልፈው ክብር ይግባውና ‹ኢየሱስ ርጉም ይሁን› (Anathema Iesous) በሉ ብለው ያሠቃዩአቸው ነበር፡፡ ቅዱስ ፖሊካርፐስ ‹‹ንጉሤን እንዴት እረግመዋለሁ?›› ብሎ ሰማዕት የሆነውም በዚህ ምክንያት ነበር፡፡ በዚያን ዘመን ‹ቄሣር ጌታ ነው› በሉ ሲባሉ እሳት ስለቱን ሳይፈሩ በአጸፋው ‹ኢየሱስ ጌታ ነው› (Kurios Iesous) ብለው በጣዖት አምላኪዎች ፊት መስክረው በሰማዕትነት የሞቱ ምእመናን ብዙ

---

[72] The Earliest Christian Confessions, /E.T/ London 1949, page 27-30

ናቸው፡፡[73] ለዚህም ነው ሐዋርያው መከራውን ሳይፈሩ ለመመስከር የቻሉት መንፈስ ቅዱስ አበርትቷቸው መሆኑን ሲገልጥ ‹‹በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር ኢየሱስ ጌታ ነው ሊል የሚችል ማንም የለም›› ያለው፡፡ (፩ቆሮ. ፲፪፥፫)

በአሁኑ ሰዓት የምንጸልየው ጸሎተ ሃይማኖት የሐዋርያትን ምስክርነት ፣ የኢትዮጵያዊው ጃንደረባን ፣ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖችን የዘመን ሰማዕታት ምስክርነት ፣ የዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤያትን ውሳኔዎች አካትቶ የያዘ የሺህ ዓመታት የጸሎት ግንብ ነው፡፡ ‹አንድ የአብ ልጅ በሚሆን በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ› የሚለውን የጸሎተ ሃይማኖት ክፍል ባነበብን ቁጥር ግን በዚህ የጸሎት አጥር ላይ

---

[73] ይህንን ቁጫርን ለሚያመልኩ ጣዖት አምላኪዎች የሚሠጥ ‹ኢየሱስ ጌታ ነው› የሚል የምስክርነት ቃል በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምኖ ሳያማትብና ሳይጸልይ ከቤቱ ለማይወጣ አርቶዶክሳዊ ምእመን እንደ አዲስ ሊነግሩና በፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት አገላለጽ የወነገለውን ለማወንገል (evangelizing the evangalized) የሚሞክሩ ሰዎች ምን ያህል እንደተሳሳቱ በዚህ መረዳት ይቻላል፡፡ አንዳንድ አርቶዶክሳውያን ‹ኢየሱስ ጌታ ነው› ሲሏቸው ‹ታዲያ እኛ ምንድን ነው አልን?› የሚሉት መልስ እንዲህ ታሪካዊ እውነታን ያዘለ ነው፡፡ ‹ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ› ብለው ለሚጠሩ ሰዎች ይህ ምስክርነት አይሠጥም፡፡

የመጀመሪያዎቹን ድንጋዮች በጋዛ ምድረ በዳ ያዋጣውን ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ልናስታውሰው ይገባል፡፡

## ፊልጶስ ዲያቆን ከሆነ "እንዴት ሊያጠምቅ ይችላል?

ጃንደረባው ‹‹ሰረገላው ይቆም ዘንድ አዘዘ ፊልጶስና ጃንደረባው ሁለቱም ወደ ውኃው ወረዱ አጠመቀውም››

ምሥጢረ ጥምቀት በቤተ ክርስቲያን ሲፈጸም ከጥንት ጀምሮ የተለመደው ሥርዓት ተጠማቂው ወደ ውኃ ውስጥ ገብቶ በመነከር (በመዘፈቅ) እና በመውጣት የክርስቶስን ሞት ፣ መቃብርና ትንሣኤ ማመኑን በሚያሳይ መንገድ ውኃ ውስጥ በመጥለቅ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ጥምቀት ሲናገር ‹በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ በጥምቀት ደግሞ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ› ብሎ የጥምቀት ሥርዓት ያለውን ተምሳሌታዊ ትርጉም አብራርቷል፡፡ (ቆላ ፪፡፲፪) በሌላ ሥፍራም ‹በውኃ መታጠብ ከቃሉ ጋር አንጽቶ› ‹ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብ› በማለት ጥምቀትን ‹መታጠብ› ብሎ ጠርቶታል፡፡ (ኤፌ. ፭፡፳፮ ፤ ቲቶ ፫፡፭) መታጠብ ደግሞ በመረጨት የሚከናወን ነገር አይደለም፡፡

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ቀደምት ክርስቲያኖች የጌታችንን ጥምቀተ ዮርዳኖስ ምሳሌ በማድረግ የሚጠመቁት ተንቀሳቃሽ በሆነ

በሚፈስስ በወራጅ ወንዝ ውኃ ነበር፡፡ ፍትሐ ነገሥትም ‹‹ወይኩን፡ ጥምቀት፡ ውስተ፡ ማይ፡ ውኂዝ፡ አው፡ በማይ፡ ዘይውኅዝ፡ ኀበ፡ ምጥማቅ፡ ፲፡ ወለእመ፡ ኮነ፡ ህየ፡ ዓጸባ፡ ይክዓዉ፡ ማየ፡ ዘረከቡ፡ ቀዲሆሙ፡ ኀበ፡ ምጥማቅ›› ይላል ‹‹ጥምቀት በወራጅ ውኃ ወይንም ወደ መጠመቂያው በሚፈስስ ውኃ ይሁን ፤ በዚያ ሀገር የውኃ ችግር ቢኖር ያገኙትን ውኃ ቀድተው ወደ ማጥመቂያው ያፍስሱ››[74]

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ለመጠመቅ ሰረገላውን አስቁሞ መውረዱ በኋላ በተሠራው የጥምቀት ሥርዓት ላይ አንዳች አመልካች ነገር ያለው ነው፡፡ እንደ ጌትነቱ አሽከሮቹን ከውኃው አስቀድቶ ማስመጣትና እዚሁ እርጩኝ ማለት ይችል ነበር ፤ ወይንም ሩቅ መንገድ በምድረ በዳ እየተጓዘ እንደመሆኑ በሰረገላው ላይ ሲሔድ የሚጠጣው ውኃ መያዙ አይቀርምና እዚያው ሰረገላው ላይ እርጩኝ ማለት ይችል ነበር፡፡ ጥምቀት ውኃ ውስጥ በመዘፈቅ የሚፈጸም መሆኑን በሚያሳይ መልኩ ጃንደረባው ሰረገላውን አስቁሞ ወደ ውኃ ወርደው ተጠመቁ፡፡[75]

---

[74] ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፫፥፳፮

[75] ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የተጠመቀበትን ትክክለኛ ሥፍራ በተመለከተ ብዙ ክርክሮች የሚደረጉ ሲሆን በወንጌላዊው ሉቃስ አተራረክ ከኢየሩሳሌም በስተደቡብ ወደ ሄብሮን በሚወስደው መንገድ ላይ ነው፡፡ በዚህ ጎዳና ላይ ብዙ ምንጮች መገኘታቸው ነገሩን ያወሳሰበው ሲሆን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊው አውሳብዮስ

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባን ያጠመቀው ወንጌላዊው ፊልጶስ ከሰባቱ የመጀመሪያ ዲያቆናት አንዱ መሆኑን ስናስብ ዲያቆን እንዴት ማጥመቅ ይችላል የሚል ጥያቄ በአእምሮአችን መነሣቱ አይቀሬ ነው፡፡ ለዚህም ይመስላል አንዳንድ ጸሐፍት የጃንደረባው አጥማቂ ፊልጶስ ዲያቆን መሆን አውኮአቸው ‹ሐዋርያው ነው› ወደ ማለት ያዘነብላሉ፡፡ ሆኖም ይህ ፊልጶስ ሐዋርያው አለመሆኑን ለመረዳት ትንሽ ከፍ ብሎ ታሪኩን ማንበብ ብቻ በቂ ነው፡፡ ስለዚህ ጃንደረባው በእርግጥም የተጠመቀው በዲያቆን እጅ ነበር፡፡

ባለ አንድ መክሊት ተብለው የሚጠሩት ተልዕኮ ብቻ ሥራቸው የሆነ ዲያቆናት በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ማጥመቅ አይችሉም፡፡ ፍትሐ ነገሥት ‹‹ወአልቦቱ፡ ለዲያቆን፡ ሥልጣን፡ ከመ፡ ይምሀር፡ ወያጥምቅ›› ‹‹ዲያቆን ያስተምርና ያጠምቅ ዘንድ ሥልጣን የለውም›› ሲል በመጽሐፈ ኪዳን ላይ የምናገኘው የአቡሊዲስ ቀኖና ደግሞ ‹‹ወዲያቆን፡ኢያጥምቅ፡ወኢያቍርብ፡ በዕዴሁ፡ ዘእንበለ፡ እምጽዋዕ፡ በእርፈ፡ መስቀል› ‹‹ዲያቆን

---

ቤት ዙር (Beth Zur) በተባለ ሥፍራ ጃንደረባው ተጠምቋል ብሎ ጽፎአል፡፡ በአሁኑ ሰዓት የፊልጶስ ምንጭ ተብሎ የሚጎበኘው የጃንደረባው የጥምቀት ሥፍ ግን ኤይን ያኤል ተብሎ ይጠራል፡፡ [One stop Bible Atlas, Nick Page, page103, ]

እያጥምቅ ፣ ከጽዋው በእርፈ መስቀል ካልሆነ በቀር በእጅ እያቍርብ›› ተብሎ ሥርዓት ተሠርቷል፡፡[76]

እርግጥ ነው አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ከተለመደው ሥርዓት በተለየ መንገድ ቤተ ክርስቲያን የሰዎችን ነፍስ ለማዳን ሲባል የምታከናውናቸው ነገሮች ይኖራሉ፡፡ አንድ ሰው መጠመቅ እየፈለገ ለሞት በሚያስጋ ሁኔታ በጠና ቢታመም እንደ ሥርዓቱ ቤተ ክርስቲያን መጥቶ ይጠመቅና ይቍረብ በማለት ፈንታ ካህናቱ ወደ ቤቱ ሔደው አጥምቀው ሥጋ ወደሙ የሚያቀብሉበት ሥርዓት (Clinical baptism) በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያችን አለ፡፡

አልፎ ተርፎም አንድ ሕፃን ከሞት አፋፍ ላይ ሆኖ የሚያጠምቀው ካህን ባይኖር ማንኛውም ክርስቲያን ‹በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቅሃለሁ› ብሎ በውኃ እንዲያጠምቀው ቀደምት አበው አዝዘዋል፡፡ ውኃ በማይገኝበት ሥፍራ ሕፃን ሊሞት ቢደርስ ደግሞ በዚያ ያለ ክርስቲያን ወንድም ሆነ ሴት ስመ ሥላሴን ጠርቶ በአየር ላይ ሦስት ጊዜ ከፍ የማድረግ ጥምቀት (Air baptism) እንዲፈጽምለት በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና የተፈቀደ ነበር፡፡

[76] ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 7፡249 ፣ መጽሐፈ ኪዳን ቀኖና ዘአቡሊዲስ 1

[77] ልጁ በሕይወት ከቆየ ጥምቀቱ አይደገምም ፤ ሜሮን ግን ይቀባል፡፡[78]

በመጽሐፈ ስንክሳር በሚያዝያ ሃያ አምስት ታሪከዋ የተመዘገበው ቅድስት ሣራ የተባለችዋ የአንጾኪያ ቅድስት ሁለት ልጆችዋን ልታስጠምቅ በመርከብ ተሣፍራ ወደ እስክንድርያ ስትጓዝ በድንገት ማዕበል ተነሥቶ ሊሰጥሙ ደርሰው ነበር፡፡ እናታቸው ሣራም ልጆቼ ሳይጠመቁ እንዳይሞቱ ብላ ጸሎት ካደረገች በኋላ የገዛ ጡትዋን አድምታ በደምዋ በልጆችዋ ላይ የመስቀል ምልክት ከቀባች በኋላ በባሕሩ ውኃ አጥምቃቸዋለች፡፡ ይህን ስታደርግ ወዲያው የባሕሩ ማዕበል ጸጥ አለ፡፡ ወደ ጳጳሱ ቅዱስ ጴጥሮስ ስትደርስ ሕጻናቱን ልታስጠምቅ ወደደች፡፡

ሊቀ ጳጳሱም ቅዱስ ጴጥሮስ ሁለቱን ሕጻናት ሊያጠምቅ ሲሞክር ውኃው እየረጋ አልነክር አለው፡፡ በመጨረሻም ሣራን ሲጠይቃት ልጆችዋ ሊሞቱ መስሏት ያጠመቀቻቸው መሆኑን ከአግራቸው ሥር ወድቃ ይቅርታን እየለመነች ነገረቻቸው፡፡ አባ ጴጥሮስ ግን ‹እምነትሽን አይቶ የልጆችሽን ጥምቀት እግዚአብሔር

[77] Orthodox Teachings. HE Panteleimon Lampadarios, page 449
[78] Lectures about Orthodox Faith, SUScopts, page 155

ተቀብሎታልና ድጋሚ እንዳላጠምቃቸው ከለከለኝ› ብሎ ጥምቀቱን ትቶ ሕፃናቱን ቅብዐ ሜሮን ቀብቶ አቊርቦ ሸኝቷቸዋል፡፡[79]

ወደ ዲያቆናት ማጥመቅ ስንመጣ አንዳንድ ጸሐፍት ‹‹በሐዋርያት ጊዜ ዲያቆንም መደበኛ ሆኖ ያጠምቅ ነበር››[80] ‹‹በመጀመሪያ ጊዜ ዲያቆን ያጠምቅ ነበር ፤ በኋላ ግን በቄስ ወይም በጳጳስ ብቻ እንዲሆን ተወስኗል››[81] ብለው ጽፈዋል፡፡ ይሁንና ከፊልጶስ ሌላ ዲያቆን ሆኖ አጠመቀ የሚል የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መዛግብት ላይ የተጻፈ የለም፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ግን የፊልጶስን ዲያቆን ሆኖ ማጥመቅ የሚተቹ ሰዎች የነበሩ ስለመሆናቸው የዲድስቅልያው ትርጉም በቅዱስ ጳውሎስ አንደበት የተነገረው ይህንን ያሳያል ፡-

‹‹ይህ ታላቅና መልካም የሆነ ፤ በመንፈስ ኃይል የነበረውና የሰማያት በር ተከፍተውለት ክርስቶስን በእግዚአብሔር ቀኝ ያየው እስጢፋኖስ ከዲቁና ማዕረጉ ገደብ ያለፈ አንዳች ነገር ግን ሲያደርግ አልታየም፡፡ መሥዋዕትን ሊሠዋ አልሞከረም ፤ እጆቹን በሌላው

---

[79] መጽሐፈ ስንክሳር ዘሚያዝያ 25, ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ 1999 ዓ.ም.
[80] ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ፤ ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ገጽ 42
[81] መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ፤ የኢ.ኦ.ተ.ቤ. መሠረተ ሃይማኖትና የካህናት ተልእኮ ገጽ 38

ላይ ሲጭንም አልታየም፡፡ የዲያቆንነቱን ሥርዓት እስከ መጨረሻው ድረስ ጠብቆ ኖረ እንጂ፡፡

ነገር ግን ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ አጥምቋልና አንዳንዶች ዲያቆናችን የሚሆን ፊልጶስን ፤ እኔን ጳውሎስን አጥምቋልና ታማኝ ወንድማችን የሆነ ሐናንያን የሚወቅሷቸው ካሉ እነዚህ ሰዎች የሚናገሩትን አያውቁም፡፡

ምክንያቱም አጽንተን የተናገርነው እንደ መልከ ጼዴቅና እንደ ኢዮብ (ኢዮ.42፡8) ከእግዚአብሔር ካልተሠጠው በቀር ወይንም አሮን ከሙሴ እንደወሰደ በሊቀ ካህናትነት ካልተሾመ በቀር ማንም ሰው የክህነትን ማዕረግ ለራሱ ነጥቆ መውሰድ እንደማይችል ነው፡፡ ፊልጶስና ሐናንያ ግን ለራሳቸው አልሾሙም ፤ ወደር በማይገኝለት ሊቀ ካህናት በክርስቶስ ለዚህ አገልግሎት የተመረጡ ናቸው እንጂ››[82]

---

[82] Yet still this so great and good a man, who was fervent in sprit, who saw Christ on the right hand of God, and the gates of heaven opened, there is no where appeared to have excersised functions which did not appertain to his office of a deacon, nor to have offerd the sacrifices, nor to have laid hands upon any, but kept his order of a deacon unto the end. But if some do blame Philip our deacon and Ananias our faithful brother, that the one did baptaize the Eunch, and one other me Paul, these men do not understand what we say. For we have affirmed only that no one snatchs the sacerdotal dignity to himself, but either receives it from God, as Melkesedek and Job, or from the high priest, as Aron from Mosses. Wherefore Philip and Ananias did not constitute themselves but were appointed by Christ, the High Priest of the

ስለዚህ የዲያቆን ፊልጶስ ማጥመቅ ጥምቀት በዲያቆናት እንዲፈጸም በይፋ ተፈቅዶ ሳይሆን የእግዚአብሔር ልዩ ምርጫ ነው የሚለው የሐዋርያቱ ድምዳሜ ነው፡፡ በአጠቃላይ የፊልጶስ ማጥመቅ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ሙሉ በሙሉ ተሠርቶ ባልተጠናቀቀበት እና በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ አገላለጽ ቤተ ክርስቲያን ‹‹ገና በጫካ ውስጥ መንገድ እየመረጠ እንደሚሔድ ሰው›› በምትጓዝበት ዘመን የተፈጸመ ሲሆን ያ ጊዜ ያለ ድንግልና ፓትርያርክ ድረስ የተሾመበት ገና ሐዋርያቱም ‹የቀረውን ስመጣ እደነግጋለሁ› እያሉ ቀጠሮ ይሠጡ የነበረበት ዘመን ነው፡፡ ይህንን አብነት አድርጎ የሐዋርያትን ሥልጣን በዘፈቀደ ይጣስ እንደነበረ አድርጎ መረዳት ወይም አሁን ላለንበት ዘመን ማጣቀሻ አድርጎ መሞገት አይገባም፡፡ ፊልጶስ በፈቃደ እግዚአብሔር ይህን ምሥጢር መፈጸሙን ግን በታላቅ አድናቆት እናስታውሰዋለን፡፡

ይህንን ተረድታ ነው መሰል በመንፈስ ቅዱስ ትእዛዝ ጃንደረባዋን ያጠመቀላትን ይህንን ዲያቆን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በስሙ በደረሰችለት ምስጋና እንዲህ ትለዋለች ፡-

‹‹ፊልጶስ፡ወንጌላዊ፡እስመ፡እንዘ፡ዲያቆን፡አጥመቀ፡
እምሐዋርያት፡ኢናሕፀፀከ፡ሕቀ፡

God, to whom no being is to be compared. /Constitution of the Holy Apostles, Book VII Sec. v. ANP vol.7, ccel, Philip Scaff/

እስመ፡ከመ፡እሉ፡አምላክ፡ኪያከ፡አልሀቀ››፡

‹‹ወንጌላዊ ፊልጶስ ሆይ ዲያቆን ስትሆን አጥምቀሃልና

አምላክ እንደነርሱ ስላከበረህ ከሐዋርያት ጥቂትም አናሳንስህም››

መልክአ ፊልጶስ

## ኢትዮጵያዊው ጃንደረባና ምሥጢረ ሜሮን

በቤተ ክርስቲያናችን ለመዳን ከሚያስፈልጉ ምሥጢራት የመጀመሪያው አንዱ ምሥጢረ ጥምቀት ሲሆን የሚከተለው ደግሞ ምሥጢረ ሜሮን ነው፡፡ ወንጌላዊው ዮሐንስ ‹‹ከቅዱሱ ቅባት ተቀብታችኋልና ሁሉንም ታውቃላችሁ›› ብሎ የተናገረለት ፣ ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ›› ብሎ ትንቢት የተናገረለት ማኅተም ሁሉን የሚያሳውቅ መንፈስ ቅዱስን የምንቀበልበት ምሥጢረ ሜሮን ነው፡፡ ይህን ምሥጢር የምንፈጽምበት ቀን የእያንዳንዳችን የግላችን ዕለተ ጰራቅሊጦስ የሚውልበት ቀን ፣ እረኛው መድኃኔ ዓለም ‹በበጎቹ

ላይ ምልክት የሚያደርግበት› ቀን ነው፡፡[83] (፩ ዮሐ. ፪፡፳ ፤ ኤፌ. ፬፡፴)

እርግጥ ነው በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን በተጠመቁ ምእመናን ላይ መንፈስ ቅዱስን የምታሳድረው ሐዋርያቱ (የዚያን ጊዜ ሊቃነ ጳጳሳት) ካሉበት ድረስ ተጠርተው መጥተው እጅ እንዲጭኑ በማድረግ ነበር፡፡ የምእመናን ቁጥር እየበዛ ሲመጣ ግን እነርሱን በየሥፍራው መጥራት የማይመች መሆኑ ስለታወቀ በእጅ መጫን ፈንታ እነርሱ በሲኖዶስ ተሰብስበው በጸሎት በሚያፈሉት ቅብዐ ሜሮን እንዲተካ በሎዶቅያ ጉባኤ በ፵፰ኛው ቀኖና ተወሰነ፡፡[84]

ዲያቆኑ ፊልጶስ ጃንደረባውን ከማጥመቁ በፊት በዚያው ምዕራፍ ላይ እንደምናነበው በሠማርያ አስተምሮ ብዙ ሰዎችን አሳምኖ አጥምቆ ነበር፡፡ ካጠመቀ በኋላ ግን እጅ ጭኖ መንፈስ ቅዱስን አላሳደረባቸውም፡፡ ይህንን የማድረግ ሥልጣን የሐዋርያት ስለሆነና ለእርሱም ስላልተሠጠው ጥምቀቱን በመንፈስ ቅዱስ ማኅተም ፍጹም ለማድረግ የሐዋርያትን መምጣት ይጠባበቅ ነበር፡፡ በኢየሩሳሌም የነበሩ ሐዋርያትም ይህንን በሰሙ ጊዜ እጃቸውን ይጭኑ ዘንድ ጴጥሮስና ዮሐንስን ወደ ሰማርያ መንፈስ ቅዱስን

[83] 'Personal pentecost of man' /Sacrament and Orthodoxy, Alexander Schmemann page 83/ St. Ephraim the Syria, Hymns on Virginity 7.6

[84] Dogmatic theology, Fr. Jossi Yakob, Course note Holy Trinity Theological College

እንዲያሳድሩ ላኳቸው፡፡ ሁለቱም ሐዋርያት መጥተው እጃቸውን ጫኑ ፤ በአንድ ወቅት በሰማርያ ሰዎች ተበሳጭቶ ‹እንደ ኤልያስ እሳት ከሰማይ ወርዶ ያጥፋቸው እንበልን?› ብሎ በእሳት ሊያስጠፋቸው የነበረው ወንጌላዊው ዮሐንስ ከወንድሙ ጴጥሮስ ጋር መጥቶ በሰማርያ ሰዎች ላይ የመንፈስ ቅዱስን እሳት አዘነመባቸው፡፡ (ሉቃ. ፱፥፶፬ ፤ ሐዋ. ፰፥፲፯)

ፊልጶስ የሰማርያን ሰዎች ካጠመቀ በኋላ ሐዋርያትን አስመጥቶ መንፈስ ቅዱስ እንዲወርድላቸው ካደረገ ለኢትዮጵያዊው ጃንደረባስ እጅ እንዲጭኑበት ሐዋርያትን ለምን አላስጠራለትም? ራሱ እጅ ጭኖ መንፈስ ቅዱስን አሳድሮበታል እንዳንል እንደዚያ የሚል ነገር አልተጻፈም፡፡ ታዲያ ጃንደረባው ተጠምቆ መንፈስ ቅዱስ ሳያድርበት እንዴት ይቀራል? ያለ መንፈስ ቅዱስ ጸጋ ጥምቀቱ ምሉዕ ሊሆን ስለማይችል የጃንደረባው ጥምቀት የተሟላ አይደለም ማለት ይሆን?

በእውነቱ ከሆነ ይህ ጃንደረባ እንደተጠመቀ ወዲያውኑ እጅ የሚጭን ሐዋርያ ሳይመጣለት ፤ ፊልጶስም እጅ ሳይጭንበት ፤ ሜሮንም ሳይቀባ መንፈስ ቅዱስ ወርዶለታል፡፡ ይህንን የሚያሳየን ‹‹ከውኃውም ከወጡ በኋላ የጌታ መንፈስ ፊልጶስን ነጠቀው›› የሚለው ቃል ነው፡፡ ምክንያቱም ፊልጶስን ነጥቆ የወሰደው

ለጃንደረባው የወረደ መንፈስ ቅዱስ ነበር፡፡ ዛሬ ካህናት ሕፃናትን ካጠመቁ በኋላ ‹ለሕፃናቱ የወረደ መንፈስ ቅዱስ ለሁላችን ይድረሰን› እንደሚሉ ፊልጶስ የተነጠቀው ለኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በወረደ መንፈስ ቅዱስ ነበር፡፡

ገድለኛው ጃንደረባ በዚህም ከሌሎች የሚለይ ክብርን አገኘ፡ ፡ ‹‹ያለ አንብሮተ ዕድ መንፈስ ቅዱስ በጃንደረባው ላይ አደረ ፤ ቅብዐ ትፍስሕት መንፈስ ቅዱስ እንደወረደለት ለማጠየቅ›› ይላል መጻሕፍተ ሐዲሳት ዘሠለስቱ ንባቡና ትርጓሜው፡፡ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር የምትዘረጋዋ ሀገር ሰው ሰለ ትሕትናው መንፈስ ቅዱስ እጁን ዘረጋለት፡፡ ‹‹የጥምቀቱ ምሥጢር ከተፈጸመ በኋላ እንደ ቀደመው ሐዋርያት እስኪመጡ ድረስ አልተጠበቀም፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ የሚገኘው በመዋቲ ሰዎች ፈቃድ ብቻ አለመሆኑ ይታወቅ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ወዲያውኑ ወረደ›› ይላል ቅዱስ አውግስጢኖስ[85]

‹‹የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሚሆን ደስታ ናት›› ተብሎ እንደተጻፈ ጃንደረባውን **መስተፍስሒ** (የሚያስደስት) የሆነ መንፈስ ቅዱስ ደስ አሰኘው፡፡

[85] St. Augstinus, Sermons On the selected Lessons of the New Testament, 49.11, Pilip Scaff, NPNF 106, www.ccel.org

(ሮሜ ፲፬፥፲፯) የደስታው ምንጭ መንፈስ ቅዱስ መውረዱ ብቻ አይደለም ያጠመቀው ሰው ፊልጶስ ተነጥቆ ሲሔድ በጻድቅ ሰው እጅ መጠመቁን እንዲረዳና ደስ እንዲሰኝ አድርጎት ነበር፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም ‹‹ፊልጶስ የተነጠቀው ከእግዚአብሔር መሆኑ እንዲታወቅና ተራ ሰው መስሎ እንዳይታየው ነበር፡፡ ደስ ያለውም ለዚህ ነው›› ይላል፡፡[86]

ያ ቀን ምን ዓይነት ቀን ነው? ጃንደረባው ሆይ ያን ቀን ምን ተሰምቶህ ይሆን? ከጥቂት ሰዓት በፊት ሰረገላህን ተከትሎ ሲሮጥ የነበረው ወጣት በመንፈስ ሰረገላ ተነጥቆ ሲለይህ ምን ተሰማህ? እንደ ኤልያስ ተማሪ አንጋጥጠህ እያየህ መጎናጸፊያውን ተቀብለህ ይሆን? ሕልም የሚመስል ቀን ያሳለፍከው ባኮስ ሆይ እስቲ ደስታህን አካፍለን፡፡ ከሰረገላህ ስትወርድ ተራ ሰው ነበርህ፡፡ ስትመለስ ግን ክርስቲያን ሆነሃል፡፡ ሰረገላህም ንዑስ ክርስቲያን አውርዳ በጥቂት ደቂቃዎች መልሳ ዐቢይ ክርስቲያን ጭናለች፡፡

ጃንደረባው ሆይ ጉዞህ እንዴት ቀጠለ? ትንቢተ ኢሳይያስን አንብበህ ጨረስከው ይሆን? ወይንስ ማንበቡን ተውከው? ስትሔድ ደስ የተሰኘኸው ምን አስበህ ይሆን? ‹ስለማይናገረው በግ› እጆችዋን ወደ ፈጣሪ ለዘረጋች ሀገርህ እስክትነግራት ቸኩለህ ይሆን? ደስ

---

[86] St. John Chrysostom, Homiles on the Acts of the Apostles, Homily 19, NPNF Philip Scaff, 1886

እያለህ የሔድከው ምን ብለህ እንደምትነግራቸው እያሰብክ ይሆን? ‹ነፍሴ የወደደችውን አገኘሁት› ‹የልቤን የነገረኝን ኑ እዩ› ልትል አቅደህ ይሆን? ታምሪን ለንግሥተ ሳባ ስለ ሰሎሞን እንደነገራት አንተም ከሰሎሞን ስለሚበልጠው ክርስቶስ ለሕንደኬ ልትነግር ጓጉተህ ይሆን?

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ፊልጶስ ከእርሱ ስለተለየ አላዘነም፡፡ ጌታውን ካገኘ ከሰባኪው ጋር ምን አለው? የተሰበከ ሰው እንደ ጃንደረባው ዝም ብሎ ‹መንገዱን መሔድ› እንጂ ‹ሰባኪው የት ደረሰ?› እያለ መከታተል አያስፈልገውም፡፡ ሰባኪውን እግር ከእግር ሲከታተሉ ስብከቱ የጠፋባቸው ብዙ ናቸውና ጃንደረባው መንገዱን መሔዱስ ጥሩ አደረገ፡፡

ቅዱስ ሄሬኔዎስ ስለዚያች ቀን እንዲህ ይላል፡-

‹‹ባጠመቀበት ቅጽበት ፊልጶስ ወዲያው ከእርሱ ተለየ፤ በነቢያት መጻሕፍት ለተማረው ጃንደረባ የሚያስፈልገው ጥምቀት ብቻ ነበር፡፡ እግዚአብሔርን የማያውቅ ሰው አልነበረም፡፡ ሕይወቱንም እንዴት መምራት እንዳለበትም የማያውቅ ሰው አይደለም፡፡ እርሱ ያላወቀው የእግዚአብሔርን ልጅ ሰው መሆን ነበር፡፡ ይህንን ዜና እንደሰማም ወዲያውኑ አምኖ የሀገሩ ሰዎች የክርስቶስን መምጣት አብሣሪ ሊሆን ደስ እያለው ሔደ፡፡ ስለዚህ

ፊልጶስ በዚህ የነቢያት መጻሕፍት በማንበብ እግዚአብሔርን በመፍራት በተዘጋጀ ሰው ላይ ብዙ መድከም አላስፈለገውም››[87]

## ጃንደረባው ሆይ ወዴት ነህ?

የቅዱስ ሉቃስ ትረካ የሚያበቃው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ‹ደስ እያለው መንገዱን ሔደ› ብሎ ነው፡፡ ይህ ጃንደረባ በእርግጥ ከተጠመቀ በኋላ ወዴት ደረሰ? ወደ ሀገሩ ሔዶ ሰብኮ ይሆን? ወደ ሌላ ሀገር ሔዶ ሰብኮ ይሆን? አኗኗሩ እንዴት ነበር? አሟሟቱስ?

ቅዱስ ጄሮም ጃንደረባውን ‹ለወገኖቹ ሐዋርያ ሆነ› ሲለው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊው አውሳብዮስ ደግሞ ከጥምቀቱ በኋላ ስለነበረው ቆይታ እንዲህ ይላል፡፡ ‹‹ይህ ሰው ከእስራኤላውያን ቀጥሎ ከወንጌላዊው ቅዱስ ፊልጶስ መለኮታዊውን ቃል ምሥጢር ለመቀበል ቀዳሚ ነበር፡፡ በዓለም ምእመናን በኵራት (የመጀመሪያ ፍሬ) ነበረ፡፡ ይህ ሰው ወደ ሀገሩ ተመልሶ ሕይወት ሠጭ የሆነውን የክርስቶስን በሰዎች መካከል መመላለስ የምታሳውቀውን ወንጌል ለመስበክ የመጀመሪያው ሰው እንደሆነ የታመነ ነው፡፡ ኢትዮጵያ

[87] Ireneuas Against Heretics

እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች የሚለው ትንቢትም ፍጻሜውን አግኝቷል›› [88]

ሰሎሞን በመኃልዩ ‹ጥቁር ነኝ ግን ውብ ነኝ› ያለውን በሥጋ ጥቁር መሆን በሃይማኖት ከመዋብ እንደማይከለክል የሚያሳይ መሆኑን ከሚተረጉሙት ቀደምት አበው አንዱ የሆነው ቅዱስ ኤፍሬም የጃንደረባውን ጥምቀትም በዚህ መንገድ ተቀኝቶበታል፡፡ ‹‹ጥቁሩ ኢትዮጵያዊው ተጠምቆ አበራ ፤ በደስታም ተጓዘ፡፡ አስተምሮ ደቀ መዛሙርትን አፈራ፡፡ ከጥቁሮች መካከል የሚያበሩትን አስገኘ፡፡ ኢትዮጵያዊያትን ለክርስቶስ የሚያበሩ ዕንቁዎች አድርጎ አቀረባቸው፡፡ ከኢትዮጵያ እንደተገኘ እንደሚያበራ ዘውድ አስጊጦ ለክርስቶስ አቀረባቸው›› [89]

ጃንደረባው ወደ ሀገሩ ተመልሶ መስበኩንና ለወገኖቹ ሐዋርያ መሆኑን ፣ በቤተ መንግሥት ክርስትናን መስበኩን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የመሰከሩ ቢሆንም ከዚያ በኋላ ስላለው ሁኔታ ግን በዝርዝር የተጻፈ ነገር አናገኝም፡፡ ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ይህ ጃንደረባ በሰበከው ስብከት ‹‹በእርሱም ዜና የኢትዮጵያ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ የጸጋ ወንጌል አመኑ›› ካለ በኋላ የጃንደረባው

[88] Eusabius, Eccelesisastical History book 2, vol. 1
[89] St. Ephraim the Syrian, The Pearl 13.3

ሚና መስበክ እንጂ ማጥመቅ እንዳልነበር ሲገልጽ ‹‹ዐቢየ ክርስቲያን ስለመሆን ግን ምክንያት አላገኙም ጃንደረባው ያጠምቃቸው ዘንድ ካህን አይደለምና›› (ወበእንተ፡ ከዊነ፡ ዐቢየ፡ ክርስቲያንሰ፡ ሰእኑ፡ምክንያተ፡እስመ፡ኢኮነ፡ካህነ፡ውእቱ፡ሕፅው፡ከመ፡ ያጥምቆሙ)፡በማለት ደምድሟል፡፡ (መጽሐፈ ምሥጢር ፳፥ ፴፰)

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባው የሰብከቱ አድማስ በኢትዮጵያ ብቻ የተወሰነ አልነበረም፡፡ ‹‹በርስትህ፡ በኢትዮጵያ፡ በአቅራቢያዋም፡ በኖብያ፡ በአሉድያ፡ ዳግመኛም፡ እስከ፡ ናፓታና፡ ሶባ፡ ድረስ፡ ክርስትናን፡ ለመስበክ፡ የዞርህ፡ የሕንደኬና፡ የሕዝብም፡ ሹም፡ ሆይ፡ በአፍሪካ፡ ውስጥ፡ ችግር፡እንዳይኖር፡ጠብቃት፡እያልህ፡ወደ፡ጌታህ፡ጸልይ› የሚለው ጸሎት የጃንደረባው ስብከት አድማስ ሰፊ መሆኑን ይመሰክራል፡፡[90]

ስለ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የሕይወት ፍጻሜና የአገልግሎት አድማስ ዘርዝሮ የመዘገበው በጉባኤ ኒቅያ ከታደሙ ሊቃውንት አንዱ እንደሆነ የሚነገርለትና በዘመነ ሰማዕታት በአረማውያን ተሰልቦ

[90] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ልደት እስከ ዕሥራ ምዕት ገጽ 13 (የጸሎቱ አቀማመጥ ግእዝ እንደሆነ ያስታውቃል ፤ ምንጭ ስላልተጠቀሰበት ዘሩን ማግኘት አልቻልሁም)

ጀንደረባ የነበረው የጢሮሱ ካህን ዶሮቴዮስ ነው፡፡ ለቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊው ለአውሳብዮስ መምህር እንደሆነ የሚነገርነት ዶሮቴዮስ ሲኖፕሲስ በተሰኘ ጽሑፉ ስለ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ያልተሰሙ መረጃዎችን መዝግቧል፡፡

በዚህም መሠረት ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በኢትዮጵያ ካስተማረ በኋላ ቀይ ባሕርን ተሻግሮ በፋርስ ፣ በዐረቢያ ፣ በሕንድና በብዙ የምሥራቅ ሀገራት ዞሮ እንደሰበከና በመጨረሻም ታፕሮባና ወይንም ሴይሎን ተብላ ትጠራ እስከነበረችው ደሴት ሔዶ እንዳስተማረ ፣ ምስክርነቱን በደም አትሞ በሰማዕትነት እንዳረፈ ፣ በክብር እንደተቀበረ በዚያን ዘመንም በመቃብሩ ተአምራት ይከናወኑ እንደነበረ ጽፏል፡፡[91]

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የስብከቱ ዳርቻ አድርጓት ነበር ተብላ የተጠቀሰችው ታፕሮባና ወይንም ሴይሎን ተብላ የተጠራችው በዛሬው አጠራር ሲሪላንካ ተብላ የምትጠራው ሀገር ናት፡፡ ከላይ ካየነው በቀር የሲሪ ላንካ የክርስትና ታሪክ ላይ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባን የሚያነሣ ብዙም የተጻፈ ነገር የለም፡፡ ሲሪላንካም እንደ ሐዋርያዋ የምትጠራው ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስን ነው፡፡ ሆኖም ከጃንደረባው ጋር በተያያዘም ባይሆን ክርስትና በሲሪላንካ በመግባቱ

[91] Lives of the Most Eminent Fathers of the Church vol. 1 87-88

ላይ ኢትዮጵያ ድርሻ ያላት ሆና መነሣትዋ አልቀረም፡፡ ከአንደኛው ክፍለ ዘመን አንሥቶ የአክሱማውያን ሀገር አቋራጭ ንግድ ማዕከል በነበረችው በአዱሊስ ወደብ በኩል ይካሔድ የነበረው ከፍተኛ የንግድ ልውውጥ እስከ ታፕሮባና ደሴት የተዘረጋ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ከአክሱም የሔዱ ኢትዮጵያውያን በታፕሮባና ወንጌልን መስበካቸውና ብዙዎችንም ወደ ክርስትና መመለሳቸውን በሲሪላንካ ክርስትና ታሪክ ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን መዝግበዋል፡፡[92]

## መፈጸም

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ምንም እንኳን ለኢትዮጵያና ለአፍሪካዊያን ሁሉ ኩራት ሊሆን የሚችል ክርስቲያናዊ ታሪክ ያለው ቢሆንም የሚገባውን ያህል አልተዘከረም ማለት እንችላለን፡፡ ይህ ሰው መንፈሳዊ ጉዞዎችን ለሚጓዙ ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለሚያነቡ ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን ለሚያደርጉና ለሚወያዩ ሁሉ አርአያ የሚሆን ውብ ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈለት ሰው ነው፡፡

ይህን ትጉሕ ተሳላሚ ፣ መጻሕፍተ ነቢያትን ደጋሚ ፣ እጅግ ትሑት ፣ አላዋቂነቱን ለመናገር የማይሰቀቅ ጻድቅ ፣

[92] Prabo Mihindukulasuriya, Another Ancient Christian Presence In Sri Lanka : The Ethiopians of Aksum, Journal of the Colombo Theological Seminary, Vol. III [2005]

ለመንፈሳዊ ነገር የተጠማ ፣ ቃሉን እየሰማ ራሱን የሚያስት ሳይሆን ወዲያው ተዘርቶበት ፍሬን የሚያፈራ ቅዱስ ፣ ስለ ክርስቶስ በፍጹም ልብ አምኖ የመሰከረ ሰማዕት ፣ ለሌሎች መዳን መንገድ የጠረገ ሐዋርያ ነውና በእውነት እጥፍ ክብር ይገባዋል::

አዳዲስ አማንያንን ወደ ክርስትና ለማምጣት የንዑስ ክርስቲያን አገልግሎትን ላይ የሚያገለግሉ ፣ የንባብን ባሕል በኢትዮጵያ ለማዳበር ለሚሹ ሁሉ የኢትዮጵያዊው ጃንደረባን ታሪክ የሚበልጥ ጥንታዊ መሠረት ያለው ኢትዮጵያዊ ተጠማቂም ሆነ አንባቢ የለም:: ቤተ ክርስቲያን በዝማሬዎችዋና በድርሰቶችዋ የምታወሳው ቢሆንም በስሙ ቤተ መጻሕፍት እንኳን ያልተሰየመለት መሆኑ አሳዛኝ እውነታ ነው::

እግዚአብሔር በእስራኤላውያን አዝኖ ሲናገር ‹‹ቀኑን ሁሉ ወደ ማይታዘዝና ወደሚቃወም ሕዝብ እጆቼን ዘረጋሁ›› ብሎ ነበር:
: (ሮሜ ፲÷፳፩) ወደ ኢትዮጵያ ግን እግዚአብሔር እጆቹን መዘርጋት አላስፈለገውም:: ምክንያቱም ‹‹ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር›› ስለዘረጋች ነው:: (መዝ. ፷፰÷፴፩)

ይህም አስቀድሞ በቅዱስ ኤፍሬም አገላለጽ ‹በተኩላዎች መካከል የተላከች በግ› በተሰኘችውና የሰሎሞንን ጥበብ ዝና ሰምታ በሔደችው በሳባ ንግሥት ማከዳ ፣ በብሉይ ኪዳኑ ጃንደረባ

በአቤሜሌክ ፣ ከስብእ ሰገል አንዱ በሆነው በባዜንና በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የተረጋገጠ እውነታ ነው፡፡ በሐዲስ ኪዳን መግቢያ ላይ የምናገኘውና ብሉይን ለብሳ ለቆየችው ኢትዮጵያ ሐዲስን ያጎናጸፋት ፣ ንባቡን ለምታውቀው ሀገር ትርጓሜውን ያመጣላት ፣ ግዝረትን ለተቀበለች ሀገሩ ጥምቀትን ያመጣላት ይህ ጃንደረባ በቅድስት ቤተ ክርስቲያ ስሙ መንሣቱ እስከ ምጽአት ይቀጥላል፡፡

‹‹ሁልጊዜ ድል በመንሣቱ ለሚያዞረን በእኛም በየሥፍራው ሁሉ የእውቀቱን ሽታ ለሚገልጥ ለአምላክ ምስጋና ይሁን›› ፪ቆሮ. ፪፥፲፬

# ለመጻፍ የተነበቡ


- ወንጌል ቅዱስ፤ ንባቡና ትርጓሜው ፤ 1997 ዓ.ም ፤ አዲስ አበባ ፤ ት/ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት
- መጽሐፈ ስዋስው ወግሥ ፤ ኪዳነ ወልደ ክፍሌ ፤ 1948 ዓ.ም. አዲስ አበባ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት
- የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡና ትርጓሜው 1988 ዓ.ም. አዲስ አበባ ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት
- ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው ፤ 1916 ዓ.ም. ፤ አሊጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ ማተሚያ ቤት
- ዜና ሐዋርያት (ነቅዐ ንጹሕ) ፤ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ፤ 1923 ዓ.ም. ፤ ጎሐ ጽባሕ ማተሚያ ቤት
- ሃይማኖተ አበው ቀደምት ፤ ኪዳነ ወልደ ክፍሌ ፤ ያልታተመ የእጅ ጽሑፍ
- የዛሬዋ ኢትዮጵያ የቅዱሳት መጻሕፍት ፤ የታሪክና የሥነ ጥንት ኢትዮጵያ ናት ፤ ቅዱስ ሲኖዶስ ፤ 1989 ዓ.ም. ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት
- የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግሥተ ሳባ እስከ ዐጽዋ ፤ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ
- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከልደተ ክርስቶስ እስከ ስሥሬ ምዕት ፤ የሊቃውንት ጉባኤ 2000 ዓ.ም
- የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ (ናፓታ- መርዌ) ፤ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ፤ 1965 ዓ.ም. ብርሃንና ሰላም ቀኃሥ ማተሚያ ቤት
- ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ ማኅበረ ቅዱሳን
- ሥርግው ሐብለ ሥላሴ (ዶ/ር) ፤ አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ፤ 1988 ዓ.ም. አዲስ አበባ
- መልክአ ፊልጶስ ግእዝና አማርኛ ፤ ደብረ ምጥማቅ ቅዱስ ፊልጶስ ቤተ ክርስቲያን 1999 ዓ.ም. 1999 ዓ.ም
- በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በግእዝ ቋንቋ ፤ ቀ/ዶ/ር ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል ፤ 2000 ዓ.ም. አዲስ አበባ
- የኢትዮጵየ እምነት በሦስቱ ሕግጋት ፤ አለቃ አያሌው ታምሩ ፤ 1953 ዓ.ም. አዲስ አበባ
- መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ፤ የኢኦተቤ መሠረተ ሃይማኖትና የክርስትና ተልእኮ
- ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ፤ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዓይ ፤ 1993 ዓ.ም. አዲስ አበባ
- Ancient Christian Commentary on Scripture, Acts, InterVarsity Press, Downers Grove, Illinios, 2006
- Ancient Christian Commentary on Scripture, Matthew, InterVarsity Press, Downers Grove, Illinios, 2006
- St. John Chrysostom, Homiles on the Acts of the Apostles,NPNF Philip Scaff, 1886

- St. Augstine of Hippo, Sermons, Philip Scaff, NPNF 1886
- Earily Christian Creeds, J.N.D. Kelly, 1960, London
- The Earliest Christian Confessions, London, 1949
- Ecclesiastical History, Eusebius Pamphilus of Caesarea, Book 1-5 /The Fathers of The Church
- The New Jerome Biblical Commentary, Theological p.i, Bangalore 2013
- All Articles Suscopts, His Grace Bishop Youssef, 2010 USA,
- Prabo Mihindukulasuriya, Another Ancient Christian Presence In Sri Lanka : The Ethiopians of Aksum, Journal of the Colombo Theological Seminary, Vol. III [2005]
- History of the Church, Rufinus of Aquileia 402, JASTOR
- Orthodox Teachings, His Eminence Panteleimon Lampadarios, Port Said, Egypt
- Dogmatic Theology, Fr. Dr, Jossi Yacob, HTTC, 2004, A.A.
- The Lives of the Most Eminent Fathers of the Church, vol 1
- The School of Alexandria, Origen, Fr. Tadros Y. Malaty, 1995, Sydney Australia
- Origen, The Early Church Fathers, Joseph W. Trigg
- Origen of Alexandria, Patristic commentary On the Gospel according to St. Mathew
- Sirgiw Hable Selasse, Anicent and MedivalHistory of Ethiopia, to 1270, 1972, Addis Ababa, United printers
- Amsalu Tefera, The Ethiopian Homily on the Ark of the Covenant, Brill Acadamic Pub, 2015
- Mebratu Kiros Gebru, Liturgical Cosmology, The Theological and Sacramental Dimensions of creation in the Ethiopian LiturgyGorgias Press, March 1 2010
- Sylvia Pankhurst, Ethiopia, A Cultural History, London Lalibela House, 1955
- Budge, A History of Ethiopia, Nubia and Abyssina, London, 1928
- Symbolic Interpretations in Ethiopic and Ephremic Litrature, Lee, Ralph, SOAS, University of London,
- A. Harnack, The Expansion of Christianity in the 1st three Centuries 1905
- Anthology of African Christianity, I. A. Phiri and D. Werner, C.Kaunda & K. Owino, WCC, 2016
- Preaching in the Apostolic Era, Fr. Tadros Y. Malaty, Sydney Australia,

ግብረ ሐዋርያት (ምዕ.8፡26-40) ኢትዮጵያዊ የመንግሥት ባለሥልጣን (ጃንደረባ) በመንፈስ ቅዱስ ምሪት በሐዋርያዊው ዲያቆን ፊልጶስ ጥምቀተ ክርስትና እንደተፈጸመለት ያስረዳል። የጥንት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች እና ሊቃውንት (ለምሳሌ ቅዱስ ሄሬኔዎስ፡ አውሳብዮስ ዘቂሳርያ፣ ዮሐንስ አፈወርቅ) ስለዚህ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ እና ስላጠመቀው ቅዱስ ፊልጶስ በሰፊው ጽፈዋል። አንዳንዶቹ ድርሳናትም ወደ ግዕዝ ቋንቋ ተመልሰዋል። አሁን ደግሞ የጃንደረባውን ታሪክ እና ከእርሱ ማንነት ጋር ተያይዘው የሚነሱትን ጥያቄዎች እና ሌሎች ተያያዥ ርእሶችን በመዳሰስ ማራኪ በሆነ አቀራረብ ከጠለቀ የማሰላሰል አመክንዮአዊ መንገድ ጋር በዚህ መጽሐፍ ቀርቦልናል።

ዲያቆን ሄኖክ በአሁኑ ሰዓት ቤተ ክርስቲያን ካሏት ኹነኛ አገልጋዮች በግንባር ቀደምነት ከሚጠቀሱት አንዱ ሲሆን ለየት የሚያደርገው በቃልም በመጣፍም ማስተማሩ ነው፤ ለዚህ ዋቢዎቹ ተወዳጅ ስብከቶቹ እና ካሁን በፊት ለአንባቢዎች ያደረሳቸው መጻሕፍቱ ናቸው። ስለ ጃንደረባው ያዘጋጀውን የመጽሐፍ ረቂቅ ተመልከትልኝ ብሎ ሲሰጠኝ በደስታ ተቀብልኩት፣ በጉጉት አነበብኩት። አቀራረቡ ማራኪ ሲሆን፣ እያስተማረ የሚሰብክ መጽሐፍ ሆኖ አገኘሁት። የሚከተለው መንገድ እያንዳንዱን ርእስ ስብከታዊ በሆነ መልኩ በመተንተን ሲሆን በእንግሊዝኛው Homiletical የሚባለው ዓይነት ነው። ይህም ጥንታውያን አበው ድርሳናቶቻቸውን የጻፉበት መንገድ ነውና ይበል ያሰኛል። ከባለቅኔው ከበደ ሚካኤል "የትንቢት ቀጠሮ"(1938 ዓ.ም.) በስተቀር ስለጃንደረባው በሰፋት የተጻፈ በሀገራችን እስካሁን አላጋጠመኝም። ስለዚህም ይህ የዲ/ሄኖክ ሥራ በዓይነቱም በይዘቱም ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ የሚሰጠው ፋይዳ ብዙ ነው። በመጨረሻም ይህን ግሩም ሥራ ያስነበበንን ዲያቆን ሄኖክ ኀይሌን እያመሰገንኩ፣ ደግመህ ደጋግመህ ጻፍ፤ እኛም በጥልቀት እናንብብ እላለሁ።

ቀሲስ ዶ/ር አምሳሉ ተፈራ
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥንታውያን ጽሑፎች ጥናት (ፊሎሎጂ) ረዳት ፕሮፌሰር

---

ተመራማሪዎች ቅዱስ ሙ[illegible] ጸሊምን፡ የማይጋ[illegible] (non-violent [illegible]) ብለው እንደ ሚጠሩት፡ የእርሱ ፍኖት በመከተል፡ የማይጋፋ የማስተማር [illegible] የሚከተለው (non[illegible]) መምህር ሄኖክ ኃይሌ በቀደሙ መጻሕፍቶቹ እንደ ተገለጠው የሚከተለው የ[illegible]ጻጻፍ ዘዴ፥ በበለጠ [illegible] ውስጥ ሰፊ፥ በትንሽ ውስጥ ብዙ እንዲለ እየደጋገመ የሚያሳ[illegible] ዘዴ ነው።

ንድፈ-ጽሑፉን ለማየት ‹ኢት[illegible]ጵያዊው ጃንደረባ› [illegible] ስጀምር፡ በፖለቲካ ዝንባሌ እንደተለከፈ ሰው፥ ገና ሳላነበው፥ ‹እንዲህ እንዲ[illegible] ሊል ይሆናል› [illegible] መጻፉ እርሻ ዘልየ በገባሁበት ጊዜ ግን፥ የቃረምኩት መንፈሳዊ ትምህርት፥ ከመጠን በላይ በስሎ፥ አበ[illegible] በፊት ለነበረኝ የተሳሳተ ድምዳሜ ሌላ መንፈሳዊ ዓይን ስላሳየኝ ደግሞ አድናቆትና አፍረትም ተሰማኝ፥ አድናቆ[illegible] ነው፥ እፍረቴ ደግሞ በዚያ ፖለቲካ ባዉረው ልቤ ነው። በላዔ መጻሕፍት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፥ በንባብ ዝንባሌ ላይ በተ[illegible]ረበት ጽሑፉ ‹መንፈሳዊ መጻሕፍት ማንበብ መነኩሴ አያደርግም፥ እውነተኛ ክርስቲያን ግን ያደርጋልና ስለዚህም በዓለማዊው ሥራ ለተጠመዳችሁስ ምንኛ ማንበብ ባስፈለጋችሁ› ይላል። ስለዚህ የዚህችን መጽሐፍ አንባቢዎች፥ "ስለ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ማንበብ፥ ኢትዮጵያዊ አያደርጋችሁም፥ እውነተኛ ክርስቲያን ግን ያደርጋችኋል" እላለሁ።

በረከት ዑቅባ ጽዮን
ደራሲና ተርጓሚ

ISBN 978-99944-75-94-0

ዋጋ. 81 ብር

ህትመት ጀጃው አታሚዎችና ዲስትሪቢዩተርስ ኃ.የተ.የግ.ማ.